S 16
5.1.92

# ሰውና እስስት

## አጫጭር ልብወለድ ታሪኮች

ከሙሉጌታ ጉደታ

1991
አዲስ አበባ

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
All rights Reserved

© Mulugeta Gudeta-1999

<u>በዚሁ ደራሲ</u>

- የአራዳ ልጆች
- የተከፋፈለ ልብ
- የእንባ ጠብታዎች
- የተቀጠፈች ፅጌረዳ
- ጭምብል

## <u>ማውጫ</u>


- ህልመኛው..........................5
- አስቻለው ዝምታ....................22
- ቤት የገባ ክረምት..................42
- ሰውና እስስት......................59
- አንድ ለመንገድ....................73
- የዋዜማው እንግዳ....................83
- የተገፋውና የተረሳው...............104

እድሜህን በሞላ የሰውን ልጅ ለመጥናት ብታውለው ጊዜህን በከንቱ ያጠፋህ እንዳይመስልህ

ዶስቶይቭስኪ

መታሰቢያነቱ

ለቸኮለች የኔሰው

# ህልመኛው

ለአሥራ ሦስት ሰዎች መንጓጓዣ ብትሰራም ከሃያ ተሳፋሪዎች በላይና ብዙ ሸቀጣ ሸቀጦች የተጫነችው ትንሿ የገጠር የመንገደኞች መኪና ወደ ጎባ ከተማ እየተጠጋች ስትመጣ ጌትነት በመስኮት በኩል ውጪ ውጪውን እየተመለከተ በሃሳብ ይብከነከናል።

"ዛሬ ቀኑ እርብ ነው። ነገ በአውቶቡስ ተሳፍሬ አዲስ አበባ እገባለሁ። እሁድን ውዱ ሰኞ ኮሌጅ እመዘገባለሁ። ዛሬ እዚሁ ጎባ አልቤርጎ ተከራይቼ አድርና ነገ በጠዋት ጉዞዬን እጀምራለሁ። አዲስ አበባ እንደደረስኩ ትንሽ ቀን እጎቴ ቤት አርፍና ከምዝገባው በኋላ ያቋረጥኩትን የኮሌጅ ትምህርት እቀጥላለሁ። ከአራት ዓመታት በኋላ በዲግሪ ተመርቄ ጥሩ ሥራ እይዛለሁ። ቆንጆ ቤት ተከራይቼ ዘመናዊ የቤት ዕቃዎችን እገዛለሁ። ቅዳሜና እሁድ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶችን እቤት እየጋበዝኩ እንደልቤ እዝናናለሁ። አሁን እንዲህ እንደ ሰማይ የራቀኝን ገንዘብ እንደ ልቤ እየመነዘርኩ እታይበታለሁ። አለሜን አይበታለሁ። ሁሉም ነገር ሲሰለቸኝ በመጨረሻ አንዷን ቆንጆ ልጅ ድል ባለ ሠርግ አግብቼ አዲስ ሕይወት እጀምራለሁ።

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የረጅም ጊዜ ምኞቴን አሳካለሁ ማለት ነው፡፡ ዘጠኝ ዓመት ሙሉ ሳልመው የኖርኩት ይሄንኑ ነበር፡፡ አቤት! ጊዜው እንዴት ይሮጣል... ገጠር ከገባሁ ዘጠኝ ዓመት ሆነኝ ማለት ነው? ቢሆንም ወደፊት በቂ ጊዜ አለኝ፡፡ ዘንድሮ ሃያ ስምንት አመቴ ነው፡፡ ከኮሌጅ ስመረቅ ሰላሳ ሁለት ዓመት ይሆነኛል ማለት ነው፡፡ ሰላሳ ሁለት ዓመት የወጣት እድሜ ነው፡፡ ከአራት ዓመት በኋላ በሰውነቴ ላይ ምንም ያህል ለውጥ አያመጣም..."

ጌትነት የገዛ መልኩን በሃሳቡ ተመለከተው፡፡ የጎፈረው ጥቁር ፀጉሩን፣ ምሁራዊ ጺሙን፣ ከሲታ ጠይም ፊቱን፣ የሲጋራ ጢስ ባያበልዛቸው ኖሮ ችምችም ብለው በቅለው ያምሩ የነበሩትን ጥርሶቹን ተራ በተራ በሃሳቡ ቃኛቸውና ከአራት ዓመታት በኋላ ብዙም እንደማይለወጡ በመገመትና በመፅናናት እንደገና በሃሳብ ተዋጠ፡፡

"አዲስ አበባ ከደረስኩ በኋላ ፀባዬን ማስተካከል ይኖርብኛል፡፡ ልክ አዲስ አበባ እንደ ደረስኩ ሲጋራ ማጤስ አቆማለሁ፡፡ ይሄንን የገንዘብ ጠር የሆነውን አመሌን ለአንዴና ለሁልጊዜ እርግፍ አድርጌ እተወዋለሁ፡፡ መጠጥም ቢሆን ሁለተኛ አልጠጣም፡፡ ጫትም አልቅምም፡፡ ኮሌጅ ከገባሁ ለምግቤና ለመኝታዬ አላስብም፡፡ ለአንድ ለሁለት ዓመት የሚበቃ ልብስ አለኝ፡፡ ደግሞስ ለተማሪ ብዙ ልብስ ምን ይሰራለታል? ለሁሉም ነገር ከተመረቅሁ በኋላ እደርስበታለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ የሴት ጓደኛም ቢሆን አልፈልግም፡፡ ትርፉ ገንዘብንና ጊዜን በከንቱ ማባከን ብቻ ነው፡፡ ትምህርቴን እስከምጨርስ ማለቴ ነው፡፡ ሃገር ቤት



ሄጄ ወላጆቼንና ዘመዶቼንም የምጠይቀው ከተመረቅሁ በኋላ ነው፡፡ ያውም የሁለት ወር ደመወዜን በቅድሚያ ካገኘሁ፡፡ ከወላጆቼ ከተለየሁ ይኸው ዘጠነኛ ዓመቴን ጨርሼ አስረኛዬን ይዣለሁ፡፡ አራት ዓመት ሲጨመርበት አስራ አራት ይሆናል፡፡ ምናልባትኮ በሕይወት ላይኖሩ ይችላሉ... ከሞት ማን ይቀራል? ለማንኛውም ግን መጀመሪያ እኔው እራሴ ሰው መሆን አለብኝ፡፡ የስከዛሬው ኑሮዬ ካሉት በታች ከሞቱት በላይ ነው፡፡ ነበርኩ እንጂ ኖርኩኝ ማለት አልችልም፡፡ ያውም በሁለት እግር መሄድና መተንፈስ መኖር ከሆነ..."

ጎባ ከተማ አቀበቱ ላይ ቂጢጥ ብላ ከሩቅ ትታያለች፡፡ በካፊያው ውስጥ ፀሐይ ብልጭ ብላ የተከዘችውን ትንሽ ከተማ ማፅናናት የፈለገች ትመስላለች፡፡

ጌትነት አሁንም ያስባል፡፡

"እንዲያውም ከአሁን ጀምሮ እራሴን መቆጣጠር መቻል አለብኝ፡፡ እናም አሁን በኪሴ የያዝኳቸውን ሲጋራዎች አጢሼ ከጨረስኩ በኋላ ሌላ አልገዛም፡፡ መጠጥም ቢሆን አልጠጣም፡፡ ኪሴ ውስጥ ስንት ብር ነው ያለኝ?... አዎን አራት መቶ ብር፡፡ አራት መቶ ምናምን ብር፡፡ ከአሁን ወዲያ ብዙም ወጪ የለብኝ፡፡ ነገ ወደ አዲስ አበባ መሄጃ የትራንስፖርት እከፍላለሁ፡፡ አቤት የማውቀው የጭነት መኪና ሹፌር ባገኝ! በነፃ አዲስ አበባ ያደርሰኝ ነበር፡፡ ግዴለም ይሁን፣ የቲኬት ሂሳብ እከፍላለሁ፡፡ ዛሬስ ምን ወጪ አለብኝ? አዎን! የአልቤርጎና የእራት፡፡ እራቱን እንኳን ልተወው እችላለሁ፡፡ አልቤርጎ ግን

አይቀርም፡፡ መቼም ሜዳ ላይ አላድርም፡፡ ምናለበት አሁን እዚህ ጎባ ውስጥ ዘመድ ወይንም ጓደኛ ቢኖረኝ ኖሮ! ስድስት ብር አድን ነበር፡፡ ረከስ ያለ አልቤርጎ ባገኝ ጥሩ ነበር፡፡ እንዳለኩት ገንዘቤን በጥንቃቄ መያዝ አለብኝ፡፡ አመልን በጉያ ነው ካሁን ወዲያ... ትልቅ ዓላማ ከፊቴ ደቅኜ እንደ ድሮው ያስረሽ ምችው ኑሮዬን መቀጠል አልችልም፡፡ ሁለቱ አብረው አይሄዱም፡፡ እራሴን መግዛት መቻል አለብኝ፡፡ እራሴን መቆጣጠር አቅቶኝ ነው ዘጠኝ ዓመት ሙሉ ነገ ዛሬ ስል ገጠር ውስጥ በስብሼ ልቀር የነበርኩት፡፡ አሁን ግን... ተመስገን ነው፡፡ ልብ ሰጠቶኝ በቆራጥነት ሕይወቴን ለመለወጥ ተነስቼአለሁ፡፡ ሁለተኛ የገጠርን ኑሮና የመምህርነትን ሥራ ለጠላቴም አይስጠው፡፡ እንደ ጠመኔ የሚበን አመዳምና ብኩን ሕይወት... ከአሁን ወዲያ ማንኛውም ነገር የሚወሰነው በእኔ ቆራጥነት ነው፡፡ አይዞሽ ጌትነት! አሁንስ ከዚህ ከአመዳም ሕይወት ነፃ ልትወጪ ነው... ከኩራዝ ወደ ኤሌክትሪክ፣ ከወንዝ ውኃ ወደ ቧንቧ፣ ከጎባ ወደ ፒያሳና ወደ ጆሊ ባር፣ ከገጠር ፅድቅ የከተማ ኩነኔ! ያውም የመምህርነት ሕይወት! ዲስክሪሲያቶ!..."

ትንሿ "ሞስኮቪች" ከመናኸሪያዋ ደርሳ ስትቆም ነበር ጌትነት ከሄደበት የሃሳብ ጉዞ የተመለሰው፡፡ ወዲያውም ከመኪናዋ ወረደና የመንገድ ቦርሳውን ትከሻው ላይ አንጠልጥሎ አልቤርጎ ፍለጋ ተሰማራ፡፡ ከአንደኛው ቡና ቤት አልጋ ይዞ የመኝታ ክፍሉን በር ከውስጥ በኩል ዘጋና ኪሱ ውስጥ የቀሩትን ሁለት ሲጋራዎች አከታትሎ ካጤሰ በኋላ አልጋው ላይ በጀርባው



ጋደም አለ፡፡

ጌትነት ሸለብ ካደረገው የድካም እንቅልፍ ሲባንን ቀኑ መምሸት ጀምሯል፡፡ ቀና ብሎ የክፍሉን መብራት አበራና አልጋው ላይ ተቀመጠ፡፡ ከዚያም እራት ለመብላት አሰበና ቅድም ለራሱ የገባውን ቃል አስታውሶ ሃሳቡን ቀየረ፡፡ ቡና ቤቱ ውስጥ በአስተናጋጅነት የሚሠሩት ቆንጆ ቆንጆ ኮረዳዎች ለማታው ሥራ ዝግጅት ጀምረዋል፡፡ ግማሾቹ ውስጥ ልብስ ብቻ ለብሰው ወደ መታጠቢያ ቤት ይሄዳሉ፡፡ ሌሎች የሽቶ ሳሙና መዓዛቸውን በአየሩ ውስጥ ያሰራጩታል፡፡ ዝግጅታቸውን የጨረሱት ደግሞ የሌሊት ሙሽሮች መስለው የሆነ ጣዕመ ዜማ እያንጎራጎሩ ግቢው ውስጥ ይጣደፋሉ፡፡ ቡና ቤቱ ውስጥ የተከፈተው ሙዚቃ እየተስረቀረቀ ልብ ውስጥ የብቸኝነትና የወሲብ ፍላጎትን የሚያጭር ይመስላል፡፡

ጌትነት ወደ መኝታ ክፍሉ ተመለሰና አልጋው ላይ ተቀመጠ፡፡ ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ወደ ቡና ቤቱ ለመሄድና ሻይ ጠጥቶ ለመመለስ ከወሰነ በኋላ የመኝታ ቤቱን በር ቆልፎ ወደዚያው አመራ፡፡

የቡና ቤቱ ደማቅ የኤሌክትሪክ ብርሃን ለረጅም ጊዜ በገጠር ጨለማ የኖሩትን አይኖቹን ቢያጥበረብራቸውም ጌትነት አይኖቹን እንደምንም ከብርሃኑ ጋር አለማመደና ሻይ አዘዘ፡፡ ከመሸ በኋላ ሻይ እንደማይሸጥ ሲነገረው ተገርሞ ለስላሳ መጠጥ ጠየቀ፡፡ እሱም የለም፡፡ አይኖቹን ቡና ቤቱ ውስጥ ወደ ተገጠገጡት ጠረጴዛዎች መለሰ፡፡ እውነትም

ሰው ሁሉ የሚጠጣው ቢራና አልኮል ነው፡፡ ለጥቂት ሴኮንዶች ልቡ መጠጥ በማዘዙና በመተው ሃሳቦች መካከል ሲሟገት ቆየና በመጨረሻ በይሉኝታ አንድ ቢራ አዘዘ፡፡ አንድ ቢራ ብቻ እንደሚጠጣ እራሱን በራሱ ካስጠነቀቀ በኋላ የተከፈተውን ጠርሙስ አንስቶ አንድ ጊዜ በረጅሙ ሲስብለት መጠጡ ተጋመሰ፡፡ ሁለተኛ ሲስብለት ጠርሙሱ ባዶ ቀረ፡፡ ለካስ ሳይታወቀው ውሃ ጠምቶት ኖሮ ቅም አላለውም፡፡

ወዲያውም የቅድሙን ውሳኔውን በመሻር ሌላ ቢራ ካዘዘ በኋላ ሌላ አዲስ ሃሳብ ማብጠልጠሉን ቀጠለ፡፡

"አንድ ሁለት ቢራ ብወስድ ምንም አይደል፡፡ ይሄን ያህል ትልቅ ወጪ ሆኖ መታሰብ የለበትም፡፡ የታደለውማ ውስኪ ይጠጣል፡፡ ባይሆን ሂሳቡን ለማካካስ እራት አልበላም፡፡ አዲስ አበባ ከደረስኩ በኋላ ግን ቅድም እንዳልኩት የመጠጥ አይኑን አላይም..."

ጌትነት በባዶ ሆዱ ሁለት ቢራ መጠጣቱ የቀኑ ጉዞ ከፈጠረበት ድካም ጋራ ተዳምሮ እራሱ ላይ ስለወጣበት ከመተው ይልቅ የመደጋገም ፍላጐት ነበር የቀሰቀሰበት፡፡ ከሶስተኛው ቢራ ሂሳቡን ከፍሎ ወጪውን በሃሳቡ እያሰላ ወደ መኝታ ክፍሉ ተመልሶ አልጋው ላይ ጋደም አለ፡፡ ከበፊቱ አሁን የመዝናናት ስሜት ይሰማዋል፡፡ የነገውን ጉዞ ሲያስብ ደስ አለው፡፡

የቡና ቤቱ ኮረዳዎች ሳቅና ሁካታ ከሙዚቃው ጋር ተደባልቆ ከሩቅ ይሰማዋል፡፡ ነገ ወደ አዲስ አበባ የማይሄድ ቢሆን ኖር እሱም ይሄን ጊዜ እንደ



ሴቶቹ ሲስቅና ሲደሰት ያመሽ እንደ ነበር አሰበና ትካዜ ቢጤ ተሰማው፡፡ ወዲያው ደግሞ መንፈሱን ጠንከር አደረገና "ከእነሱ ሕይወት የእኔ ዓላማ ይበልጣል!" ብሎ አሰበ፤ "የእነሱ ሳቅና ደስታ ከአንገት በላይ ነው፡፡ ጊዜያዊ ነው፡፡ የእኔ ዓላማ ሲሳካ ግን ዘላቂ እርካታ አገኝበታለሁ፡፡"

ልብሱን አወላልቆ ለመተኛት ቢያስብም "ተው! ጊዜው ገና ነው፤ ከአሁኑ ተኝተህ እንዴት ይነጋልሃል? ገና ረጅሙ ሌሊት ከፊትህ ይጠብቅሃል!" የሚል ድምፅ ከውስጡ የሰማ ይመስል መቁረጥ አቅቶት አልጋው ላይ በጀርባው እንደ ተጋደመ አሁንም አሁንም በዓይነ ህሊናው ከሚመጣበት ከቡና ቤቱ ትዕይንት ጋር ትግል ገጠመ፡፡ ትንሽ ቆይቶም የሴቶቹ ሳቅና ሁካታ ሲበረታ እንዲሁም ሙዚቃው እየተቀያየረ ሲሟሟቅ ወደ ቡና ቤቱ ተመልሶ ለእንቅልፍ ያህል አንድ ሁለት ቢራ ደግሞ ለመመለስ ወሰነና ጌትነት ፀጉሩን በችኮላ በጣር በጣር አድርጎ መልኩን በትንሿ የኪስ መስተዋት አየት ካደረገ በኋላ የመኝታ ቤቱን በር ቆልፎ ወጣ፡፡

ቡና ቤቱ ውስጥ ገብቶ እንደተ ቀመጠም አንደኛዋ አሻሻጭ ቀልጠፍ በማለትና ጌትነት ካለበት ቦታ በመሄድ ምን እንደሚፈልግ ጠየቀችው፡፡ ያዘዛትን ቢራ ካቀረበችለትም በኋላ ራቅ ብላ በመቆም በሚለግመጡ ዓይናቿ አይን አይኑን ትመለከተው ጀመር፡፡ እሱም ልጅቷ እንደምታየው ስላወቀ በተደጋጋሚ በዓይኑ ጥግ ወደ እሷው ሁለት ሶስት ጊዜ ሲመለከት አይን ለአይን ተጋጩ፡፡ መልኳ፣ አለባበሷና ጠቅላላ ሁኔታዋ ድር

የሚያውቃቸውን የአዲስ አበባ ኮረዳዎች አስታወሱት፡፡

ትንሽ ቆይቶም እየሰረቀ ማየቱን ትቶ ፊት ለፊት ይመለከታት ጀመር፡፡ ለሌላ ሰው መጠጥ ስትቀዳና ቡና ቤቱ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ስትመላለስ የሰውነቷን ቅርፅ አንድ በአንድ አጠናው፡፡ ከዚያም በሃሳቡ ምናልባት እንደ እሱው እንጀራ ፍለጋ ከሩቅ አገር ወይንም ከአዲስ አበባ መጥታ ከነገ ዛሬ እመለሳለሁ ስትል እግ ክፍሏ ሆኖ ወይንም ጊዜው ሳታስበው እያመለጣት ከዚሁ ሃገር የቀረች እድለ ቢስ ልጅ ትሆን ይሆናል በማለት አሰበና አዘነላት፡፡ ልጅቷ ከማንም ጋር አትነጋገርም፡፡ ሌላ ማንንም አትመለከትም፡፡ የታዘዘችውን ከፈጸመች በኋላ ከአንደኛው የቤቱ ማዕዘን አጠገብ ከሚገኘው ወንበር ላይ ተቀምጣ ጌትነትን ታየዋለች፡፡ በድንገትም ልጅቷ ከየት እንደመጣችና እንዴት እንደመጣች የማወቅ ብርቱ ፍላጐት ጌትነትን ተጠናወተው፡፡

ሁለቱን ቢራ እንዴት እንደ ጨረሰው አልታወቀውም፡፡ ለልጅቷ ምልክት ሰጣትና ሌላ ቢራ አዘዘ፡፡ ፈገግ ብላ ያመጣችውን ቢራ ከፈተችለት፡፡ ፈገግታዋ የደግነትና የፍቅር አስተያየት መግለጫ፣ የብቸኝነትና የሕይወት ሰለባ የሆነች ውብ ሴት ፈገግታ መሰሉ ስለ ተሰማው የርህራሄ ስሜት ልቡን እንደ መርፌ ጠቅ አደረገው፡፡

ልጅቷ ቢራውን ብርጭቆው ውስጥ ቀድታለት ልትሄድ ስትል "እ... ስሚ የኔ እህት..." አለና ጌትነት ፈራ ተባ እያለ ክንዷን ያዝ አደረገው፡፡ ልጅቷም ከመቅፅበት ፊቷን ወደ እሱ በማዞር ፈገግ



ብላ ጠየቀችው፡፡

"እኔን ነው የጠራኸኝ?"

"እ... አዎን አንቺን ነው!"

"እሺ ምን ልታዘዝ?"

"ስምሽን ማን ልበል? መቼስ ዕውቀትና ፍጥረት አንድ ቀን ነው!"

"ማክዳ እባላለሁ፡፡ አንተስ?"

"ጌትነት እባላለሁ፡፡ ጌትነት ዘሪሁን!"

"ምን ልታዘዝህ?"

"ምን ትወስጂያለሽ?"

"አንተ የያዝከውን"

"ታዲያ ምን ትጠብቂያለሽ?"

ማክዳ ቢራዋን ልታመጣ ሄደች፡፡ ዘቢብ የመሰለች ጠይም ናት፡፡ የታችኛው ከንፈሯ ትንሽ ስጋ ከበድ ያለው ሆኖ ጣል ስታደርገው የታችኛው ጥርሷ የተሸለቀቀ በቆሎ መስሎ ይታያል፡፡ ሁለመናዋ የወጣትነት ኃይልና ትኩስ የወሲብ ስሜት ይነበብበታል፡፡ የተቀባችው ሽቶ ስሜት ይረብሻል፡፡

ጌትነት ያሰባል፣ "ከሁለት ቢራ በላይ አልጋብዛትም፡፡ እኔ ጋ ሶስት፣ እሷ ጋ ሁለት፡፡ አምስት፡፡ ከዚያ በላይ ቀልድ የለም፡፡ ገብቼ መተኛት ነው!"

ማክዳ ቢራዋን ይዛ ተመለሰችና አጠገቡ ያለውን ወንበር ስባ ከተቀመጠች በኋላ ቀና በማለት በፈገግታ ተመለከተችው፡፡

"ይቅርታ አድርግልኝና ከየት ነው የመጣኸው?"

"ከዚሁ ነው..."

"ከዚሁ አይደለም!"
"እንዴት?"
"አይቼህ አላውቅማ!"
"ስቀልድሽ ነው፡፡ ከጊኒር ዛሬ መግባቴ ነው"
"ጎባ ትቆያለህ?"
"አልቆይም፡፡ ነገ ወደ አዲስ አበባ እሄዳለሁ፡፡"
"መምህር ነህ አይደል?"
"በምን አወቅሽ?"
"ታስታውቃላችሁ!"
"መምህር አትወጂም መሰለኝ!"
"ውይ! ምነው አንተ? መምህር ያልተወደደ ሌላ ማን ይወደዳል? እናንተ ለራሳችሁ የምታሳዝኑ መስኪኖች ናችሁ!"
"ምን ታደርጊዋለሽ..."
"ነገ የት ነው እሄዳለሁ ያልከኝ?"
"አዲስ አበባ!"
"እውነት አዲሳባ ነው የምትሄደው? ለምንድነው የምትሄደው?"
"አይ ምንም አይደል... እንደዚሁ ነው"
"ውይ! አዲስ አበባ እንዴት ናፍቃኛለች መሰለህ!"
"አዲስ አበባ ነበርሽ እንዴ?"
"አዎን ነበርኩ... ነበርኩ ልበል እንጂ..."
"የት አካባቢ ነበርሽ በናትሽ?"
"አርማ ጋራዥ አካባቢ!"
"ከዋናው ፖስታ ቤት ጀርባ?"
"ልክ ነህ!"



"ከማን ጋር ነበር የምትኖሪው?"
"ከወላጆቼ ጋር"
"ለምን አዲስ አበባን ትተሽ መጣሽ ታዲያ?"
"ከቤተሰቦቼ ተጣልቼ"
"ለምን ተጣላሽ?"
"በቃ ምን ልበልህ... ሳላውቀው ተሳስቼ ከፍቅረኛዬ አረገዝኩና ሲታወቅብኝ ጊዜ አፍሬ ናዝሬት አክስቴ ቤት ሄድኩ፡፡ አክስቴ ስትቆጣኝ ደግሞ ሆድ ባሰኝና ጠፍቼ ሻሸመኔ ገባሁ... ከዚያም እዚህ መጣሁ፡፡"
"እርግዝናውስ... ማለቴ... ልጁ?"
"ልጁማ ተወለደ፡፡ ምን ያደርጋል አልተባረከልኝም እንጂ"
"ምስኪን! ፍቅረኛዬ ያልሽውስ?"
"ጥሎኝ አሜሪካ ገባ፡፡"
"አይፅፍልሽም?"
"አይፅፍልኝም፡፡ እናንተ ወንዶች የልባችሁን ካደረሳችሁ በኋላ መቼ ዞር ብላችሁ ታያላችሁ!"
"ታዲያ አዲስ አበባ አይሻልሽም ነበር"
"የዘመዶቼን ዓይን ማየት አልፈልግም!"
"ምስኪን..."
"ምን ታደርገዋለህ... ወድጀ መሰለህ የምስቀው? የእኔ ነገር እንደማሽላ ነው፡፡ እያረሩ መሳቅ!"
"አይዞሽ ከቢራው ድገሚ፡፡ በጣም ታሳዝኚያለሽ!"
"ይቅርብኝ አልጠጣም፡፡ እራሴን ያመኛል!"

"አንድ ድገሚ ምንም አይልሽም!"

"በል እንግዲህ አመሰግናለሁ... መልካም ጉዞ ይሁንልህ"

"ምናልባት አዲስ አበባ የምትልኪው መልእክት ካለሽ ላደርስልሽ እችላለሁ፡፡"

"ለማን እልካለሁ ብለህ ነው... እንዳልኩህ ከዘመዶቼ ተቆራርጬ ቀርቻለሁ፡፡"

"ጓደኛ የለሽም?"

"ከፍቅረኛዬ ሌላ ጓደኛ አልነበረኝም፡፡ ምን ያደርጋል እሱም ከዳኝ፡፡"

"በይ እንግዲህ አልጠጣም ካልሽ እኔም ልሂድ!"

"ትንሽ አትጫወትም ነበር? ገና ሶስት ሰዓት'ኮ ነው!"

"መጫወት እንኳን እጫወት ነበር... ነገ ደግሞ የአዲስ አበባ መንገድ ይጠብቀኛል፡፡"

"ብቻህን ነህ አይደል?"

"ነገ ማለትሽ ነው?"

"ኧረ ዛሬ... ብቻህን ነው ወይ የምታድረው ማለቴ ነው!"

"አዎን ብቻዬን ነኝ፡፡"

"እንግዲያውስ ፈቃድህ ከሆነ ብቅ ብዬ አስናበትሃለሁ፡፡ አስራ ሶስት ቁጥር ነው አልጋ የያዝከው አይደል?"

"የመኝታዬን ቁጥር እንዴት አወቅሽው ግን?"

"ብቸኛ የብቸኛን አድራሻ ያጣዋል ብለህ ነው!"

"ከመጣሽ ጥሩ ነው" አለ ጌትነት ባልተረጋገጠ ድምፅ፣ "እጠብቅሻለሁ፡፡" ከዚያም ስለ ማክዳ



እያሰላሰለ ወደ መኝታ ክፍሉ ተመለሰና አልጋው ላይ በጀርባው ከተጋደመ በኋላ አይኖቹን ከቤቱ ኮርኒስ ላይ ተክሎ ያሰላስል ገባ፡፡

"ምን ዓይነት የዋህ ልጅ ነች? ምስኪን..." ይላል ጌትነት በሃሳቡ፣ "ፍቅረኛዋ የከዳት ከርታታ፡፡ ይቺን የመሰለች ቆንጆ ልጅ ተወልዳ ካደገችበት ከተማ ተሰዳ በወጣትነቷ ስንት ስቃይ ታያለች... በእሷ አይን እኔ ሕይወትን ሳማርር የኖርኩት በከንቱ ነው ማለት ነው፡፡ ደግሞም እኔ ከነገ ጀምሮ አዲስ አበባ እገባለሁ፡፡ እሷን ግን የሕይወት መርከብ ካላሰበችውና ካልፈለገችው ወደብ እንደ እቃ ሲያራግፋት ይኖራል፡፡ አሳዛኝ ፍጡር..."

ፈገግታዋ ደግሞ ደጋግሞ በሃሳቡ ይታየዋል፡፡ ፈገግታዋ አንድ የተደበቀ መልእክት ያዘለ ይመስለዋል፡፡ እናም በፈገግታዋ ውስጥ የተደበቀ የመሰለውንና ለጊዜው ሊያውቀው ያልቻለውን ምስጢር ለማወቅ በተቀሰቀሰበት ብርቱ ፍላጐት ጭምር ቃል እንደገባው ማክዳን ሊጠብቃት ወሰነ፡፡

ትንሽ ቆይታም ልጅቷ ገርበብ ያለውን የመኝታ ክፍሉን በር አንኳኩታ ጥልቅ አለችና ጌትነት ፊት በመቆም ቁልቁል እየተመለከተችው ያንን ልብ የሚያቀልጠውን ፈገግታዋን ካሳየችው በኋላ ከጎኑ ተቀመጠች፡፡ በቅድሙ ልብስ ፋንታ የሰውነቷን ቅርጽ ወለል አድርጎ የሚያሳየውን የሌሊት ልብስ ለብሳ ነጠላ ጫማዋን አድርጋለች፡፡ ከታጠበችው ወጣት ሰውነቷና ከልብሷ የሚመነጨው መዓዛ ልብ ያዋልላል፡፡

"ቆየሁ እንዴ? ይቅርታ! ሂሳብ ሳስረክብና

ልብስ ስቀይር ነው!"

"አይ... አልቆየሽም!"

"የነገ መንገደኛ! አይዞህ አዲስ አበባ በደህና ትገባለህ፡፡ በጠዋት በራሪው ወይንስ በአዳባ አዳሪው ነው የምትሄደው?"

"በጠዋት በራሪው ነው! በአንደኛው!"

"ታዲያ አዲስ አበባን ሰላም በልልኝ እሺ?"

"የቱን የቱን ቦታ ሰላም ልበልልሽ?"

"ከተማዋን በጠቅላላ!" አለችና ማከዳ ድንገት አንገቱን አቅፋ አልጋው ላይ በጀርባው ጣለችው፡፡ "አይዞህ ተጫወት! ይሄው ነው መንገድ ሲገቡ"፣ "አይዞህ ተጫወት! ይሄው ነው መንገድ ሲገቡ" ጭንቅ ጭንቅ ይላል፡፡ ያውም ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ... ጫማህን አውልቀውና አልጋው ላይ ጋደም በል፡፡ ስንት ጊዜ ሆነህ ግን አዲስ አበባን ካየሃት?"

"ዘጠኝ ዓመት፡፡ ሳላስበው ወጥቼ እመለሳለሁ ስል ቀልጩ ቀረሁ!"

"በጣም ይገርማል፡፡ የብዙዎቻችን እድል ተመሳሳይ ነው፡፡ አንተስ እንግዲህ ልትገላገለው ነው፡፡ እኛ ነን እንጂ እንደ ፈረደብን የኑሮን አተላ ስንጋት የምንኖረው፡፡ ብዙዎቻችን የተመኘነውን መሆን አለመቻላችን ያሳዝናል፡፡"

"አይዞሽ! አንድ ቀን አንቺም ወደ አዲስ አበባ ትመለሺ ይሆናል፡፡ ዋናው ነገር ተስፋ አለመቁረጥ ነው፡፡ በዚህ ዓለም ተስፋ ከቆረጥሽ በቁምሽ ሞትሽ ማለት ነው፡፡ እንዳልኩሽ እኔ ዘጠኝ ዓመት ነው የታገስኩት፡፡ ዘንድሮ ግን ወደ አዲስ አበባ ባልመለስ ኖሮ ምን ልበልሽ መቀወሴ የማይቀር ነበር፡፡ ትዕግስቴ ተንጠፍጥፋ ልታልቅ አንዲት



ጠብታ ብቻ ነበረች የቀረችው፡፡ ትዕግሥት ሲያልቅ ደግሞ አደገኛ ነው!"

"እውነትህን ነው፤ ያለ ተስፋ መኖር አይቻልም፡፡"

"ምናልባት ደብዳቤ ብልክልሽ በየትኛው አድራሻ ልጻፍልሽ?"

"በጎባ ፖስታ ቤት በኩል ቀበሌ 01 ብለህ ብትልክልኝ ይደርሰኛል፡፡"

"የወጪ ልበልሻ ታዲያ ማከዳ"

"ይበቃኛል ጠጣሁ አይደል?"

"መጠጣት አለብን በቃ! ለእኔም ለአንቺም ወደፊት መልካም ዕድል እንዲገጥመን መመኘት አለብን፡፡ ይህችን ምሽት ምንም ጊዜ ቢሆን አልረሳትም!"

"እኔንስ ትረሳኛለህ?"

"ያላንቺማ ምሽቱን አላስታውስም!"

ሲጠጡ፣ ሲዳሩና ብዙ ነገር ሲጫወቱ አምሽተው እኩለ ሌሊት ሲያልፍ እንሶላው ውስጥ ገብተው ጠፉ፡፡ ከዚያም ከወሲባዊ እርካታ በኋላ የሚመጣው ሰመመን እያባበለ እያባበለ ወስዶ ድብን ካለ የእንቅልፍ ዓለም ጨመራቸው፡፡

እንደ ማንኛውም የደስታ ጊዜ ሌሊቱ አጭር ነበር፡፡ ጌትነት ከእንቅልፉ ሲባንን ወፎች ይንጫጫሉ፡፡ ደንግጦ ተነሳና ልብሱን መለባበስ ጀመረ፡፡ ማከዳን ከጎኑ ሲያጣት በመብረቅ የተመታ ያህል ክው ብሎ ቀረ፡፡ ከማታ ወጪው ምን ያህል እንደ ተረፈው ለማወቅ እጁን ወደ ኪሱ ዘው አደረገ፡፡ ምንም ገንዘብ የለም፡፡ ጣቶቹ

እየተንቀጠቀጠ ኪሶቹን ተራ በተራ ፈተሻቸው። ምንም! ጫማውንና ካልሲውን ሳይቀር በረበረ። የአልጋውን ፍራሽ ገልብጦ፣ አንሶላውንና ብርድ ልብሱን እያራገፈ መረመረ። ጠብ ያለ ነገር አልነበረም። በጉልበቱ መሬት ላይ ተንበረከከና የአልጋውን ስር ፈተሸ። የወረቀት ቁራጭ እንኳን በአካባቢው አይታይም።

ድንገት ልቡን የነሳው ይመስል ከደጋኑ እንዳመለጠ ቀስት ተስፈንጥሮ ወደ ውጪ ወጣና ፈገግ ማለት በጀመረው ንጋት ውስጥ የማክዳን ስም ደግሞ ደጋግሞ ተጣራ። የሚመልስለት የገደል ማሚቶ እንኳን አልነበረም።

ጌትነት እንደ እብድ እየጮኸ ወደ ቡና ቤቱ ግቢ በር ሄደ። ዘበኛው ጥቁር ብርድ ልብስ ለብሶ ቆሞ ይመለከተዋል። የግቢው በር ገርበብ ብሏል።

“ማክዳስ?! ማክዳ የታለች?!” ጌትነት እንደ ብራቅ ጮኸ።

“ሻንጣዋን ይዛ አሁን ወጣች” አለ ዘበኛው በብርድ ልብስ አፉን እንደ ሸፈነ።

“ምን?! ሻንጣዋን ይዛ?”

“አዎን፣ መንገድ ሳትገባ አትቀርም”

ጌትነት መናገር አልቻለም። እየሮጠ ወደ መኝታ ቤቱ ተመለሰና የመንገድ ቦርሳውን አንጠልጥሎ እንቅፋት ግራና ቀኝ እያላጋው የግቢውን በር በርግዶ ከወጣ በኋላ ሩጫውን ቀጠለ። ወዲያውም ወደ አዲስ አበባ የሚበረው አውቶቡስ ጥሩምባውን ደጋግሞ አሰማና ሞተሩን አስነስቶ ጉዞውን ጀመረ። ሁለት መቶ ሜትር ያህል ራቅ



ብሎ ጌትነት ወደ መናኸሪያው ለመድረስ በመንደሩ ውስጥ ይሹለከለካል። ድንጋጤ፣ ድካም፣ ብስጭት... በኮረኮንቹ መንገድ ላይ ይፍገመገማል።

ጌትነት ተስፋ አልቆረጠም። የመንገድ ቦርሳውን ትከሻው ላይ እንዳንጠለጠለ የአውቶቡሱ አራት ጎማዎች በእርጥቡ ጥርጊያ መንገድ ላይ አትመውበት ባለፉት ሁለት መስመሮች መካከል ትንፋሹ እስኪቆረጥ ድረስ መኪናውን ተከትሎ ሮጠ። አውቶቡሱ እየራቀ እየራቀ ሄደና በመጨረሻም ከሩቅ የሚሰማውን ጥሩምባውንና ከጎማዎቹ ስር የሚነሳውን አቧራ ብቻ ለጌትነት አይንና ጆሮ ትቶ ከአካባቢው ተሰወረ።

ጌትነት ሩጫውን መቀጠል አልቻለም። ቀዝቃዛ ላብ በግንባሩና በጆሮ ግንዱ ይወርዳል። ልቡ ደረቱ ስር እንደ ላስቲክ ኳስ እየነጠረች በአፉ ሾልካ ልትወጣ ምንም ያህል አልቀራት። እግሮቹ መራመድ ተሳናቸውና ተዝለፍልፎ ከመሬት ላይ ወደቀ። እንደ እሳት የሚፋጅ የንዴት፣ የቁጭትና የተስፋ መቁረጥ እንባ አይኖቹ ላይ ድንገት ግልብጥ አለበትና ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ከዚያም እንደ ምንም ከወደቀበት ተነስቶ የእውር የድንብሩን እየተንገዳገደና ቦርሳውን እየጐተተ ወደ ሮቤ የሚወስደውን መንገድ ተከትሎ መሄድ ጀመረ። ወዴት እንደሚሄድ ግን አያውቀውም።

ሕይወት-የህልም እንጀራ–የህልም ጉዞ...

አሁን ግን ሁሉም ነገር ቅዠት ሆኖበታል።

# አስቻለው ዝምታ

ስሜ አስቻለው ተሻለ ነው፡፡ እናቴ ነፍሷን ይማራትና ድሮ እንደ ነገረችኝ ከሆነ ገና አራስ ቤት ከነበርኩበት ጊዜ ጀምሮ ሁሉን ነገር በዝምታ ስለምቀበል ነበር አስቻለው ያለችኝ፡፡ ቢርበኝም፣ ቢጠማኝም፣ ብቻዬንም ብሆን አላለቅስም ነበር አሉ፡፡ አንድ ቀን ባዶ ቤት ጥላኝ ውሃ ልትቀዳ ከቤት ወጥታ ትሄዳለች፡፡ ይሄንንም ታሪክ እሷው ናት የነገረችኝ፡፡ አልጋ ላይ ነበር ያስተኛችኝ፡፡ ስትመለስ ከአልጋው ላይ ተገልብጬ ወርጄ መሬት ላይ ወድቄ ታገኘኛለች፡፡ ሆኖም አላለቅስም ነበር አለች፡፡ ከአልጋ ላይ ወድቆ የማያለቅስ ሕፃን! ይታያችሁ እስኪ... ማታ ለአባቴ ትነግረዋለች፡፡ እሱም በነገሩ ተገርሞ "እግዚአብሔር ቻይ አድርጎ ነው የፈጠረው!" ይላታል፡፡ አስቻለው ብላ የሰየመችኝ በዚያው ጸንቶ ይቀራል፡፡ ትልቅ ከሆንኩ በኋላ ግን ከግማሽ ደርዘን በላይ ስሞች ወይንም የቅጽል ስሞች አውጥተውልኛል፡፡ መሬት፣ ድንጋይ፣ ዝጋታም፣ ደባሪው፣ ጋግርታም፣ ዝምታ ይሉኛል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ "አስቻለው ዝምታ" በተባለው ስምና የቅጽል ስም ነው የምታወቀው፡፡ አሁንማ እንዲያውም



አስቻለው የተባለው ስሜ እየተረሳ "ዝምታ" ነው የሚሉኝ፡፡

እኔ በበኩሌ በነዚህ ሁሉ የቅጽል ስሞች ተስማምቼ አላውቅም፡፡ መሬትም፣ ድንጋይም፣ ዝጋታምም፣ ደባሪም፣ ጋግርታምና ዝምተኛም እንዳልሆንኩ አውቀዋለሁ፡፡ እነሱ ግን የፈለጉትን ስም የመስጠት መብት አላቸው፡፡ ውሃውን አፈር፣ አፈሩን ደግሞ ውሃ ብለው ለመጥራት ቢስማሙ ስሙን ስለለወጡት ምን የሚለወጥ ነገር አለ? እኔ ግን ዝጋታም አይደለሁም፡፡ አፌ ቢዘጋ ልቤ አልተዘጋም፡፡ አፌ አይናገር እንጂ በልቤ ብዙ እላለሁ፡፡ ዝምታዬ እራሱ ከንግግር የበለጠ ቋንቋ መሆኑን የተረዱልኝ አይመስለኝም፡፡ እንደማይገባቸው ስለማውቅ ለምን አይገባችሁም ብዬ አልከራከራቸውም፡፡ ይሄማ ፀሐይ ለምን የጨረቃን ቦታ አልወሰደችም ብሉ አጉል ሙግት ውስጥ ሜግባት ይሆንብኛል፡፡

ለምን የቅጽል ስም አወጣችሁልኝ ብዬም ከሰው አልጣላም፡፡ የፈለጋቸውን ስም ይስጡኝ፡፡ እኔ እንደሆንኩ· የሚሉትን ሁሉ እንዳልሆንኩ አውቀዋለሁ፡፡ ቢሆንስ ደግሞ ለምሳሌ መሬት የሚሉት የቅጽል ስሜ ምን ክፋት አለው? ከመሬት የበለጠ ምን ጥሩ ነገር ይገኛል? ሁላችንንስ መሬት አይደለች ችላ የምታኖረን? ድንጋይም ቢሆን ጥሩ ስም ነው፡፡ የቅድል ስም የሚያወጡልኝ ሰዎች የድንጋይ ያህል ቁምነገር እንደማይሠሩ አውቃለሁ፡፡ ደባሪው ቢሉኝስ ምንቸገረኝ? አምላክ በአምሳሉ እንደ ሠራኝ አውቃለሁ፡፡ ደግሞስ የገዛ መልኬን

እኔው እራሴ እንደ ጭቃ ጠፍጥፌ አልሠራው... ለመልኬ ደባሪነት ተጠያቂ ሊያደርጉኝ አይችሉም፡፡ ሆኖም አልናገራቸውም፡፡ "ውሃ ቢወቅጡት" ምን ይላል? ነው የሚባለው? "እምቦጭ!"

ታዲያ ዝም ስለምል መቼስ የማያደርጉልኝ ነገር አልነበረም፡፡ ከላይ እስኪ ታች፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ እኔን መሳቂያ ለማድረግ የማይሞክር ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡ ከላይ ልጀምርላችሁ እስኪ፡፡ በተላላኪነት ከምሰራበት መሥሪያ ቤት አንድ ቀን አለቃችን ቢሮ አድርስ ተብዬ የተሰጠኝን ወረቀት ይዤ ስገባ እንዲህ አሉኝ፣ "ስማ ዝምታ! ጫማህ ስለሚሸት ሁለተኛ እኔ ቢሮ እንዳትገባ፡፡ የምታመጣውን ወረቀት ከውጭ ሆነህ ለፀሐፊዬ አቀብላት-እሷ ታመጣልኛለች፡፡ መልሱን ውጭ ሆነህ ጠብቅ!" እሺ ብዬ፣ እጅ ነስቼ ወጣሁ፡፡ ሙቀት ሲሆን ጫማዬ እንደሚሸት አውቃለሁ፡፡ ሆኖም ማታ ማታ ከመተኛቴ በፊት እግሬንና የእግር ሹራቤን ሳላጥብ ቀርቼ አይደለም፡፡ መጀመሪያ ነገር ከቤቱ ወደ ሥራ የምመላለሰው በእግሬ ነው፡፡ መቼስ በሰባ ብር የወር ደምወዝ በታክሲ አልመላለስ! ወይንም አራት ጥንድ ጫማዎችን አልገዛ! በዚያ ላይ መሥሪያ ቤት ውስጥ እረፍት የለኝም፡፡ ከጠዋት እስከ ማታ ፎቁን ስወጣና ስወርድ፣ ከአንዱ ቢሮ ወደ ሌላው ስሯሯጥ ነው የምውለው፡፡ ማቼም የማይልከኝ ሰው አልነበረም፡፡ "ዝምታ እዚህ ሂድ!" - እሺ፣ "ዝምታ እዚያ ሂድ!" - እሺ!፣ "ዝምታ ይሄንን አምጣ!"-እሺ!፣ "ዝምታ ያንን አምጣ!" እሺ ነው የምለው፡፡ የአለቃችን ፀሐፊ እንኳን ከመሥሪያ ቤት ውጭ



አንዴ "ለፊቴ ቅባት ግዛልኝ፣" አንዴ ደግሞ "ውጭ የሚጠብቀኝ መኪና መጥቶ እንደሆነ ሂድና ተመልከት!" ትለኛለች፡፡ ሌላው ቀርቶ በየወሩ ከፋርማሲ ጥጥ ግዛ እያለች ዘወትር ስትልከኝ ግድ የላትም፡፡ ይሄ ሁሉ ታዲያ ዝም ስለምልና እሺ ስለምል አይደል? እንደ ሞኝ እንደሚያዩኝ አውቃለሁ፡፡ እኔ ግን ሞኝ አይደለሁም፡፡ ለሰው መታዘዝ ምን ሞኝነት ነው? እነሱ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስና መስራት የማይወዱት ሰነፎቹ ናቸው የተሞኙት ወይንስ እኔ ስሠራ የምውለው ሰውዬ ነኝ የተበለጥኩት? አሁንም ቢሆን አልናገርም፡፡ ፍርዱን ለህሊናቸው እተወዋለሁ፡፡

ወደ ተነሳሁበት ታሪክ ልመለስና፣ አለቃችን "ጫማው ይሸታል" ያሉኝ ነገር በየት አድርጎ ከሰው ጆሮ እንደ ገባ አላውቅም፣ ሰው ሁሉ መሳቂያ መሳለቂያ አደረገኝ፡፡ ምን ብለው እንደ መከሩኝ ታውቃላችሁ? ግማሹ አለቃችን ቢሮ ሳትደርስ ጫማህን በሩ ላይ አውልቅና ባዶ እግርህን ግባ ይለኛል፤ እስኪ ይታያችሁ የአለቃችን ቢሮ ቤተ መቅደስ አይደለ ባዶ እግሬን በዚያ በቀዝቃዛ ሲሚንቶ ላይ የምሄደው! ለነፍሴ ወይንስ ለሥጋዬ እንዲሆነኝ ብዬ ነው? ደግሞስ ባዶ እግሬን ስገባ አሳቸው ቢሆኑ ምን ይሉኛል? አበደ ብለው የባሰ ከሥራ ሊያባርሩኝ ይችላሉ፡፡ ድሮም እንደማይወዱኝ አውቀዋለሁ፡፡ በቡሃ ላይ ቆረቆር ይሏችኋል እንደዚህ ነው፡፡ ግማሾቹ ደግሞ እንደዚህ ይሉኛል፤ "ዝምታ ለምን ነጠላ ጫማ አታደርግም?" ይታያችሁ እስኪ እኔን የሚያክል የአርባ ሁለት አመት ሰውዬ መንግስት መሥሪያ ቤት ውስጥ

በነጠላ ጫማ ወለሉን እየጠፈጠፍኩ ወጧ እንዳማረላት ባልቴት ወዲያና ወዲህ ስል! እሺ ብዬ ነጠላ ጫማ ብገዛ እኮ መልሰው ሊስቁብኝ ነው! የነጠላ ጫማዬን ድምጽ ከሩቅ እየሰሙ "ይሄውላችሁ ዝምታ መጣ!" "ዝምታ ወደዚያ ሄደ!" እያሉ ሲሳለቁብኝ ሊውሉ እኮ ነው፡፡ መቼም እንደ ሰው ሳይሆን እንደ አሻንጉሊት አይደለም የሚየዩኝ! የአርባ ሁለት ዓመት አሻንጉሊት አግኝተዋል! አሁንስ ቢሆን መሳለቂያ መሆኔ መቼ ቀረ፣ እንዲያውም ዝም ብዬ እለፋለሁ እንጂ...

ደምወዝ ስቀበል ጥርሴን ነክስኩና አዲስ ጫማና ካልሲ ገዛሁ፡፡ ታዲያ አዲሱን ጫማዬን ያደረግሁ እለት በልበ ሙሉነት የተለመደውን ወረቀት ይዤ አለቃዬ ቢሮ ስገባ መጀመሪያ ጫማዬን ተመለከቱና ሆዳቸውን እስኪያማቸውና ዓይኖቻቸው እስኪያለቅሱ ድረስ ሳቁብኝ፡፡ እኔም ደንግጬ፣ "ምን አጠፋሁ?" ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡ ሳቃቸውን እንደ ምንም አቋረጡና "ካፖርቱ የሚል ርእስ ያለውን ጎጎል የሚባለው የሩሲያ ደራሲ የጻፈውን ታሪክ አንብበሃል?" ብለው ጠየቁኝ፡፡ ደንገጥኩና እንዳላነበብኩ ነገርኳቸው፡፡ በተባለው ታሪክ ውስጥ አካከዩቪች የተባለውን ገጸ ባሕርይ እንደምመስል ነገሩኝ፡፡ . ከዚያም ታሪኩን ፈልጌ እንዳነበውና መሰሌን ሰው እንዳውቀው አዘዙኝ፡፡ ለምን ከልብ ወለድ ታሪክ ጋር እንዳመሳሰሉኝ አልገባኝም ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ምን ጊዜ አለኝና ነው ልብ ወለድ መጽሐፍ የማነበው? እዩዩ ሲዳላ አይደል? ሆኖም መቼም የአለቃ ትዕዛዝ ስለሆነ የተባለውን ታሪክ ፈልጌ ማንበብ ቃል ገባሁና ከቢሮ ወጣሁ፡፡ ገና የታዘዝኩትን ታሪክ አግኝቼ ሳላነበው የ



"ካፖርቱን" ጉድ ሰማሁት!

ለካስ በተባለው ታሪክ ውስጥ አካኪዩቪች የሚባል አንድ ሰውዬ አዲስ ካፖርት ገዝቶ ስራ የሄደ እለት የባልደረቦቹ መሳለቂያ ሆኖ ነበር፡፡ ጓደኞቹ ናቸው የሚነግሩኝ፡፡ እስኪ ይታያችሁ... በሌላው አገር ድሮ የተፈጸመው ታሪክ ከእኔ ጋር ምን የሚያገናኘው ነገር አለ? ቢሆንም ምንም አልተናገርኩ፡፡ ለትንሽ ቀን "አካኪዩቪች" እያሉ ሲጠሩኝ ከረሙና ወረቱ ሲያልፍላቸው እርግፍ አድርገው ተውት፡፡ ታዲያ ዝም ማለቴ ምን አጎዳ ትሉኛላችሁ?

ጸዳለ የምትባለዋ አዲስ ተላላኪ ተቀጥራ ከመጣች ከጥቂት ቀናት በኋላ እንደዚህ አሉኝ፣ "ፀዳለ እወደዋለሁ ቢያነጋግረኝ ምናለበት? ትላለች ሂድና አነጋግራት ዝምታ!" ይታያችሁ እስኪ ሴት ቤት መሄድ በጀመርኩበት ዘመን ብወልድ ኖሮ እኮ ፀዳለ የተባለችውን ልጅ የምታህል አደርስ ነበር፡፡ ብለው ብለው ልጄ ከምትሆን ኮረዳ ጋር ለያፋቅሩኝ ይወተውቱኝ ገቡ፡፡ እኔ ግን እንኳን ፀዳለን ልከጅል ይቅርና አንድ ሁለት ብርሌ ጠጅ ጠጥቼ ተረት ሰፈር ወዳለው ቤቴ ስጓዝ ከመንገዱ ግራና ቀኝ የተኮለኮሉትን ሴተኛ አዳሪዎች እንኳን ዞር ብዬ አይቻቸው አላውቅም፡፡ በሰባ ብር ደሞወዝ እንኳን ሴት ላሽባብበት ጠግቤ የማልበላበት ቀን ሞልቷል፡፡ "ትናንት ጫማው ይሸታል" እያሉ ሲሳለቁብኝ ከረሙና ዛሬ ደግሞ ሴት አጩልኝ፡፡ ዝም አልኳቸው፡፡ ታዲያ አርፈው ሊቀመጡ ነው... ፀዳለ ከተባለችው ልጅ ዘንድ ይሄዱና ደግሞ "እወዳታለሁና አስተዋውቁኝ ብሏል" ይሏታል፡፡

በኋላ ነገሩ ካለፈ ነው የሚነግሩኝ፡፡ ፀዳለ ሃይለኛ ቢጤ ነበረችና አንድ ቀን እንዲህ አለችኝ፣ “ለመሆኑ በምን ብትገምተኝ ነው እንደዚህ የደፈርከኝ? እንዳንተ ሁለት ፀጉር ያወጣች ሴት ሞልታልሃለች! እኩያህን አትፈልግም? ቢያንስ ቢያንስ አንተ አባቴ ትሆናለህ!” ብላ ከፍ ዝቅ አድርጋ ተናገረችኝ፡፡ ምንም አላልኳትም፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የነዚያ የተንኮለኞች ሥራ መሆኑን እራሷ ስትደርስበት መልሳ ይቅርታ ጠየቀችኝ፡፡ ታዲያ ዝም ማለቴ ምን አከፋ? ደግሞስ እኔ አሻፈረኝ አልኳቸው እንጂ እነሱ ቁልቁል ወርደው ሴትና ወንድ አገናኝ ሲሆኑ ለመሆኑ እራሳቸውን ማስከበራቸው ነው ማዋረዳቸው? የእነሱ ውሽከታ በለጠ ወይንስ የእኔ ዝምታ? አሁንም መልሱን ለእነሱው እተዋለሁ፡፡

ምን ያደርጋል፣ ከዚያም በኋላ ቢሆን አላረፉም፡፡

“ዝምታ መቼ ነው ልብስህን የምትለውጠው?” ይሉኛል፡፡ እስኪ ይታያችሁ፣ አንዱ ለሚለብሰው ልብስ ሌላው ምን አስጨነቀው?

“ዝምታ በወርቅ ሲለወጥ ነው!” ይላል ሌላው፡፡

“ያልተናገረ ምላሱ ይቆረጣል!” አንዱ ይቀበላል፡፡ እነሱ ለፍልፈው ምን ሲፈይዱ ነው?

“በዝምታ ነው የሚጀመረው!” ሌላው ይመልስለታል፡፡

“ምላሱ ሲቆረጥስ ዝም አይልም፣ ይናገራል!” ሦስተኛው ሰው ያክልበታል፡፡

“ዝምታ ደምወዝህን ምን ታደርገዋለህ?” አንዱ በሌላው ደመወዝ ምን አገባው? ይችም



ደምወዝ ሆና ጠያቂ ተነሳባት!...

“ለውሽማው ይሰጣታል!” አራተኛው ሰው ይመልስለታል፡፡

“ዝምታ ለምን ሚስት አታገባም?” ባገባ ባላገባ ምን ቸገራቸው?

አንድ ሰሞን መሥሪያ ቤታችን ውስጥ አንድ ነገር ተፈጸመ፡፡ አለቃችን ጠዋት ሥራ ሲገቡ ጠረጴዛቸው ላይ እንዲህ የሚል ጽሑፍ የተጻፈበት ወረቀት ያገኛሉ፤ “በአድልዎ፣ በዝምድና፣ በሃገር ልጅነት፣ በጉቦና በአማላጅ ያለ ችሎታቸው ለሠራተኞች ዕድገት መስጠትና ያላአግባብ ደሞዝ መጨመር በአገርና በህብረተሰቡ ላይ ጭምር ታላቅ በደል መፈጸም ነው!” አለቃችን ወረቀቱን ሲያነቡ በንዴት ይጦፋሉ፡፡ ወዲያውም ወረቀቱን ማን እንደ ጻፈው ለማወቅ አውጫጭኝ በምስጢር ይጀመራል፡፡ እነዚያው የሚቀልዱብኝ ሰዎች አሁን ደግሞ ምን ይላሉ መሰላችሁ፡፡ “ምናልባት ዝምታ መናገር ስለማይወድ የሚሰማውን ለመግለጽ ብሎ ያደረገው ይሆናል” ብለው ማስወራት ጀመሩ፡፡ እኔ ግን የተጻፈው ሃሳብ ትክክለኛ መሆኑን ባውቅም እኔ ስላልጻፍኩት ነገሩን ሰምቼ ዝም አልኩ፡፡ እየዋለ እያደረ ነገሩ በእኔ ላይ ከረረ፡፡ በመጨረሻም “እሱ መሆን አለበት የጻፈው!” ብለው በጭፍን ወሰኑብኝ፡፡

አለቃችን ቢሯቸው ድረስ አስጠሩኝና ለብቻዬ አነጋገሩኝ፡፡ የዚህን ጊዜ ግን ጫማዬን አይተው ለመሳቅ ጊዜ አልነበራቸውም፡፡ እኔ በሰው ማላገጥ አልወድም እንጂ በንዴት የተኮማተረውና ድሮም ቢሆን ቁንጋ ቢጤ የነበረው የመልካቸው

አልመልስላቸውም፡፡ በመጨረሻም አንድ ቀን አንዷን ሴትዮ እቤቴ ድረስ ይዘው መጥተው፣ “አስቻለው... በሞቱት እናትህ ብለህ ይህች ሴትዮ በሥራ ምክንያት ከክፍለ አገር ተቀይራ መጥታ ማረፊያ ቤት ስላጣች እየተሰቃየች ናትና ደባል አስገባት፡፡ የጠየቅሃትን ኪራይ ትከፍልሃለች፡፡ ፀባይዋ ቆንጆ ነው ታየዋለህ፡፡ ለአንተም ቢሆን ከብቸኝነቱ ይልቅ ከሰው ጋር መኖሩ ይሻልሃል!” አሉኝ፡፡ በጣም የምወዳትን የሞተችውን እናቴን ስም ጠርተው ስለለመኑኝ ብቻ እሺ አልኳቸው፡፡ ያንኑ እለት ማታ ሴትዮዋ አልጋዋንና ጥቂት እቃዎቿን ይዛ እቤቴ በደባልነት ገባች፡፡ አንድ ሳምንት፣ ሁለት ሳምንት፣ ወር፣ ሁለት ወር አለፈ... ሴትየዋ ሥራ የላትም፡፡ ፀባይዋም ቢሆን ዝም ብዬ ስመለከተው እነሱ እንዳሉት ሳይሆን የሚገርም አይነት ነበር፡፡

ትዝ ይለኛል፣ ክረምት ገብቶ ነበር፡፡ እንደ ወትሮው ሁሉ እኔም በአንደኛው ክፍል ውስጥ ተኝቼአለሁ፡፡ ደባሌ ከሌላው ክፍል ተኝታለች፡፡ ሌሊት ነው፡፡ ኃይለኛ ዝናብ ይዘንባል፡፡ ነጎድጓዱ ደግሞ ቤቱን ሊያፈርሰው የደረሰ ይመስለኛል፡፡ ከእንቅልፌ ነቅቼ ዝናቡን ሳዳምጥ የምተኛበት ክፍል በር በኃይል ይንኳኳል፡፡ ደንግጬ ተነሳሁና በውስጥ ሱሪዬ ብቻ ከአልጋዬ ወርጄ ማን እንደሚያንኳኳ ጠየቅሁ፡፡ . ደባሌ ነበረች የምታንኳኳው፡፡ በሩን ከፈትኩና ለምን እንዳንኳኳች ጠየቅኋት፡፡ “መብረቅ ስለምፈራ ብቻዬን መቆየት አልቻልኩም፡፡ ጨለማው ውስጥ ደግሞ ሰው የሚመስል ነገር ቆሞ አየሁት፡፡ እርግጠኛ ነኝ ሰይጣን ከመብረቅ ለመደበቅ እቤት ውስጥ ገብቷል!” አለች፡፡ በዚህን ጊዜ ኃይለኛ



ነጎድጓድ ተሰማ፡፡ ደባሌም “በስመ አብ ወልድ ወመንፈስቅዱስ!” ብላ በጨለማ ውስጥ ስትዘል አጠገቤ ስለነበረች ተጋጨን፡፡

እጄን ዘረጋሁና ደባሌን በጨለማው ውስጥ ያዝኳት፡፡ እንዳትወድቅ ብዬ ነበር የያዝኳት፡፡ እሷ ግን አንድ ጊዜ በኃይል ጮኸችና፣ “እውነት አንተ አስቻለው ነህ ወይንስ ቅድም ጨለማ ውስጥ ያየሁት ሰይጣን?” ብላ ጠየቀችኝ፡፡ እውነት መስሎኝ እንዳትፈራ ብዬ እጅዋን ያዝኩና ሰይጣኑ አለመሆኔን አረጋገጥኩላት፡፡ ከዚያም እንደ ያዝኳት አልጋዬ አጠገብ አደረስኳትና፣ “አይዞሽ ዝም ብለሽ አልጋ ላይ ተኚ፣ እኔ ወንበሩ ላይ እቀመጣለሁ፡፡” አልኳት፡፡ ወንበሩ ከአልጋው አጠገብ ነው፡፡ ከአጠገቧ ከሄድኩ የልብ ድካም በሽታ ስላለባት መብረቅ የወረደ እንደሆን በድንጋጤ ብቻ እንደምትሞት በልመና አይነት ነገረችኝ፡፡ እሺ አልኩና አልጋው ጫፍ ላይ አጠገቧ ተቀምጬ ነጎድጓዱን እያዳመጥኩ የጠፋው መብራት እስኪመጣ ድረስ በጨለማው ውስጥ መጠበቅ ጀመርኩ፡፡ ዝናቡም ሳያቆም፣ መብራቱም ሳይመጣ እንቅልፍ አሸንፎኝ አልጋው ጫፍ ላይ ጋደም አልኩ፡፡ ደባሌ አጠገቤ እንደ ነበረች አስታውሳለሁ፡፡ ጠዋት ሲነጋ ታዲያ በሕይወቴ ደርሶብኝ የማያውቅ ድንጋጤ ልቤን ሊነሳኝ ምንም አልቀረው፡፡ ደባሌ ክንዶቿን አንገቴ ላይ ጠምጥማ ተኝታለች፡፡ አንገቴን የጨመደዱትን ክንዶቿን አላቀቅሁና በተከታታይ ሦስት ጊዜ አማትቤ ከአልጋው ላይ ከወረድኩ በኋላ ልብሴን ለባብሼ ወደ ሥራዬ ሄድኩ፡፡

ቀኑን ሙሉ የማታው ነገር ሲገርመኝና ሲያሳፍረኝ ዋለ፡፡ ማታ ወደ ቤቴ ስመለስ ሌላ እንግዳ ከደባሌ ጋር ተቀምጦ አገኘሁት፡፡ ገና ከመግባቴ! "እስቻለው፣ ና ተዋወቀው ወንድሜን!" አለች ደባሌ፡፡ ምንም ሳልጠራጠር ከሰውዬው ጋር ተዋወቅሁ፡፡ ዕድሜው ከሰላሳ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጠረንገሎ ነው፡፡ በአካል የእኔ ተቃራኒ ነው ማለት ነው፡፡ ከሰውዬው ጋር ከተዋወቅሁ በኋላ መኝታ ቤቴ ገባሁና አልጋዬ ላይ አረፍ አልኩ፡፡ ወዲያው የክፍሉ በር ተንኳኳ፡፡ አበበች ነበረች ያንኳኳችው፡፡ በነገራችን ላይ የደባሌ ስም አበበች ነው፡፡ በሩን ከፈትኩላትና ገባች፡፡ ከዚያም፣ "እስቻለው! ለእንግዳው መጋበዣ ገንዘብ አምጣ እስኪ!" አለችኝ፡፡ ለወር መድረሻ ብዬ ከአፌ በጭቁ ያስቀመጥኳትን ድፍን አምስት ብር አውጥቼ ሰጠኋትና ወንድሜ ነው ያለችውን ሰውዬ አስተናገደችበት፡፡ ከዛሬ ነገ ይሄዳል ስል እንግዳው ብዙ ቀን ቆየ፡፡ በመጨረሻም ወንድም ተብዬው የሄደ እለት ማታ ቤት ስገባ አበበች አልጋዬን አንጥፋ እኔ ከማድርበት ክፍል ውስጥ ቡና አፍልታ ጠበቀችኝ፡፡ ቤቱ ፀድቷል፡፡ ምንም ሳልናገር ቡናውን ጠጣሁ፡፡ ትንሽ ቆየችና ደግሞ የእኔን ፍቃድ እንኳን ሳትጠይቅ አልጋዬ ላይ ወጥታ ለጥ አለች፡፡ የዝናቡ እለት ሌሊት የሆነው ሁሉ ትዝ አለኝ፡፡ ዛሬ መብረቁም ሰይጣኑም የለም ሂጂና አልጋሽ ላይ ተኚ ልላት ከአፌ ላይ መለሰኩት፡፡

"ለምን አበበችን አታገባትም?" አሉኝ እነዚያው መጀመሪያ በደባልነት እንድትኖር ያመጧት ሰዎች፡፡ "አሃ! አጅሬት ሁኔታውን ነግራቸዋለች ማለት ነው...



ትናንት ዋሽተው እቤቴ አስገቧት፡፡ እሷም የልቧን ሰራች፡፡ ዝም ስላልኳቸው ዛሬ ደግሞ ዋሽተው ሊድሩኝ ነው..." አልኩ በልቤ፡፡ የተፈራረምንበት የሰማንያ ወረቀት ቀለሙ ሳይደርቅ ወንድም ተብዬው እንግዳ እንደገና ከተፍ አለ፡፡

የሚስቴ ወንድም ነው ብዬ እንደ ወጉና እንደ አቅሜ ከጋበዝኩት በኋላ አረቄ ተገዝቶ ስንጠጣ አመሸንና መቼም መተኛት አይቀርም ተኛን፡፡ እኔ በባል ወግ እንግዳው በእንግድነቱ ከአበበች የድሮ አልጋ ላይ ተኛ፡፡ ዶሮ ሲጮህ ከእንቅልፌ ብንን አልኩ፡፡ አበበችን ከጎኔ ሳጣት ደነገጥኩ፡፡ መብራቱን ሳላበራ ቀስ አልኩና ከአልጋዬ ወርጄ በጨለማው ውስጥ እየዳበስኩ እንግዳ ተብዬው ሰውዬ ወደተኛበት ክፍል ሄድኩ፡፡ በእውነቱ ያን እለት ሰይጣን ገፋፍቶኝ ይሆናል እንጂ እንደዚህ አይነት ተንኮል ከዚያን ቀን በፊት አስቤም አላውቅ፡፡ ምናልባት ከጋብቻው ጋር አዲስ ፀባይ ተጋብቶብኝ ይሆናል፡፡ ድንጋጤም ጭምር ሊሆን ይችላል፡፡ ሰውዬው ከተኛበት አልጋ አጠገብ ስደርስ እንዲህ የሚል ድምጽ የሰማሁ መሰለኝ፡፡

"ቀስ ብለሽ ትሄጂያለሽ... አረቄ ስለጠጣ ቶሎ አይነቃም!" ወንድም ተብዬው ነበር፡፡

"ያወቀ እንደሆነ ይገድለኛል፡፡ ልሂድ!" አበበች ነበረች፡፡

ድንጋጤው ጨለማ ውስጥ እራሴን አዙሮ ሊጥለኝ ነበር፡፡ በፍጥነት ወደ አልጋዬ ተመልሼ ተኛሁ፡፡ ትንሽ ቆይታ አበበች ተመልሳ መጣችና ከጎኔ ተኛች፡፡ እንቅልፍ የያዘኝ መስዬ አዳምጣታለሁ፡፡ በልቤ ታዲያ፣ "አሁን ማንን ይሆን

ያታለልሽው? እኔን ወይንስ እራስሽን?" እላለሁ፡፡ ይሄ በሆነ በስንተኛው ወር እንደሆነ በቅጡ ባላስታውሰውም አንድ ቀን አበበች እንዲህ አለችኝ፤ "እስቻለው! መውለጃዬ ስለደረሰ የገንፎ እህል ማዘጋጃ ገንዘብ ያስፈልገኛል!" ደነገጥኩና ለመጀመሪያ ጊዜ፣ "ስንት ወር ሆነሽ?" ብዬ ጠየቅኋት፡፡ "ስምንት ሞልቶኛል!" አለች፡፡ "ታዲያ... አልኩና ልናገር ያሰብኩትን ነገር መልሼ ተውኩት "ታዲያ ምን?" አለች አበበች በቁጣ፣ "ታዲያ የገንፎ እህል አያስፈልገኝም? ባዶ ቤት ልውለድ?" "ከተጋባን ስንት ጊዜ ሆነን?" እንደገና ጠየቅኋት፡፡ በእሷ ብሶ አሁንም እየተቆጣች "ከመጋባታችን በፊት የሆነውን አታስታውስም ማለት ነው?" ብላ ጠየቀችኝ፡፡ ከዚህ በኋላ አልጠየቅኋትም፡፡ ደግነቱ ያን ሰሞን ቋንሽ ዕቁብ ስለነበረችኝ እንዳጋጣሚ ሆኖ እጣው ለእኔ ወጣና የጠየቀችኝን ገንዘብ ሰጠኋት፡፡ ከወር በኋላ አበበች ወለደች፡፡ ልጁን አየሁት፡፡ ቁርጥ ያንን ወንድሜ ያለችውንና በእንግድነት ቤታችን የሚመላለሰውን ሰውዬ ይመስላል፡፡ የጎረቤቱ ሰው "እንኳን ደስ አለህ! ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ አገኘህ!" ሲለኝ ሁሉ አፌ "ባምላካችሁ!" ቢልም ልቤ ግን "አንተ እስቻለው! ይሄንንም ነገር በዝምታ ልታልፈው ነው?" እያለ መጎትጎቱን አልተወም ነበር፡፡

አበበች አራስ ቤት እያለች ወንድም ተብዬው ተመልሶ ሲመጣ ብዙ አረቄ ከጠጣ በኋላ እንዲህ አለኝ፤ "ስማ አቶ እስቻለው! ይቅርታ አድርግልኝና የተወለደው ልጅ የእኔ ነው!"

"አውቃለሁ፡፡ የአንተ ነው፡፡" አልኩት፡፡



"እንዴት አወቅኸው?"

"መልኩ ቁርጥ አንተን ነው የሚመስለው፡፡"

"የምሬን እኮ ነው የምልህ!"

"እኔም የምሬን ነው፡፡"

"እንዴት አወቅህ ታዲያ?"

"ሁሉንም ነገር አይቻለሁ፤ ሰምቻለሁ፡፡"

"ታዲያ..."

"ታዲያ ምን?"

"እያወቅህ እንዴት ዝም አልክ?"

"ታዲያ ምን ላድርግ?"

አልመለሰልኝም፡፡ ነገሩ መልሶ እራሱን ሳይገርመው የቀረ አይመስለኝም፡፡ ልጁ የእሱ መሆኑን ሲነግረኝ የአንተ አይደለም ብዬ አምባጓሮ የማነሳ መስሎታል፡፡ ነገሩን ያላወቅሁ መስሎት ሲጨነቅ ሰንብቶ ይሆናል፡፡ ለነገሩማ እኔ ነበርኩ አስቀድሜ ጠብ ማንሳት የነበረብኝ፡፡ አበበች በተጋባን በአራት ወር ወለድኩልህ ስትለኝ ነበር ነገሩ ሁሉ ያለቀው፡፡ አበበች ከአራስ ቤት ስትወጣ የነገር አባታችን ባሉበት ሰማኒያው ተቀደደ፡፡ ይህንንም ያደረገችው እራሷ አበበች ነበረች፡፡ ትንሽ ቀን ቆይታ ደግሞ እንዲህ አለችኝ፣ "ልጁ ሲገረዝ የአይን አባት የምትሆነው አንተ ነህ!" እሺ ብዬ ተቀበልኩ፡፡ መቼም የወለደችው ልጅ ወርቅ ይመስላል፡፡ ልጅ ስለምወድ በልቤ፣ "ምነው የእኔ ልጅ በሆነ ኖሮ!" ብዬ ሳልቀና አልቀረሁም፡፡ አባቱ እየመሰልኩት ነው መሰለኝ ባየኝ ቁጥር ወደ እኔ እየተንጠራራ ያለቅሳል፡፡ እናቱ የምትሠራውን ሁሉ ቢያውቅ ኖሮ እንዴት ይስቅ ነበር!

በመሃሉ ዘመድ ተብዬው ባል አይሉት ውሽማ አበበችን ጥሏት ጠፋ፡፡ ለምን የልጁ አባት እንደ ጠፋ ብጠይቃት በመውለዷ ጥሏት እንደ ጠፋና ሁለተኛ እንደማይፈልጋት በሃዘን ነገረችኝ፡፡ እኔ ሲጥልብኝ ልጅ እወዳለሁ፡፡ የአበበችን ልጅ በተለይ በጣም እወደዋለሁ፡፡ እሱም እንደሚወደኝ አውቃለሁ፡፡ እንደ አባቱ ነው የሚያየኝ፡፡ እሱ ታዲያ ምን አጠፋ? እናቱ የሚሆን መስሏት ያደረገችውን አደረገች፡፡ ሳይሆን ቀረ፡፡ ታዲያ ሕፃኑ እኔን ቢያፈቅርና እንደ አባቱ ቢያየኝ እኔም ብወደውና እንደ ልጄ ባየው ምን ጥፋት አለበት? መቼስ ልጅ በእናቱ ስህተት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

አንድ ቀን ታዲያ እናቱ እግሬ ላይ ወድቃ ለፈጸመችው ስህተት ሁሉ ይቅርታ እንዳደርግላት ተማጸነችኝ፡፡ ምንም ስህተት እንዳልፈጸመች ሳረጋግጥላት መቼም ሳይገርማት አይቀርም፡፡ ልጁን ከመውደዴ የተነሳ ግማሽ ሊትር ወተት ተከራይቼለታለሁ፡፡ የገረመኝ ነገር ቢኖር አበበች የልጅዋን አባት ስም በእኔ ስም ማስጠራቷ ነው፡፡ "በረከት አስቻለው" ብላ ጠራችው፡፡ ምናልባት ውለታ የዋልኩላት መስሏት ያንን ለመክፈል ብላ ያደረገችው ይሆናል፡፡ መቼም ካሁን ወዲያ ያንተ ልጅ ነው ብላ እንደማትከሰኝ የታወቀ ነው፡፡ ብትለኝስ ምን ቸገረኝ-አሳድገዋለሁ፡፡

የመሥሪያ ቤት ባልደረቦቼ የደረሰብኝን ሁሉ ስለማያውቁ አሁንም ይቀልዱብኛል፡፡

"ዝምታ መቼ ነው ሚስት የምታገባው?"



ብለው ይጠይቁኛል

"አለቃ በበታቹ ማፌዝ ሲተው" እላቸዋለሁ፡፡

"ዝምታ መቼ ነው ትዳር የምትይዘው?" ይሉኛል ደግሞው፡፡

"ተንከልና መሰሪነት ሲያበቃ፣ የመንግሥት ገንዘብ መዝረፍ ሲቀር፣ ጉቦ መብላትና አድልዎ ሲያበቃ፤ ሚስት በባሏ ላይ ማመንዘሯን ስትተው፣ ወንዱ የወለደውን ልጅ ሲያሳድግ!" ብዬ እመልስላቸዋለሁ፡፡

አሁንስ ዝምታ አፍ አወጣ ብለው የምቀልድ እየመሰላቸው በሳቅ ይሞታሉ፡፡ ማን ያውቃል፣ ትንሽ ቆይተው ደግሞ ሌላ የቅጽል ስም ያወጡልኝ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ዝምታ ከንግግር በላይ ተደማጭ ቢሆን መልካም ነበር እያልኩ አስባለሁ፡፡ ሰሚ ቢያገኝ ኖሮ የእኔም ዝምታ ከንግግር በላይ በተሰማ ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን ዝምታዬ ቢገባቸው ይግባቸው ባይገባቸውም ምን አደርጋለሁ... እንደ እነሱ ግን አልወሽክትም፡፡ ምን ያደርጉኛል? ያው እንደለመዱት ይስቁብኛል እንጂ፡፡ ከእነሱ የእድሜ ልክ ልፍለፋና ከእኔ ዝምታ የትኛው ተሽሎ ይሆን? "አንዱ በአንዱ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ" አሉ! በመጨረሻ የሚስቀው በደንብ እንደሚስቅ ግን እርግጠኛ ነኝ፡፡

# ቤት የገባ ክረምት

“በዝናብ ወዴት ትሄዳለህ?” አለችው ብሩክታዊት ወረቀትና መጽሐፉን የሚይዝበትን ቦርሳ አንጠልጥሎ በር ላይ ቆሞ ዝናቡን ሲመለከት አይታው፡፡ የጠዋት ዝናብ ነው፤ ነጎድጓድና ብልጭታ የሌለው ዝናብ፡፡

ጳውሎስ ሳይናገር ትንሽ ጊዜ ቆየና፣ “ዝናቡ ውጪ ብቻ አይደለም የሚዘንበው!” አላት፣ አይኖቹን ዝናቡ ላይ ተክሎ፡፡

“እንዴት?” አለችው ብሩክታይት፡፡

“እዚህ ልቤ ውስጥም ሲዘንብ ነው ያደረው፡፡” አላት፣ በጣቱ ወደልቡ እያመለከተ፡፡

“እንዴት?” ብላ እንደገና ጠየቀችው፡፡

“ክረምቱ ልቤ ውስጥም ገብቷል፡፡” አላት፡፡

“ምን ማለትህ ነው?” አለች ብሩክታይት፣ “ለምን በግልጽ አትናገርም?”

“ልቤንም ሲበርደው ነው ያደረው ለማለት ነው፡፡”

“እኔ እንዲህ አይነት አማርኛ አላውቅም!” አለች “ብሩክታይት”

“ታውቂያለሽ” አለ ጳውሎስ፡፡

“አልገባኝም አልኩህ አልገባኝም!”



አልመለሰላትም ትንሽ አሰበና ደግሞ፣ “ቤት የገባ ክረምት! ልብ የገባ ክረምት!” ብሎ አጉተመተመ፡፡

“ምን ነካህ በጠዋት ጳውሎስ?” አለች ብሩክታዊት፡፡

“ክረምቱ ቤታችንም ውስጥ እየገባ ነው፡፡” አለ ጳውሎስ፡፡

“ቤት የሚገባ ክረምት አንተ ታውቃለህ!”

“መቼ ይሆን ነጻ የምንሆነው?” አለ ጳውሎስ፣ ደጅ ደጁን እየተመለከተ፡፡

“የምን ነጻነት” አለች ብሩክታይት፡፡

“የሚወዱትን ብቻ መሥራት፣ ለራስ ብቻ ተጠያቂ መሆን...” እንደገና አጉተመተመ፡፡

“አሁንስ ማን ያዘህ!” አለች ብሩክታይት፣ “አሁንም እንደፈለገህ መሆን ትችላለህ!”

“አንቺና ልጁ” አላት፡፡

“ልጁ ደግሞ ምን አደረገኝ ነው የምትለው?”

“ሰላም ሰጪኝ! ትንሽ ጊዜ ታገሺኝ!”

“ማን ሰላም ነሳህ? እራስህ ነህ ሰላም ያጣኸው!”

“እንዴት ማለት?”

“እንደ አውሬ በእኩለ ሌሊት እየገባህ!” ጳውሎስ አቋረጣትና፣ “እሱን እርሸው በቃ... የማታው ይበቃሻል!” አላት፡፡ እሷም በተራዋ አቋረጠችውና፣ “እሺ ምንድነው ፀባይህን እንደዚህ በቀን በቀን የሚለዋውጠው? ከመሬት ተነስተህ የሚያነጫንጭህ! አንዳንዴ ደግሞ ከመሬት ተነስተህ ዝግት የሚያደርግህ!”

አልመለሰላትም፡፡ በር ላይ ቆሞ ዝናቡን

እየተመለከተ ያስባል፡፡

"ላስረዳት አልችልም፡፡ ሊገባት አይችልም፡፡ አታምነኝም፡፡ ፊት ለፊት የምታየውን ጳውሎስን እንጂ ሌላውን ጳውሎስ አታውቀውም… በውስጤ የተደበቀውን ሌላውን እኔነቴን ልታውቀው አልቻለችም… አብረው እየኖሩ አለመተዋወቅ… በአንድ ሰው ውስጥ ሁለት ስብእና… መቼ ይሆን የሰው ልጅ የፈለገውን መሆን የሚችለው? በየቀኑ መጨነቅ… የፈለጉትን መሆን አለመቻል… ሁልጊዜ ያለመደሰት አባዜ…"

ሃሳቡ ድንገት ወደ ትናንት ማታ ተመለሰ፡፡

ትናንትም ቢሆን እኩለ ሌሊት ላይ ነበር ወደ ቤት የመጣው፡፡ እንደ እብድ ብቻውን እየተነጋገረ፡፡ "ቱ ሄል ዊዝ ዩ ሰካራም!" ይላል እራሱን በራሱ፣ "ዩ ብላዲ አርቲስት! አልኮሊክ አርቲስት! አሁን ቤትህ… ስትገባ… ሚስትህ… የት አመሸህ… ብላ… ትጮህብሃለች! እሺ… ካለችህ… አባብላህ… ይዘሃት… ትተኛለህ… አለበለዚያ… ሰላም… አጥተህ… ሰው… ሰላም… ትነሳለህ… ሰካራም… ነህ… አል ራይት…!"

ቤቱ ደርሶ በሩን አንኳኳው፡፡

"ኳ! ኳ! ኳ! ኳ!"

ብሩክታይት ታዳምጠዋለች፡፡

"ኳ! ኳ! ኳ! ኳ!"

ብሩክታይት ዝም ብላ ታዳምጣለች፡፡

"ብሩክታይት!" አለና በሩን አንድ ጊዜ በቡጢ ደለቀው፡፡

ብሩክታይት አልመለሰችለትም፡፡

"ብሩክታይት!… ማይ ጎድ!… ምን…



ሆናለች? እንቅልፍ… ነው… ወይስ ሞት?!"

"እውቃ ነው" ይላል በልቡ ደግሞ "እውቃ ነው ዝም የምትለው… ያው የተለመደው አመሏ ነው… የዝምታ አመጽ… መበቀያ ዘዴዋ ነው…"

ብሩክታይት ቤት ውስጥ ሆና ታስባለች፡፡ "የታባቱ! አልከፍትለትም! የኔ አንጀት በቅናት እንደ ተጠበሰ እሱንም ባይሆን ትንሽ ብርድ ይጥበሰው… ብርዱ ባይሰማውም በቃ ትንሽ በጨለማ ይገተር!"

ወዲያው ደግሞ፣ "በሞትኩት! ማጅራት መቺ ተከትሎት ቢመጣስ?… ከሰው ተጣልቶ ቢመጣስ!… አስገደልኩት ማለት አይደለም!" አለችና ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ በሩ ሄደች፡፡ በሩን ከፈተችውና ከጥግ ቆመች፡፡ ጳውሎስ አልገባም፡፡ ብሩክታይት ደነገጠችና በሩን መልሳ ዘጋችው፡፡ "ማነው እሱ 'ያንኳኳው? ካልተናገርክ ሁለተኛ አልከፍትልህም! ምንድነው ይህ ሰውን ማስፈራራት? በውድቅት እየመጡ ሰው ማስደንገጥ! ሙት አልከፍትልህም! ውጭ ታድራታለህ እንጂ አልከፍትልህም! እኔ ነኝ ካላልክ አልከፍትልህም!"

ጳውሎስ ከት ብሎ ሳቀ፡፡ ሳቁን ታውቀዋለች፡፡

ብሩክታይት በሩን በርግዳ ከፈተችና፣ "ማንን ለመፈታተን ነው? ማንን ለመሰለል ነው?" ብላ አንባረቀችበት፣ "እኔ ብሩክታይት እንዳንተ አይደለሁም፡፡ ሲያልፍም አይነካኝ፡፡ ከነማን ተማርከው ይሄን ዘዴ ደግሞ ልጄ? ማንን ለመፈተን ነው በር አንኳኩቶ ዝም የሚባለው?

ይሄውልህ አልጋው! መስኮቱም ያውልህ ዝግ ነው...

በጓሮ ወጣ እንዳትል ደግሞ ታውቀዋለህ የጓሮ በር የለም፡፡ መጀመሪያ እራስህን አርምና ከዚህ በኋላ ሰው መጠርጠር ትጀምራለህ እሺ? በራሱ የማይተማመን ነው ሌላውን የሚጠረጥረው!" አለች፡፡

ጳውሎስ ዝም ብሎ ወደ ቤት ገባ፡፡ ብሩክታይት በሩን መልሳ ዘጋችው፡፡

ቅድም የታጠበችበት የገላ ሳሙና መዓዛ የጳውሎስን አፍንጫ ዳሰሰው፡፡

ጳውሎስ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄደና አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠ፡፡

"ቢኒያም'ኮ ተኝቷል!" አለች ብሩክታይት ተከትላው መጥታ፣ "ደግሞ በቁምህ እንዳትወድቅበትና አንድ ልጄን ጨፍልቀህ እንዳትገድለው! ከሦስት ዓመት ትዳራችን የተረፈኝ ፀጋ ቢኖር ልጄ ብቻ ነው!"

"ሌላ ምንም አልተረፈሺም?" ሊላት ፈልጎ ነበር፡፡ ነገሩ ስላላማረው እራሱን በግድ ተቆጣጠረና ዝም አለ፡፡

ትንሽ ቆይቶ እራት ጠየቃት፡፡ አልራበውም፡፡ የት በልተህ መጣህ እንዳትለው ፈርቶ ነው የጠየቃት፡፡

"እዚያው በልተህ አትመጣም ነበር!" አለችው እንደፈራው፣ "እንዴቸ እስካሁን እራት ሳትሰጥህ ቀረች ልጂ? በባዶ ሆድ ፍቅር ምን ይሠራል? ትጎዳባታለህ እኮ!"

"ምንድነው የምትይው?" አለ ጳውሎስ፣ ብሩክታዊት የምትለው እየገባው፡፡

"አንተ ምንድነው የምትለው?" መለሰችለት፣



ከተቀመጠችበት ሆና እየተቁነጠነጠች፡፡

"እራት ነው ያልኩሽ ሌላ ምን አልኩሽ?" አለ ጳውሎስ፡፡

"እራት የለም! እዚያው ካመሸህበት ሄደህ ብላ!"

"የት ነው ያመሸሁት?"

"ታውቀዋለህ!"

"የት ነው እሱ፣ ሙች አላውቀውም!"

"አጥብቆ ጠያቂ የናቱን ሞት ይረዳል አሉ!" አለች ብሩክታይት

"ምህረት ጋ ነዋ ሌላ የት ታመሻለህ! ሰሚ ካሁኑ ከናፈቀህ ያውልህ ደጋግመህ ስማው! ምህረት ጋ ምህረት ጋ! ነው ያመሸኸው!"

"የማነች ምህረት?" እንደማያውቃት ሆኖ ጠየቃት፡፡

"እባክህ የኔ ጌታ የማታውቃት ለመምሰል አትሞክር! መዋሸት አትችልም ጳውሎስ... ያስታውቅብሃል፡፡ ግን አየህ፣ ያላወኩ እንዳይመስልህ! እሷ ግን አታዋጣህም፡፡ የስንቱን ትዳር እንዳፈረሰች ታውቀዋለህ፡፡ ከዚህ በፊት እንዳልከው የእኔ ነገር ይቅርና ይሄን አንድ ሕፃን እንዳታሳድግ ትሆናለህ፡፡ ሰምተናል ግሮሠሪውን እንዴት እንደ ከፈተች፡፡ አንድ ባለ ጋራዥ ነው አሉ የከፈተላት፡፡ እሷ ስትለክፈው የአራት ልጆቹን እናት ከቤት አባረራት፡፡ ወንዱ ግሮሰሪዋን እያየ አበላለሁ ብሎ ሲጠጋት ተበልቶ ይቀራል! እሷ እያማረባት ይሄዳል፡፡ እንኳን ሦስት አንድ የወለደች አትመስልም፡፡ እኛ ግን ገና በአንድ ልጅ

እንደ ትሬንታ ኳትሮ ወላልቀናል!”

ጳውሎስ ዝም ብሎ አዳመጣትና፣ “የማነች ምህረት እሷ እንደዚህ የምትወርጂባት?” ብሎ ጠየቃት፡፡

“ተው እባክህ ጳውሎስ! ምን የማታውቃት ይመስል ደጋግመህ ትጠይቀኛለህ? ምህረት ምህረት ነቻ! እዚህ ሰፈር ስንት ምህረቶች አሉ? እንኳን አንተ የሰፈሩ ጎረምሶች ሳይቀሩ ያውቋታል! ያቺ ሁልጊዜ የምታመሽባት የግሮሠሪዋ ምህረት! እንዴት እረሳሃት ልጄ?” ብሩክታይት እያፌዘች ጠየቀችው፡፡

ወጥመድ ውስጥ የገባች ድኩላ የሆነ መሰለው፡፡

“አ! ያቺ መንገድ ዳር ያለው ግሮሠሪ... እ... ምህረት ግሮሠሪ የሚሉት?... እና ምህረት ምን ሆነች ነው የምትይው?” አለ ጳውሎስ፣ ከገባበት ወጥመድ ለመውጣት እየተፍጨረጨረ፡፡

“ምህረት ውሽማህ ነች በቃ! ለማምታታት አትሞክር! እኔን አታታልለኝም!” አለችው ፍርጥም ብላ፡፡

“ማነች ውሽማዬ እባክሽ?” አለ ጳውሎስ፣ ወጥመድ ውስጥ እየተወራጨ፡፡

“ምህረት! ምህረት! ምህረት! ያውልህ ስሟ ከናፈቀህ እስክትጠግበው ድረስ ስማው! ብቻ ሰው ሲያነሳብህ በስርቅታ እንዳትሞትብህ እንጂ!”

“የእኔ ውሽማ?” አለ ጳውሎስ፣ ፖሊስ ፊት ቀርቦ ወንጀሉን ማመን እንደ ተሳነው ሰው ሁሉ ቃላቱ ላይ በደንብ እየተጫነ፡፡

“አዎን የአንተ ውሽማ! የአንተ!” በሃይል ጮሃ



መለሰችለት፡፡

“እረ ሰው እንዳይሰማሽ እባክሽ” አለ ጳውሎስ ሙትት ባለ ድምፅ፡፡

“ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው አሉ! አንተ አልሰማህም እንጂ ሰውማ አውርቶ ጨርሶታል!”

ከመከላከል ማጥቃቱን መረጠና፣ “ምን ትቀልጃለሽ እባክሽ! ስብሰባ አድርጋችሁ ነበር እንዴ?” አላት፡፡

“ለምንድነው ስብሰባ የምናደርገው?”

“ምህረት የጳውሎስ ውሽማ ነች ብላችሁ ለመወሰን ነዋ!” አላት፡፡ እያፌዘ ደግሞ “ብራቮ የኔ ሚስት! ይቺ ናት ጨወታ አለ ዘፋኙ!” አላት፡፡

“በማነው የምትቀልደው አ?” አለች ብሩክታይት ድንገት ቱግ ብላ፣ “የልብህን እየሠራህ በማነው የምታሾፈው?... ወሰደች ብለህ ነው አይደል እንደዚህ የምታላግጥብኝ? መሄጃ የላትም ብለህ ነው አይደል መጫወቻ ያደረከኝ! በቃ ነገ እነማዬ ጋ እሄዳለሁ! አልፈልግም በቃ!”

“ምኑ ነው የበቃው?” አለ ጳውሎስ፣ በሆዱ ደስ እያለው፡፡

“ሁሉም ነገር!” አለች ብሩክታይት በንዴት መጠፏ እያስታወቀባት፡፡

“እኔም?...” አለ ጳውሎስ፣ አልኮል ጠብ እንዳለበት ቁስል በሚቆጠቁጥ የፌዝ ፈገግታ እየተመለከታት፡፡

“አዎን አንተም!” አለች ብሩክታይት የሚናደድ መስሏት፡፡

“ልንለያይ ብርክት?”

“አዎን ምንም ማድረግ አልችልም! በቁሜ ተቃጠልኩ! ድሮስ ከእናንተ ጋር የኖረ ምን ሰላም ያገኛል! በቃ እኔም እሄድልሃለሁ አንተም እንደ ልብህ ትሆናለህ!”

“እኔን ፈተሽ ማንን ልታገቢ?”

“እሱ የእኔ ጉዳይ ነው ማንም አያገባውም!”

“ብንያምስ?”

“እነማዬ ጋ ያድጋል!”

“እኔ አልፈታሽማ!”

“ተቃጥለሽ ሙች የሚል ሕግ የለም!”

“እሺ የሆነው ሆነና” አለ ጳውሎስ፣ አንድ እግሩን በሌላው ላይ ደርቦ፣ “ምን አይነት ባል ነው የምታገቢው ብርክት?”

“ምን አገባህ? ” አለችው ተቆጥታ “እሱ የኔ ምርጫ ነው!”

“በናትሽ ብርክት ንገሪኝ! ምን አይነት ባል ነው የምትፈልጊው?” ብሩክታይት ቀና ብላ አየችውና፣ “እኔ የምለውን የሚሰማ! በጊዜ ቤቱ የሚገባ! የማያናድደኝ፣ ከብዕርና ከወረቀት ይበልጥ እኔን የሚወድ እና...” አለች እያሰላሰለች፡፡

“እና የማያስቀናሽ! አይደል ብሩክታይት?” አለ ጳውሎስ በመናደዷ ውስጥ ውስጡን ደስ እያለው፡፡

“አዎን የማያስቀናኝ! በመቅናቴ አላፍርበትም! ሁሏም ሴት መቅናት አትችልም፣ መውደድ የሚችል ብቻ ነው መቅናት የሚችለው!”

“ትወጂኛለሽ ማለት ነዋ ብርክት!” አለ ጳውሎስ በፌዝ አይነት፡፡



“ባልወድህ ኖሮ ሦስት ዓመት ቀርቶ ሦስት ቀን እንኳን አበሬህ አላድርም ነበር! አንተ ግን ገና ለገና ተወደድኩኝ ብለህ በነፍሴ ትጫወትብኛለህ አይደል?”

“እኔም'ኮ እወድሻለሁ ሙች!”

“ብትወደኝማ ነው እዚህ አይኔ ሥር ውሽማ ይዘህ የምታቃጥለኝ! የሰው መዘባበቻ የምታደርገኝ! የጎረቤት ቡና መጠጫ የሆንኩት! የሴቶች መሳለቂያ ያደረከኝ!”

“እሱን እርሽው ብርክት! ሊያጣሉን ነው የሆነ ያልሆነውን የሚነግሩሽ”

“እሷ እራሷ ነች ያወራችው!” አለች ብሩክታይት እንደገና ግንፍል ብላ፡፡

“ማ?”

“ምህረት እራሷ!”

“ምን አለች እባክሽ?”

“የእኔ ነው ትላለቻ! ሌላ ምን ትላለች?”

“ማንን?”

“አንተን!”

“እባክሽን አትቀልጂ!” አለ ጳውሎስ፡፡

“አሁንስ አበዛሽው!”

“በዛም አልበዛም በቃ አልኩህ በቃ!”

“ምኑ ነው የበቃው?”

“የአንተ ነገር!”

“ምን አደረኩሽ እኔ ብሩክታይት? ለምን ከመሬት ተነስተሽ እንደዚህ ትሆኛለሽ?”

“ዘማዊ ነህ!” አለችው ድንገት፡፡ ቃላቶቹ ጆሮው ውስጥ እንደ ቦምብ ፈነዱ፡፡

"ዝም በይ አንቺ!" አለ ጳውሎስ፣ "ወንድ ልጅ እንደዚህ አይባልም!"

"ይባላል!" አለችው።

"እመታሻለሁ!" አላት ውሸቱን።

"ብትመታኝማ ደስ ይለኝ ነበር! መምታት ቀርቶ በገደልከኝ! በቁሜ ከምትጫወትብኝ ብትገድለኝ ይሻለኝ ነበር!"

"ሆሆ! ደግሞ ሚስቱን ገደለ ተብዬ የሰው መተረቻ ልሁን?"

"የእኔ ሞት ሳያሳዝንህ ለሰው ተረት ትጨነቃለህ! በቅ ሌላ ለማንም አታስብም ማለት ነው?"

"ብንያም አለ"

"ስለ ብንያም አያገባህም! ሕፃኑን አታንሳው፤ እኔው እበቃሃለሁ!"

"በያ ብለሽ ብለሽ ልጅንም ካጂኝ!"

"እበትም ትል ይወልዳል አለች እማዬ!"

"አንቺ ልጅ ዝም በይ እመታሻለሁ! እንደዚህ አይባልም!"

"ያውልህ አለሁልህ ምታኝ! በለኝ! በናትህ ጳውሎስ ምታኝ! ብትመታኝ ደስ ይለኛል... ምታኝ እባክህ ተቃጥያለሁ! እባክህ ይወጣልኝ እንደሆነ ምታኝ! እባክህን ጳውሎስ በነገር ከምታቃጥለኝ እንደፈለከው ደብድበኝ! ከፈለክም ግደለኝ! ሰክሮ ነው የገደላት ትባላለህ! አይዞህ ምንም አትሆንም ጳውሎስ! ያውልህ የተቃጠለው ፊቴ በለኝ!" አለችና ጉንጯ ላይ ማዲያት የጣለበትን ቀይ ዳማ ሰልካካ ፊቷን አቀረበችለት።



ጳውሎስ ቀና ብሎ አያትና፣ "አበድሽ እንዴ አንቺ ልጅ?" አላት።

"እ... እኔ... አ... አላበድኩም... ግ... ግን..." ሳግ አላናግር አላት።

አልጋው አጠገብ ካለው ወንበር ላይ ነው የተቀመጠችው። ጳውሎስ ክንዱን ዘርግቶ እጁን እራሷ ላይ አስቀመጠውና ፀጉሯን ለማሻሸት ሞከረ።

"አልፈልግም በቃ ልቀቀኝ! አልፈልግም! እያናደድከኝ አልፈልግም! ሂድና የምህረትን ፀጉር አሻሽላት!" አለችው።

ሲጠጣው ያመሸው ጂን ይሸታል። ደም በጎረሱ ዓይኖቿ ቀና ብላ አየችው።

"ለምን እንደዚህ ትሆኛለሽ ብርክት?" አለ ጳውሎስ።

አልመለሰችለትም።

እንደገና ደግሞ፣ "ለምን ትናደጂያለሽ እንደዚህ? ለምን የሰው ወሬ እየሰማሽ እንደዚህ ትሆኛለሽ? ብርክት ሙች የምትይው ነገር ሁሉ ትክክል አይደለም። "ሙች! መሃላ አልወድም እንጂ በፈለግሽው ነገር እምልልሽ ነበር!" ሞቅታው ስለበረደበት ተናዷል።

"እሺ ለምን ታመሻለህ?" የጎሪጥ አይታ ጠየቀችው።

"እየሽ ብርክት እንደዚህ አትሁኚ እሺ?" አለ ጳውሎስ ድምፁ ያለቀሰ ሕፃን ልጅ የሚያባብል እየመሰለ፣ "እየሽ በቃ... ከአሥር ሰዓት በኋላ ቢሮ ትንሽ ቆየሁና መጽሐፉን ትንሽ ሠራሁ... ከዚያም

ወደ ቤት ልመጣ ስል አንድ ሰው አገኘኝና ካልጋበዝኩህ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ ፒያሳ ትንሽ አመሸሁ... አንድ ሁለት ስንል ሳናውቀው ለካ ሰዓቱ ሄዷል... ለምን ታክሲ አይጠፋም መሰለሽ... ምንም ምርጫ አልነበረኝም፤ በእግሬ መጣሁ፡፡ ለዚህ ነው የቆየሁት ብርክት..." አለ መዋሸቱን እያወቀው፡፡

"የት ነው ጠጣሁ ያልከው?" አለችው፣ ወንጀለኛ በሚመረመርበት አይነት፡፡

"ፒያሳ... ፒያሳ አልኩሽ እኮ!"

"እዚህ አካባቢ አልጠጣህም?" አለችው ፍርጥም ብላ፣ "ምህረት ቤት አልጠጣህም?"

"አልጠጣሁም!" አለና ሽምጥጥ አድርጎ ካዳት፡፡

"እስኪ ብንያም ይሙት በል!"

"ብንያም ይሙት!"

"እሺ የዛሬው ይቅርና... ሌላ ቀን ለምን ምህረት ግሮሠሪ ትገባለህ? ሰምቻለሁ፤ ያልሰማሁ እንዳይመስልህ!"

"ማን ነገረሽ?"

"ምን ቸገረህ ሰምቻለሁ ሰምቻለሁ!"

"በፊት በፊቴ ቆይቷል... ሙች ብርክት! ካንቺ የምደብቀው ነገር የለም... እና አንድ ሁለት ቀን ሰው ይዞኝ ገብቷል፡፡ ማንኛውም መጠጥ ቤት እንደምገባው ገብቻለሁ... ግን ማነው አየሁት ብሎ የነገረሽ ብርክት?"

"ያየህ ሰው ነግሮኛል አልኩህ! ስሙ ምን ይሠራልሃል?"

"እንዳልኩሽ ስጠጣ ሊያዩኝ ይችላሉ፡፡ ታዲያ ይሄ ወንጀል ነው ብርክት?"

"ምን ስትጠጣ ብቻ! ገና ከሩቅ ስታይህ ነው አሉ ሁለመናዋ ጥርስ ብቻ የሚሆነው... ደግሞም እንደ ሰው ባንኮኒ ላይ ወይንም ወንበር ይዘህ ሳይሆን የምትጠጣው እሷው ክፍል ውስጥ ጓዳ ነው አሉ የምትቀመጠው! ጉድህን ሰምቼልሃለሁ! ሌላም ብዙ ነገር ሰምቻለሁ!"

"ሌላ ነገር ደግሞ ምን ሰማሽ?"

"እሷ መኝታ ቤት ውስጥ ጎርደን ጂን ከነጠርሙሱ በበረዶና በቶኒክ ነው አሉ አብራችሁ የምትኮመኩሙት!" አለች ብሩክታይት፡፡ ትንሽ ዝም አለችና ደግሞ፣ "መጠጣቱን ጠጣ... ግን እየህ አልጠቀመችህም፡፡ መርዝ ነው የምትግትህ፡፡ ከዚህ ሁሉ ለምን ጥሩ ጥሩ ምግብ እየሠራች አታበላህም? ደግሞስ ከግሮሠሪ ትዳርህ አይበልጥብህም? ሥራህንስ ቢሆን ቤትህ ውስጥ ሆነህ አትሠራውም? እኔን የሚያስጠላ ምን እየነት መድሃኒት አቀመሱህ በናትህ? ደግሞስ መዝናናት ከፈለክ ለምን ራቅ ብለህ አትሄድም? ለምን ሰፈር ውስጥ እየተልከሰከስክ እኔንስ የሰው መሳቂያ ታደርገኛለህ?" አለችው፡፡

"አልጠላሁሽም" አለ ጳውሎስ "አሁንም እንደ ድሮው እወድሻለሁ፡፡ አትረጂልኝም እንጂ እወድሻለሁ፡፡ ችግሬን ግን አትረጂልኝም፤ ቢሆንም እወድሻለሁ፡፡"

"ታዲያ ለምን በጊዜ ቤት አትገባም?"

"ነገርኩሽ እኮ..."

ብሩክታይት አቋረጠችውና፣ "ምንም ብትለኝ

አይገባኝም! አላምንህም! ለመሆኑ ምህረት ቤት ካልሄድክና ጎርደን ጂን ካልጠጣህ ሥራውም አይሠራልህም?" አለችው።

"ዛሬ አልሄድኩም እኮ ነው የምልሽ! እንዴት ብዬ ላስረዳሽ?" አላት።

ጳውሎስ አልጋው ጫፍ ላይ እንደ ተቀመጠ ነው። ብሩክታይት እግሮቿን አጥፋ ወንበሩ ላይ ተኮራመተችና በረጅሙ የሌሊት ልብሷ ጫፍ ሸፈነቻቸው። ከዚያም አገጯን ጉልበቷ ላይ አስደገፈችውና መሬት መሬቱን ትመለከት ጀመር። ፀጉሯ ጆሮዎቿን ሸፍኖ ግራና ቀኝ በአየር ላይ ተንጠልጥሏል።

ጳውሎስ ይመለከታታል። የገላ ሳሙናዋ ጠረን ትንሽ ትንሽ ይሸተዋል።

"እሺ እራት አትሰጭኝም ብርክት?" አላት፣ ልጅ እናቱን በሚለማመጥበት አይነት።

"ያውልህ አቅርብና ብላ!" አለችው፣ ጉንጯን ከጉልበቷ ላይ ሳታነሳ።

"አንቺ እያለሽ እንዴት እኔ አቅርቤ ልብላ?"

"እኔ ምንህ ነኝ!" አለችው፣ መሬት መሬቱን እያየች።

"ሚስቴ ነሻ ብርክት!"

"ሂድና ምህረትን እንደሱ በላት!"

"በቃሽ አሁንስ አበዛሽው!" አላት በተራው ገንፍሎ።

"ቢበቃ ባይበቃ ምን እንዳትሆን ነው?" አለችው አገጯን ጉልበቷ ላይ እንዳስደገፈች "ከፈለክ



ምህረት ጋ ተመለስህ ሂድ! አይዞህ ሰዓቱ እንደሆን ገና ነው... እሷ ቀርታብህ ነው አይደል እንደዚህ የሚያነጫንጭህ?"

እንዴት ከተቀመጠበት ተፈናጥሮ እንደተነሳ አያውቀውም። ብቻ ዘሎ ተነሳና በጥፊ አጮላት። እሷም ተነሳችና አንገቱን በሁለት እጆቿ አነቀችው።

"ይሻልሻል ልቀቂኝ!" አለ ጳውሎስ ሁለት እጆቹን ቁልቁል እዝለፍልፎ ጥሎ ብሩክታይትን እየተመለከታት።

"ግደለኝ በቃ!" አለችው አንገቱ ላይ ተጠምጥማ።

ያደገውን ጸጉሩን ከኋላ በኩል ይዛዋለች። የገላ ሳሙናው መዓዛ ይሸተዋል።

"አልገድልሽም ልቀቂኝ!" አላት።

"በቃ ግደለኝ!" አለችው፣ እልህና መማጸን በተደባለቀበት አንደበት፣ "ዘላለም ባንተ ከምቃጠል ዛሬ ግደለኝ! ግደለኝ ነው የምልህ ግደለኝ!"

ስትናገር ትንፋሿ አንገቱን እንደ እሳት ወላፈን ይፈጀዋል።

"አንቺን ገድዬ ምን አገኛለሁ?" አላት በመጨረሻ።

"ምናልባት አንድ ታሪክ ትጽፍበት ይሆናል! እናንተ እንደሆናችሁ የራሳችሁን ጉድ ነው እሉ በሌላ ሰው ላይ የደረሰ አስመስላችሁ የምትጽፉት!" አለችና ጳውሎስ ፊት ቆማ ከፀጉሩ ጀምራ ፊቱንና አንገቱን ተመለከተችና አይኖቿን ድንገት አፍጥጣ፣ "እሺ ይሄ ሸሚዝህ ኮሌታ ላይ ያለውስ ቀለም

ምንድነው?” ብላ ጠየቀችው፡፡

“ምን? የምን ቀለም?” አለ ጳውሎስ ደንግጦ፡፡

“ምናልባት ሥራህን ቀይረህ ቀለም ቀቢ ሆነህ ይሆናል ማን ያውቃል!”

“ምንድነው የምትይው?” አላት እንደገና፡፡

“ይሄ ምንድነው ኮሌታህ ላይ ያለው ቀይ ቀለም? ነው የምልህ እስኪ ኮሌታህን ተመልከተው!”

አንገቱን ቆልምሞ የሸሚዙን ኮሌታ ተመለከተውና ደነገጠ፡፡

“በርግጥ ቀ... ቀለም ነው...” አላት፡፡

አቋረጠችውና፣ “ምናልባት ቀለም ስትቀባ ተፈናጥሮብህ ይሆናል!” አለችው፡፡ ወዲያው ደግሞ ቱግ አለችና፣ “የሷው ከንፈር ነው! እኔ መቼ አጣሁት... የዚያ የለምቦጯም ከንፈሯ ቅርጽ ነው! የምህረት ከንፈር ነው አይቻታለሁ!” አለች፡፡

“እባክሽ ዝም በይ አሁንስ አበዛሽው!” አለ ጳውሎስ፣ በቁጣና በሃፍረት መካከል ተንጠልጥሎ እየተወዛወዘ፡፡

“አንገትህን ያገኘች መስሏት ነው ኮሌታህን የሳመችው” አለች ብሩክታይት “ትንሽ ጎንበስ አትልላትም ነበር ከንፈርህን እንድታገኘው!”

ጳውሎስ ምንም ሳይናገር ጫማውንና ልብሱን አወላለቀና አልጋ ውስጥ ገብቶ ተኛ፡፡

ብሩክታይት ልብሷን ስታወልቅ ይሰማዋል፡፡ ብንያምን በመሃል አስተኛችና እሷ በግድግዳው በኩል ተኛች፡፡ የገላ ሳሙናው መዓዛ ደስ በሚለው በብሩክታይት ጠረን ተተክቶ ይሸተዋል፡፡ አስር ጊዜ ቁና ቁና ትተነፍሳለች፡፡



እግሩን ዘርግቶ በአንሶላው ውስጥ እግሯን ፈልጎ ነካው፡፡ እግሯን አውናጨፈችና አሸሸችው፡፡ እጁን በብንያም ላይ አሳለፈና ዳሌዋ ላይ አስቀመጠው፡፡ እጁን በጥፍሮቿ ቧጠጠችው፡፡ እሳት የፈጀው ያህል እጁን ሰበሰበና ሁሉም ነገር እንደማይቻል ተገንዝበ ቀዝቃዛ አንሶላውን ከተከናነበ በኋላ አይኖቹን ጨፈናቸው፡፡ ወዲያውም ዋና ገጸ ባህርይዋ ወላንሳ ምህረትን ቁመስላ በአይነ ህሊናው ታየችው፡፡ የልብወለዱ ዓለም ወላንሳ ከምህረት ሕይወት ጋር እየተመሳሰለበት፣ ወላንሳን ምህረት ውስጥ ፍለጋ ሲሄድ እንዴት ወጥመድ ውስጥ እንደገባ ሲያስበው ይገርመዋል፡፡

ሰሞኑን ግን የድራማውን የመጨረሻ ክፍል ጽፎ ይጨርሳል፡፡ ከዚያ በኋላ ምህረት ቤት አይሄድም፡፡ እናም እሱ ራሱ ተዋናይ የሆነበትን የሕይወት ድራማ ይፈጸምና ወደ ብሩክታይት ይመለሳል... የዚያን ጊዜ ቤት የገባውም ክረምት ይወጣ ይሆናል...

“ምን ላድረግ?” አለ ጳውሎስ እንቅልፍ አልመጣልህ ብሎት እየተጨነቀ፣ “ተሰጥኦ ስቃይ ነች... ማነው እሱ አንድ ጊዜ ስላላየኸው ነገርና ስላልተሰማህ ስሜት አትፃፍ ብሎ የመከረው?... ቼሆቭ ነው መሰለኝ... አዎን ቼሆቭ ነው... ወላንሳን ፍለጋ የምህረትን ሕይወት ማጥናት... ታዲያ ምን አጠፋሁ?... የሰው ልጅ መቼ ይሆን ህሊናው በነገረው መንገድ በሕይወት ውስጥ መጓዝ የሚችለው... ለመኖር በየቀኑ መጨነቅ... እራስን

ለመሆን መጨነቅ... ተሰጥኦ ስቃይ ነች... ቢሆንም መሸሽ የለብህም... የሕይወት ትርጉሙ ይሄው ነው... ከራስ ጋር መታገል... ከብዙ ነገሮች ጋር መታገል... ከሕይወት መሸሽ አትችልም... በገዛ ተሰጥኦህ እንደምትሰቃይ ማን ያውቅልሃል?... ማን ግድ አለው? ማን ያውቅልሃል?... የገዛ ሚስትህ እንኳን አታውቅልህም...!"

በመጨረሻም እንቅልፍ ገሳገለው፡፡



# ሰውና እስስት

አንድ ቀን ጠዋት በቅርቡ ስንታየሁ ከእንቅልፉ በድንጋጤ ባኖ ሲነሳ ትውስ ያለው ነገር ቢኖር ሌሊት ያየው ህልም ነበር፡፡ አስፈሪ ህልም፡፡ እንደ ተንቀሳቃሽ ትዕይንት ርዕስ አለው ህልሙ፡፡ 'ትንቢት' ይሳል የህልሙ ርዕስ፡፡ ዋናው ተዋናይ ያው ስንታየሁ ነው፡፡ ዕልም ካለው በረሃ መሃል ብቻውን የቆመ ይመስለዋል፡፡ አንድ መልአክ መስታወት ከሚመስለው ሰማይ ክንፎቹን እያርገበገበ ብቅ ይልና ቁልቁል ወደ ስንታየሁ እየቀረበ ይመጣል፡፡ የዚህን ጊዜ ስንታየሁ ደንግጦ አሸዋው ላይ ይንበረከክና ፊቱን በሁለት እጆቹ ይሸፍነዋል፡፡ ድንገት በሃይል ከመደንገጡ የተነሳ ያጎፈረው ጸጉሩና ያሳደገው ጢሙ በድንገት በረዶ መስሎ ይነጣል፡፡ ሰውነቱ በፍርሃት ከመራዱ የተነሳ የተንበረከከበት አሸዋማ መሬት በላቡ ይወረዛል፡፡

መልአኩ ወደ እሱ እየቀረበ ሲሄድ የስንታየሁም ፍርሃት ያንኑ ያህል እየተባበሰ ሄደ፡፡ መሬቷ ከእግሩ ሥር ራደች፡፡ ስንታየሁ የሚወድቅ መሰለውና አሸዋውን በሁለት እጆቹ ጨምድዶ

ያዘ። ድንገት አንድ ድምጽ በሃይል ሲሰማ ስንታየሁ ጆሮዎቹን በጣቶቹ ደፈናቸው።

"በጥፋትህ ቀሪውን ሕይወትህን ደግሞ እስስት መስለህ በረሃ ውስጥ ስትንከራተት እንድትኖር በፈጣሪ ተፈርዶብሃል!" ይላል ድምፁ። ሰውም መልአክም የሚመስለው ፍጡር ነበር የሚናገረው። ስንታየሁ ከተንበረከከበት እንደምንም ተነስቶ አይኖቹን ወደ ሰማይ ሲያቀና መልአኩ ገና ድሮ ትቶት ወደ ሰማይ አርጓል። ስንታየሁ በአሸዋው ላይ ሲሮጥ በላብ እንደተዘፈቀ ከእንቅልፉ ባነነ።

ጠዋት ታዲያ አልጋው ላይ እንደተጋደመ በግንባሩ ላይ የሚንቆረቆረውን ላብ ለመጥረግ እጁን ለማንቀሳቀስ ቢሞክር የሚቻል ሆኖ አላገኘውም። በሰው እጅ ፋንታ የእስስት እግር ተተክቷል። ያንኑ አዲስ የእስስት እግር አንስቶ ግንባሩን ሊነካ ቢሞክር አልደርስበት አለው። ይህ ነው የማይባል ድንጋጤ ሰውነቱን አንቀጠቀጠው። በጀርባው ለመንጋለል ቢሞክር አልተቻለውም። ከአልጋው ለመውረድ እግሩን ቢዘረጋው መሬት አልደርስልህ አለው። በጣም ከመደንገጡና ከመናደዱ የተነሳ ከአልጋ ላይ ወድቆ መሬቱ ላይ ተከሰከሰ። መራመድ አልቻለም። ጎንበስ ብሎ እግሮቹን አያቸው። የእስስት እግሮች ናቸው። መልኩ ምን እንደሚመስል ለማየት ስለቸኮለ ከበሩ አጠገብ ግድግዳ ላይ ወደተሰቀለው መስታወት በእስስታዊ እርምጃ መንቀሳቀስ ጀመረ። ድሮ ሰው በነበረበት ጊዜ ሁለት እርምጃዎች ብቻ የሚወስድበት መንገድ አሁን የዝቋላን ተራራ የመውጣት ያህል አስቸጋሪ



ሆነበት።

እንደምንም ከግድግዳው አጠገብ ደረሰና ቀና ብሎ መስታወቱን ለማየት ቢሞክር የሰማይ ያህል ርቆ ታየው። ሰው በነበረበት ጊዜ መልኩን መስታወት ውስጥ ሳያይ ወደ ደጅ አይወጣም ነበር። አሁን ደግሞ ምን እንደሚመስል ለማየት ስለጓጓ ሽቅብ ወደ መስታወቱ ለመዝለል ሞከረና ተመልሶ መሬት ላይ በጀርባው ተከሰከሰ። ከተንጋለለበት በስንት መከራ ተነስቶ ለመቆም ቢሞክር ሰው አለመሆኑ ትዝ ብሎት ሙከራውን እርግፍ አድርጎ ተወው። ከዚያም በጥልቅ ማሰብ ጀመረ። እንዴት አድርጎ መስታወቱ ጋ ደርሶ መልኩን ይየው? ካጎፈረው ጸጉሩና ጢሙ በስተቀር ምኑም ምናምኑም የእስስት መልክ ነው። እዚያው መስታወቱ ውስጥ መልኩ ሲለዋወጥ ተመለከተው። አንዴ የጣሪያውን ቀለም፣ አንዴ የግድግዳውን መልክ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ መስታወቱን እራሱን ይመስላል። ህልሙን እንደገና አስታወሰው። የመልአኩ ቃል ትዝ አለው። "በጥፋትህ ቀሪ ሕይወትህን ደግሞ እስስት መስለህ በረሃ ውስጥ ስትንከራተት እንድትኖር በፈጣሪ ተፈርዶብሃል!" ስንታየሁ በሁኔታው ምርር ብሎ ማልቀስ ጀመረ። እንባውን ሊጠርግ አንደኛውን የእስስት እግሩን ብድግ ሲያደርገው ግድግዳውን ለቀቀና በአየር ላይ ተምዘግዝጎ መሬት ላይ ተከሰከሰ። አንጓሉ የተፈጠፈጠ፣ አከርካሪው የተሰበረ መሰለው። ወዲያው ደግሞ የሰው አካልና አከርካሪ እንደሌለው

ትዝ ሲለው በእስስትነቱ መጠነኛ ደስታ ተሰማው፡፡ አወዳደቁ ኃይለኛ ስለነበር ግን ህመም ሳይሰማው አልቀረም፡፡

ህመሙ ሻል ሲለው ደግሞ ህልሙንና እርግማኑን እንደገና አስታወሰ፡፡ በተፈረደበት ፍርድና በቅጽበታዊ ፍጻሜው እጅግ አምርሮ ስላዘነ በብቸኝነት የሚሞት መሰለው፡፡ ሃፍረቱን የሚችለው አልመሰለውም፡፡ እንዴት አድርጎ ሁለተኛ የሰው ዓይን ያያል? ትናንት እንኳን ሰው ነበር፡፡ ከሚሰራበት የጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ውሎ ነበር እቤቱ የገባው፡፡ ዛሬ ጠዋትም ቢሆን ጓደኞቹ ሥራ ይገባል ብለው ይጠብቁታል፡፡ ደግሞም የቢሮውን ቁልፍ እሱ ስለሚይዘው መስሪያ ቤት መሄድ ካልቻለ አብረውት የሚሰሩት ሁለቱ ጓደኞቹ ቢሮ ሊገቡ አይችሉም፡፡ የዛሬው ይቅርና እስከወዲያኛውስ እንዴት ብሎ ይኖራል? ትናንት ሰው፣ ዛሬ እስስት- የፈጣሪ ቁጣ!

እንደዚህ በሃሳብ እየተብሰለሰለ ቤቱ ወለል ላይ ሲዘዋወር ቆይቶ በተዘጋው ቤት ቀዳዳ ወደ ውጪ ሲመለከት ጊዜው መርፈዱን ተገነዘበ፡፡ ፀሐይ ደምቃለች፡፡ ሰዎች እየተነጋገሩ ወደ ሥራቸው ይጣደፋሉ፡፡ ፊቱን ወደ አንደኛው የቤቱ ግድግዳ አዙሮ ሽቅብ ተመለከተ፡፡ ከፍ ብሎ ግድግዳው ላይ የመልአኩ ሚካኤል ምስል በመስታወት ውስጥ ሆኖ ተሰቅሏል፡፡ ስንታየሁ ሰው የነበረ ጊዜ እራሱ ነበር ምስሉን በግድግዳው ላይ የሰቀለው፡፡ አሁን ያንን ምስል ሲመለከት አንዳች ዓይነት የብሶት፣ የብቸኝነትና የተስፋ መቁረጥ ስሜት እስስታዊ



ስሜቱን ረበሸውና ስቅስቅ ብሎ ማልቀሱን ቀጠለ፡፡ ከዚያም ቀና ብሎ የሚካኤልን ምስል እየተመለከተ እንዲህ ሲል ጮሆ ጠየቀ፣ "ምን ባጠፋሁ እንዲህ ዓይነት ፍርድ ይፈረድብኛል?" በማለት፡፡ በሃይል ቢጮህም ድምጹ ደግሞ የድሮው ወፍራሙ ሳይሆን እንደ ክር የሰለለ ነበር - እስስታዊ ድምጽ፡፡

የመልአኩ የሚካኤል ምስል በስንታየሁ ሁኔታ እጅግ አድርጎ ስላዘነ ያነጋግረው ጀመር፡፡ እስስትስ ቢሆን የእግዚአብሔር ፍጡር አይደል?

"ለምን እንደዚህ ታዝናለህ ወዳጄ?" የሚካኤል ምስል ጠየቀ፡፡

"ሁኔታዬን አታየውም?" ስንታየሁ ሰው - የነበረው - እስስት፣ መለሰ፣ "ትናንት ሰው ዛሬ እስስት! ለምን አላዝን ጌታዬ?"

"ምን ታደርገዋለህ? ሁሉም ነገር የፈጣሪ ትዕዛዝ ነው!" አለ የሚካኤል ምስል፡፡

"ምን አጠፋሁና እንዲህ እንድሆን ተፈረደብኝ?"

"ሰው የነበርክ ጊዜ ሥራህ ምን ነበር ለመሆኑ?"

"ጸሐፊ ነበርኩ ጌታዬ!" ስንታየሁ እስስቱ መለሰለት፣ "እንደ ደራሲም እንደ ጋዜጠኛም ያደርገኝ ነበር"

"ለመሆኑ ስንት ዘመን አገለገልክ?"

"ቆይቻለሁ ጌታዬ" አለ እስስት የሆነው ሰው "ቢያንስ ሶስት መንግሥት አይቻለሁ!"

"ምናልባት ፈጣሪ ኃጢአትህን ቢያስተሰርይልህና ተመልሰህ ሰው ብትሆን..."

"ተመልሼ ሰው ልሆን!?" ስንታየሁ በጉጉት ጠየቀ፣ "ተመልሼ ሰው ለመሆን ምን ላድርግ?"

"እስኪ ሃጢኃትህን አንድ በአንድ ተናዘዝ" የሚካኤል ምስል አዘዘው።

"እሺ ጌታዬ! ከየት ልጀምር?... እ... አዎን! ከድሮ ልጀምር። የረባ ትምህርት እንኳን የለኝም። የተማረ መስሎ የመታየት በሽታ የተጠናወተኝ ግን ገና ከድሮው ነው። ሳጭበረብር ነው የኖርኩት ማለት ነው። ይሄም ጥፋት ነው አይደል?" "በደንብ እንጂ! ሃሳዊ መሲህነት ሃጢኃት ነው!" አለ የሚካኤል ምስል፣ "ለማንኛውም እስኪ ተናዘዝ ቀጥል!"

"በተማሩ ሰዎች ስለምቀናና ከእኔ የበለጠ ገንዘብና ሥልጣን እንዳያገኙ ስለምፈልግ እነሱን ጠልፌ ለመጣል ሌት ተቀን የተንኮል ወጥመድ ስተበትብ ነው የኖርኩት። እኔን በሚበልጡኝና በምጠላቸው ሰዎች ላይ እየሰለልኩ ለመንግሥት መረጃ ሳቀርብ የኖርኩትም ለዚሁ ነበር። ይሄም ጥፍት ነው አይደል?"

"በደንብ እንጂ! የሚካኤል ምስል መለሰለት፣ "ወንድምህን እንደራስህ ውደድ የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ ጥሰሃል!"

"እሺ ሌላ... ሌላ ደግሞ አዎን!... ልቤ የተመኘችን ሴት ሁሉ ደፍሬአለሁ። ሥልጣን የነበረኝ ጊዜ ደምወዝ አስጨምርላችኋለሁ እያልኩ ብዙ ምስኪን ሴቶችን አባልጌአለሁ። ባል ያላቸውንም የሌላቸውንም... ይሄም ጥፋት ሳይሆን አይቀርም..."

"ለመሆኑ አላገባህም ነበር?"

"አላገባሁም። እራሴን ከመጠን በላይ ስለምወድ ለራሴ ብቻ ነው የኖርኩት። እውነቱን ለመናገር ይሄ የራስ መውደድ አባዜ ሳይሆን አይቀርም ለዚህ ሁሉ መከራ የዳረገኝ። ከሰውነት ተራ አወጥቶ ከእንስሶች ጎራ የደባለቀኝ እሱው ነው!"

"አታመንዝር የሚለውን ትእዛዝ ጥሰሃል። የሌላውን ሚስት መመኘትህ በእርግጥም ሃጢአት ነው። እሺ ሌላስ? ቀጥል ወዳጄ። ሃጢኃትህን ሳትደብቅ አንድ በአንድ ተናገር። ምናልባት ፈጣሪህ ይቅር ቢልህና ተመልሰህ ሰው ብትሆን..."

"ከእንስሳትነት ወደ ሰውነት የምመለስ ከሆነ እናገራለሁ። "አለ ስንታየሁ እስስቱ፣" ጥላቻ ሌላው ተግባሬ የነበረ ይመስለኛል። ንቀት፣ ጥላቻና ምቀኝነት። የትውልድ ሀገሬ ሰው ካልሆነ፣ ዘመዴ ወይንም የእኔን የበላይነት ተቀብሎ የሚያጎበድድልኝ ወይንም ወሬ የሚያቀብለኝ፣ አለበለዚያም የእኔን የውሸት ዝና በከተማው ውስጥ የሚያስራጭልኝ ካልሆነ በስተቀር ማንንም ሰው አልወድም ነበር። አሁን ሳስበው ይኸው ከጥንቱ የሰፈነብኝ የሰው መጥላት አባዜ ሳይሆን አይቀርም ለእንስሳትነት ያበቃኝ"

"ጠላትህን እንኳን እንደ እራስህ ውደድ ይላል መጽሐፉ። አንተ ግን ምንም ያላደረጉህን ሰዎች ነው ስትጠላ፣ ስትንቅና ሕይወታቸውን ስታበላሽ የኖርከው። ከኃጢአትም ኃጢአት! እሺ ቀጥል..."

"አዎን ተመልሼ ሰው የምሆን ከሆነ ሁሉንም ነገር ልናገረው" አለ ስንታየሁ

እስስቱ፣ “እንደ እውነቱ ከሆነ ምንም ነገር አያረካኝም፡፡ ስልጣን ቢሰጡኝ ይበልጥ ሥልጣን እፈልጋለሁ፡፡ ገንዘብ ባገኝ የበለጠ ገንዘብ እመኛለሁ፡፡ በፍጹም አልረካም፡፡ ይሄስ ከሰውነት ወደ እስስትነት ለመቀየሬ ምክንያት ይሆን ይሆን?”

“ሃብታሞች፣ አልጠግብ ባዮችና ጨካኞች መንግሥተ ሰማያትን አይወርሷትም ሲባል አልሰማህም?” የሚካኤል ምስል መልሶ ጠየቀው፡፡

“የሰማዩ ቀርቶ የምድሩንም አላገኘሁት አሁንማ!” አለ ስንታየሁ እስስቱ እንደገና ሰቅስቅ ብሎ እያለቀሰ፣ “አልጠግብ ማለቴ ሳይሆን አይቀርም ለዚህ ሁሉ መከራ የዳረገኝ!”

“ጸሐፊ ነበርኩ ብለሃል” የሚካኤል ምስል ቀጠለ፣ “ደግሞም ለሶስት መንግሥት አገልግዬአለሁ ያልክ መሰለኝ... በየዘመኑ ምን ብለህ ጻፍክ? እስኪ ቀስ ብለህ አስታውሰው፡፡ ምናልባትም ኃጢአትህ የተደበቀው እዚያ ውስጥ ይሆናል፡፡ እስኪ አሁን እንኳን እውነቱን ተናገር፡፡ ምናልባት ፈጣሪህ ይቅር ቢልህ”

“ተመልሼ ሰው ከሆንኩስ እውነቱን እናገራለሁ!” አለ ስንታየሁ እስስቱ ሲቃ ባነቀው ድምጽ፣ “አዎን በአንደኛው መንግሥት ትዝ ይለኛል፣ ልጅ እግር ነበርኩ፡፡ ገና ሮጬ አልጠገብኩም ነበር፡፡ ገንዘብና ዝና ለማግኘት ሌት ተቀን እዋትት ነበር፡፡ እውነትም እንደተመኘሁት ቀናኝና ገንዘብ አገኘሁ፡፡”

“እንዴት አገኘኸው ለመሆኑ?”

“ንጉሡ እራሳቸው ናቸው የሸለሙኝ”



“ምን አድርገህ ሸለሙህ? ”

“ዘመኑ በእኛ አቆጣጠር 1953 ይመስለኛል፡፡ አዎን ልክ ነው፡፡ የመንግሥቱ ንዋይ አመጽ በከሸፈ ማግስትና ንጉሡ ተመልሰው ሀገራቸው ሲገቡ ነው፡፡ በጋዜጣችን ላይ የጻፍኩት ርዕሰ አንቀጽ ስላስደሰታቸው በሚኒስትሩ በኩል አስጠርተው አንዲት መኪና ሸለሙኝ፡፡ እኔም መኪናዋን ሸጥኩና በገንዘቡ ተደሰትኩበት፡፡”

“ምን ብለህ ጻፍክ ለመሆኑ?”

“የምስራቅ አፍሪካ አብሪ ኮከብ! ጻሐዩ ንጉሠ ነገሥታችን! በጥቂት ያኀረሳቸውን እጅ ነካሾች በሆኑ ከሃዲ ጀኔራሎች የተቃጣባቸውን ሴራ በጣጥሰው በድል አድራጊነት የአፍሪካ መዲና ከሆነችው አዲስ አበባ ሲገቡ ሕዝቡ ላይ ያንዣብብ የነበረው የጥፋት ደመና ተገፈፈ!” ብዬ ጻፍኩ

“በሁለተኛው መንግሥትስ ምን ብለህ ጻፍክ?”

“በሁለተኛው መንግሥት ዕድሜዬ እየገፋ መጥቶ ከወጣትነት ወደ ጎልማሳነት ተሸጋገርኩ፡፡ በንጉሱ ዘመን ገንዘቤንና ጉልበቴን የትም ስዘል ስላጠፋሁት ሚስትም ሳላገባ ቤትም ሳልይዝ ቆየሁ፡፡ ታዲያ ድንገት የጽጉሬን መሸበት ስመለከት ደነገጥኩና አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ተገነዘብኩ፡፡ ሆኖም ቤት የመስራት አቅም አልነበረኝም ነበር፡፡ ታዲያ አዲሱ መንግሥትም ቢሆን ጥሉ አልጣለኝም፡፡ አንዲት ቆንጆ ሐተታ ጽፌ አቀረብኩ፡፡ ወዲያውም ትልቅ መኖሪያ ቤት እንዲሰጠኝና ደሞወዜም እንዲጨመርልኝ የዛሬን

አያድርገውና ፕሬዚዳንቱ እራሳቸው ነበር የፈቀዱልኝ፡፡

"ምን ስላደረክ ነበር ሽልማቱ የተፈቀደልህ?" የሚካኤል ምስል ጠየቀ፡፡

"በጻፍኩት ሐተታ ላይ እንዲህ ብዬ ነበር፣ 'በሊቀመንበሩ የሚመራው የምርጥ ወጣት መኰንኖች አመራር ያንን የበሰበሰ የዘውድ አገዛዝ ገርስሶ የእኩልነት ዘመን አመጣልን፡፡ ሊቀመንበሩ ባይኖሩ ኖሮ የቀን ጀብ እንክት አድርጎ ይበላን ነበር' ብዬ ጻፍኩ፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ቀይ ሽብር የሚሉት ሲመጣ መሥሪያ ቤታችን ውስጥ ምንም ነገር ውስጥ ያልነበሩትን ንጹህ ሰዎች ጸረ መንግሥት ናቸው በማለት በምስጢር እየጠቆምኩ አንድ በአንድ አስለቀምኳቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ነበር ያንን ሽልማት ያገኘሁት፡፡ የዛሬን አያድርገውና ሊቀመንበሩ ቤተ መንግሥት ድረስ አስጠርተው 'ይቺ ሃገር አንተን የመሰሉ ታማኞች ስላሏት በእጅጉ ትኮራለች!' ብለው አመሰገኑኝ፡፡ በመረጃ ክፍል ውስጥም በትጋት እንድሠራ መከሩኝ፡፡ ሁለት ደመወዝ እበላ ነበር፡፡ አንድ በጋዜጠኛነቴ፡፡ ሌላው ደግሞ በመረጃነቴ"

"በሶስተኛው መንግሥት ምን አደረክ?" የሚካኤል ምስል ጠየቀ፡፡

"ሶስተኛው መንግሥት ሲመጣ ይኸው እንደምታየኝ ጸጉሬም ጢሜም ሸበተ፡፡ ድንገት እርጅናና ህመም እየተጫጫነኝ መጣ፡፡ ጡረታ መውጪያዬም ደረሰ፡፡ አሁን ደግሞ ምን ላድርገ እያልኩ ስጨነቅ አንድ ነገር ብልጭ አለልኝ፡፡



ለምን ይኼንንስ መንግሥት ቢሆን አላሞካሽም? የማታ እንጀራዬ ሊያምር ይችላል ብዬ አሰብኩ፡፡ አዲሱ መንግሥት እንደተቋቋመ ተሽቀዳድሜ እንዲህ የሚል ጽሑፍ አቀረብኩ፡፡ "በንጹሃን ደም የተጨማለቀው አምባገነን መንግሥት ተገርስሶ የዲሞክራሲ ጮራ ፈነጠቀ፡፡ በአምባገነኑ መንግሥት ጨለማ ውስጥ ስንማቅቅ ለኖርነው ጭቁኖች ብርሃን ወጣልን፡፡ የጥጋብና የነጻነት ዘመን ተጀመረ፡፡ ኢትዮጵያ ተመልሳ የሥልጣኔንና የእኩልነት፣ የሰላምና የፍቅር ሃገር ሆነች!" ብዬ ጻፍኩ፡፡ የድሮው መንግሥት ባለሥልጣኖች ሲታሠሩ እኔ ከመአቱ ተረፍኩ፡፡ ሹመት እንኳን ባላገኝም ድሮ ከዚያም ከዚያም ብዬ ያጠራቀምኩት ገንዘብ ስለነበረኝ ሰው ሁሉ ሲቸገር እኔ በደስታ መኖር ቀጠልኩ... ምን ያደርጋል ታዲያ ይኸው እንደምታየኝ በድንገት ከሰውነት ወደ እስስትነት ተለውጬ መከራዬን ማየት ጀምሬአለሁ..." አለና ስንታየሁ እስስቱ እግሮቹን እያወራጨ ማልቀሱን ቀጠለ፡፡

"ኑሮህ ጥሩ ከነበረ ታዲያ ለምን ነበር የምትማረረው?" የሚካኤል ምስል ጠየቀው፡፡

"እውነቱን ለመናገር ገንዘብ በቻ አልነበረም የምመኘው፡፡ በእርግጥ ገንዘብ እወዳለሁ፡፡ ሆኖም ሥልጣን ደግሞ ነፍሴ እስክትወጣ አፈቅራለሁ፡፡ ለዚህ ነበር ዘወትር ይከፋኝ የነበረው፡፡"

"ስማ ወዳጄ!" አለ የሚካኤል ምስል! "ድሮውንም ቢሆን ፈጣሪህ በስህተት ነበር ሰው ያደረገህ፡፡ መጀመሪያውኑ እስስት አድርጎ መፍጠር

ሲችል ሰው አደረገህ፡፡ አሁን እስስት ያደረገህ ወደ እውነተኛው ባህሪህ ሊመልስህ ፈልጎ ነው፡፡ መማረር አይገባህም፡፡ እስስት ብትሆንም የእግዚአበሔር ፍጡር ነህና!"

"ሰው እንዴት እስስት ይሆናል?"
ስንታየሁ እስስቱ እንባ እየተናነቀው ጠየቀ፡፡

"ይሄማ በፈጣሪ ሥራ መግባት ነው" አለና የሚካኤል ምስል ግድግዳው ላይ ከተሰቀለው መስተዋት ሥር በድንገት ተሰወረ፡፡

ስንታየሁ እስስቱ ቀዝቃዛው ቤት ውስጥ ብቻውን በእስስታዊ እግሮቹ ቆሞ ቀረ፡፡ የጊዜው መርፌድ በበሩና በመስኮቱ ጠርዝ በኩል በሚገባው የፀሐይ ጨረር ይለያል፡፡ ሰዎች ሲነጋገሩ ይሰማዋል፡፡ በሩን እንዴት አድርጎ ይከፍተዋል? እንዴትስ አድርጎ ወደ ውጪ ወጥቶ የሰውን አይን ያያል? የማታውን ህልሙን አስታወሰ፡፡ በህልሙ ብቻውን የቆመበት በረሃ ትዝ አለው፡፡ የመልአኩ ድምጽ እስስታዊ ጆሮው ውስጥ አስተጋባበት፡፡ "በጥፋትህ ቀሪውን ሕይወትህን ደግሞ እስስት መስለህ በበረሃ ውስጥ ስትንከራተት እንድትኖር በፈጣሪ ተፈርዶብሃል!"

በሩ እንኳን ቢከፈትለት ወደ ውጪ ወጥቶ ከሰዎች ጋር ባይሆን ከእስስቶች ጋር ተደባልቆ ይኖር እንደነበር በጸጸት ሲያስብ ስንታየሁ አይኖች ላይ እንባው መጥቶ ግጥም አለ፡፡ የዚህን ጊዜ በእስስታዊ ዓይኖቹ ምንም ነገር አልታይህ አለው፡፡ "ትንቢቱ ተፈጸመ" አለ በልቡ፡፡



# አንድ ለመንገድ

ገና ገብቼ እንደ ተቀመጥኩ ድንገት አጠገቤ መጣና፣ "ቀዩን ወይንስ ነጩን?" ብሎ በቁጣ ጠየቀኝ፡፡ ዘወትር የምጠጣውን በልምድ ያውቀዋል፡፡

"ቀዩ ስንት ሆነ?" መልሼ ጠየቅሁት፡፡

"ያው ነው ሦስት ብር!"

"በጠርሙስ?"
እራሱን በአዎንታ ነቀነቀ፡፡

"በብርጭቆስ?"

"ብር ከሀያ አምስት!" እንደ ተቆጣ መለሰልኝ፣ "ጠርሙሱ ይሻልሃል ግን!"

"አልጨርሰውም" አልኩት፡፡

"ምን አላት ብለህ ነው?... ሦስት ብርጭቆ ማለት ነው!"

"ነጩ ስንት ነው?" እንደገና ጠየቅሁት፡፡

"ያው ነው፣ ሦስት ብር እንዲያውም ነጩ ይሻልሀል፡፡ ብዙ ነው!"

"የምጨርሰው አይመስለኝም፤ ቢሆንም ነጩን አምጣው" አልኩት "ቀዝቃዛውን... ከአንድ ፔፕሲ ጋር!"

ከቤቱ ጥግ ራቅ ብሎ የቆመውን ማቀዝቀዣ ሲከፍተው የገማ ዓሣ ሽታ ተቀመጥኩበትን ትንሽ ክፍል አወዳት፡፡ ከክፍሏ በአንደኛው ግርግዳ ላይ ከፍ ብሎ በነጭ ጨርቅ ላይ በእጅ ጥልፍ የተሰራው የጊዮርጊስ ምስል ከነፈረሱ ይታያል፡፡ እኔ ከተደገፍኩት ግድግዳ በላይ ደግሞ አቡዬ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የአንድ አይናቸው ውሀ ለእርግብ ያጠጣሉ፡፡ በሦስተኛው ግድግዳ ላይ በተሰቀለው የቱሪስት ፖስተር ላይ የሚታየው የባህታዊ ምስል "ወይን ያስተፌሥህ ልበሰብ!" እያለ እዚያች ክፍል ውስጥ ገብቶ ለሚጠጣው ሁሉ ቡራኬ የሚሰጥ ይመስላል፡፡

ዲነጋ የቪኖ ጠርሙሱንና ፔፕሲውን አወጣና ፊቱን ከስክሶ የማቀዝቀዣውን በር በሀይል ወርውሮ በመዝጋት "ጥንባታሞች!" ብሎ ተሳደበ፡፡ ማንን ማለቱ እንደሆነ መጀመሪያ አልገባኝም ነበር፡፡ ከዚያም ጠርሙሶቹንና ብርጭቆውን አጠገቤ ካለው ትንሽ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠና መክፈቻውን አምጥቶ ጠርሙሶቹን ተራ በተራ ከፈታቸውና ቪኖውን ከቀዳልኝ በሁዋላ ባናቱ ላይ ትንሽ ፔፕሲ ጠብ አደረገበትና የተረፈውን ቪኖው ጠርሙስ ውስጥ ሞላው፡፡

"ምነው ዛሬ ደበረህ?" አልኩት ሊሄድ ሲል፡፡

"ዛሬ በጣም ደብሮኛል ጋሼ"

"ምነው ምን ሆንክ?"

"ከመሃመድ ጋር ተጣልቻለሁ፡፡ ዛሬ ወይንም ነገ ከስራ እወጣለሁ!"



"ምነው ለምን ተጣላችሁ?"

"ዛሬ ስለተበሳጨሁ አንድ ጠርሙስ አረቄ ባገኝ እጠጣለሁ!"

"ምንድነው ነገሩ?"

"ተወው ጋሼ ምን ይሰራልሀል?"

"ሌላ ብርጭቆ አምጣ" አልኩት፡፡

ሌላ የታጠበ ብርጭቆ ይዞ ከተፍ አለ፡፡

ቀዳሁለትና "ጠጣው!" አልኩት፡፡ ብርጭቆውን አንስቶ መጠጡን ግጥም አደረገው፤ ከንፈሮቹን በለበሰው ካኪ ካፖርት እጅጌ አበሰ አደረገና ብርጭቆውን መዝጊያው ስር ካለው ውሀ ከተሞላበት ሳህን ውስጥ አለቅልቆ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠውና ወደ ሌላው ክፍል ሄደ፡፡

ብርጭቆዬን አንስቼ ግማሽ ድረስ ጠጣሁለትና ሲጋራዬን ለኮስኩ፡፡ ዲነጋ ተመልሶ መጣና፣ "እግዜር ይስጥህ ጋሼ!" ብሎ ፈገግ አለ፡፡

"ዲነጋ!" መሃመድ ነበር ከወዲያኛው ክፍል የጠራው፡፡

"አቤት!"

"ምን እየሰራህ ነው? ናና ሂሳብ አስብ! በሽታ ያስብህ!"

"እዚህ ታዝዤ ነው መጣሁ"

"በሽታ ይምጣብህ!"

ዲነጋ ፈገግ ብሎ ጠቀሰኝና ወደተጠራበት ሄደ፡፡ ወዲያው ተመልሶ ደግሞ ማቀዝቀዣውን ተደግፎ ቆሞ ይመለከተኝ ጀመር፡፡

"ለምን ከመሃመድ ጋር ተጣላችሁ?" አልኩት፡፡

"ጠጡ ጋሼ!" አለኝ ለጠየቅሁት ጥያቄ መልስ ለመስጠት አለመፈለጉ እያስታወቀበት።

"እየጠጣሁ ነው" አልኩት ሳቅ ብዬ "እንዳልደግምህ..."

"በቃ በቃ! ጋሼ እግዜር ይስጥህ!" አለ ዲነጋ።

እንደገና ወደሌላው ክፍል ሄደና ሁለት ብርጭቆዎች ይዞ ተመለሰ። ሁለቱም ብርጭቆዎች ከሰው ፊት የተመለሰ መጠጥ ይዘዋል። ዲነጋ ከበሩ ስር ካለው ብርጭቆ ማጠቢያ ሳህን አጠገብ ሄደና ግራና ቀኝ መልከት መልከት ብሎ ብርጭቆዎቹ ውስጥ የቀረውን መጠጥ ተራ በተራ ጨለጠና አፉን በመዳፉ ከጠራረገ በሁዋላ ብርጭቆዎቹን ውሀው ውስጥ አለቅልቆ ዞር ብሎ ጠቀሰኝና ፈገግ አለ።

"ምንድን ነው?" ብዬ ጠየኩት። ብዙ ጊዜ ጭላጭ ሲጠጣ አይቼዋለሁ።

"አንደኛው ውስኪ ነው። አንደኛው ኮኛክ ነው። ጠግበው ነው ጥለውት የሄዱት፤ ዛሬ አንድ ጠርሙስ አረቄ እንኳን ባገኝ እጠጣለሁ!" አለ።

"ለምን የሰው ጭላጭ ትጠጣለህ?"

"ምን ላድርግ ጋሼ? በየመጠጥ ቤቱ ስሰራ የመጠጥ ሱስ ያዘኝ፤ ገዝቼ እንዳልጠጣ ደሞዜ ትንሽ ነች። ቀለብ ከቤት በወር 20 ብር ብቻ ነው የሚሰጠኝ። ከዚሁም ላይ ጠርሙስ ወይንም ብርጭቆ ስሰብር ይቆረጥብኛል። በወር ንፁህ ደምወዝ ከ10 ብር በላይ አይደርሰኝም። መሃመድ ደግሞ ብታየው አውሬ ነው። ተጣልተናል። ዛሬ



አንድ ጠርሙስ አረቄ ባገኝ ግጥም አድርጌ እጠጣ ነበር!"

"ለምን ተጣላችሁ?" አልኩት እንደገና።

"ትናንት ማታ ሁለት የቢራ ጠርሙስ ከነውሀው ሰበርኩ"

"እንዴት ሰበርከው?"

"ከፍሪጅ ሳወጣ በቃ እጄ በውሀ ርሶ ስለነበር አመለጠኝና ወደቀ"

"ምናለህ ታዲያ መሃመድ?"

"ሮጦ መጣና በጥፊ መታኝ። እከፍላለሁ እንጂ ለምን ትመታኛለህ አልኩት። አህያ ስለሆንክ በጥፊ ሳይሆን በዱላ ነበር መመታት ያለብህ አለኝ። ሰው ነኝ እንጂ አህያ አይደለሁም አልኩት። የሰው አህያ ነህ አለኝ። ተናደድኩና ሰው ለመሆን መጠጥ መነገድ አያስፈልግም። እኔም ነገ ጠዋት ከእዚህ ከአንተ ቤት ፊት ለፊት ሱቅ ልከፍት እችላለሁ አልኩት። ይሄን ጊዜ ምን ልበልህ በንዴት አበደ። ከነገ ጀምሮ መሄጃህን ፈልግ አለኝ፤ ምናልባት ዛሬ ያባርረኛል። አለበለዚያም ነገ ያባርረኛል። አላውቀውም። ግን ጋሼ መሃመድ እስከ ዛሬ የቆረጠብኝ ገንዘብ እራሱ አንድ ሱቅ ይከፍትልኝ ነበር!"

"አይዞህ ሌላ ስራ ታገኛለህ።" አልኩት።

"እኔም እዚህ ይሻለኛል ብዬ ነበር... ምን መሰለህ፣ ደመወዙ ሳይሆን ሆዴንና መኝታዬን ስለሚችሉኝ ነው።"

"ለምን ትጠጣለህ ታዲያ?"

"አንተ ለምን ትጠጣለህ ጋሼ?" እየሳቀ

ጠየቀኝ፣ “እንደሱ እንኳን ማለት አትችልም”

“እኔማ ገንዘብ ስላለኝ ነው የምጠጣው” አልኩት እየቀለድኩ፣ “እንዳንተ ብሆን ኖሮ ግን አልጠጣም ነበር”

“እኔ ገንዘብ ስለሌለኝ እየተበሳጨሁ ነው የምጠጣው፡፡ እንዳንተ ገንዘብ ቢኖረኝ አልጠጣም!”

ዲነጋ ወደ ሌላው ክፍል ሄደና ቂጡ ስር ቀይ መጠጥ የቀረበትን አንድ ብርጭቆ ይዞ ተመለሰ፡፡ ከዚያም ብርጭቆ ማለቅለቂያው ሳህን አጠገብ ቆሞ ከጨለጠው በሁዋላ ብርጭቆውን አለቅልቆ ዞር አለና በፈገግታ ተመለከተኝ፡፡

“ምንድነው” ብዬ ጠየቅሁት፡፡

“ያሁኑስ አኘሬቲቭ ነው!” አለ ዲነጋ፡፡

“ሲደባለቅ አያምህም?”

“ሲደባለቅ ጥሩ ነው!”

መልኩ ቅድም ቀይ ነበር፡፡ ትንሽ ቆይቶ አጋም መሰለ፡፡ አሁን ደግሞ ቲማቲም ሊመስል ምንም አልቀረውም፡፡ ማቀዝቀዣውን ተደገፈና ቆመ፡፡ የአይን ቆቡ አብጧል፡፡

“ዓሣው አይሸትህም?” አልኩት፡፡

“ከነገ ጀምሮ የት ያገኘኛል?” አለና ትከሻውን ነቅነቅ አደረገው፣ “ከዚህ ቤት ብሄድ ግማት ነው የሚቀርብኝ እንጂ ሌላ ምን ይቀርብኛል?” አለ ጮክ ብሎ፣ “ግማታቸውን ጥዬላቸው እሄዳለሁ!”

“ተው መሃመድ ይሰማሀል” አልኩት፡፡

“ይስማ! ማን ይፈራዋል? በአፌ ማን ያዝበታል? አፍ የተፈጠረው ለመብያ ብቻ አይደለም፡፡ ለመናገሪያም ጭምር ነው፡፡ እስከዛሬም



ዝም ያልኩት ይቆጨኛል፡፡ ጋሼ! የሰው ዋና ጠላት ማለት ፍርሀትና ዝምታ ነው!” አለ ዲነጋ፡፡

“አሁኑኑ ቢያባርርህስ?”

“እሱማ አይቀርም፤ አውቀዋለሁ፡፡”

“ደምወዝህን እንዳይከለክልህ!”

“ለማየት ያብቃህ ጋሼ... የቅድሙን ብር ከህምሳ ያስከፍለኛል፡፡ ከደምወዜ ምንም ገንዘብ እንደማይቀረኝ አውቀዋለሁ፡፡”

“ድገምና ጠጣ፤ ይሄን ሁሉ አልጨርሰውም!” አልኩት የቪኖውን ጠርሙስ አንስቼ፡፡ ዲነጋ ቀልጠፍ ብሎ ብርጭቆውን አቀረበልኝና ሞላሁለት፡፡ አጠገቤ እንደቆመ ጨለጠው፡፡ ከዚያም በፈገግታ አየኝና ወደ ማቀዝቀዣው ሄዶ ቆመ፡፡

“መቼስ እሳህ ይስጥህ ጋሼ! ሌላ ምን እላለሁ... ስራስ እንዴት ነው ጋሼ?”

“ጥሩ ነው” አልኩት፡፡

“አሁንም ያንኑ አናፂነት ነው የምትሰራው?”

“አሁንም አናፂ ነኝ፡፡”

“ከአናፂነት የበለጠ ስራ የለም ጋሼ! አናፂነት አንደኛ ስራ ነው፡፡” አለ ዲነጋ፡፡

“ጥሩ ስራ ነው፡፡” አልኩት፡፡

መሃመድ መጣና አጠገቤ ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ባዶ ጠርሙስና ቂጡ ስር የቀረውን ብርጭቆ ከተመለከተ በሁዋላ፣ “እዚህ ጋ ሂሳብ አስብ!” አለ፡፡ ዲነጋ ማቀዝቀዣውን ተደግፎ አይኖቹ ገርበብ ብለው መናገር የደከመው በመምሰል፣ “ሂሳብ የለበትም ተከፍሏል!” ብሎ

መለሰለት፡፡ ደነገጥኩ፡፡ መሃመድ አጠገቤ ቆሞ በጥርጣሬ ይመለከተኛል፡፡ እጄን ኪሴ ውስጥ አስገባሁና፣ "ቆይ አልተከፈለም... ተሳስቶ ነው፡፡ የሰጠሁት መስሎት ነው፡፡" ብዬ ገንዘቡን ሰጠሁት፡፡ መሃመድ ገንዘቡን ተቀበለኝና፣ "አንተ ቤቴን ለማፍረስ ነው አይደል የተነሳኸው? ከነገ ጀምሮ አይንህን እንዳላየው!" ብሎ ጮኸበት፡፡ ወደ እኔ ዞር ብሎ ደግሞ፣ "ተመልከተው እስኪ! ሰክሯል እኮ! ከየት እንደሚያመጣው አላውቀውም፣ ሁልጊዜ ሲሰክር አየዋለሁ፡፡ እየሰረቀ ይጠጣል ማለት ነው አይደል?" አለ፡፡ አልመለስኩለትም፡፡

"አሁኑኑ እሄዳለሁ!" አለ ዲነጋ በድንገት ከመሃመድ በማያንስ ጩኸት፣ "ያንተ ቤት ቢቀር ምን የምሆን ይመስልሃል?" የትም ሰርቼ እበላለሁ! ደግሞም፡፡ በቅርብ ቀን ውስጥ ከዚህ ቤት ፊት ለፊት እዚያ መንገድ ዳር ሱቅ ከፍቼ በሱቁ መስኮት በኩል አንገቴን አውጥቼ እየሳቅሁብህ "በላ ጋሼ መሃመድ! ያውልህ ፊቴ እንደለመድከው በጥፊ ምታው!" ብዬ ባልስቅብህ እናቴ አልወለደችኝም፡፡ በየወሩ ከደመወዜ በቆረጥከው ገንዘብ ፎቅ ሥራበት እሺ?" አለና ከጥቅምት ንፋስ በፈጠነ ሁኔታ ሮጦ ሄዶ ከቤት ወጥቶ ወደ ውጭ ተወረወረ፡፡

ከመሃመድ ቤት ስወጣ በጣም ጨልሟል፡፡ የመኪናውን መንገድ ተሻግሬ ወደ ቤት ሳመራ ዲነጋ ከሁዋላዬ ሲጠራኝ ሰማሁት፡፡ ቆም ብዬ ተመለከትኩት፡፡ የስራ ልብሱን እንደለበሰ ነው፡፡ አሁንም ይስቃል፡፡

"ምነው ጋሼ ጉድ አደረከኝ?" ብሎ



ጠየቀኝ፡፡

"ምነው ምን አጠፋሁ?"

"እንዳትከፍል ብዬ ተከፍሏል ስል አልተከፈለም ብለህ ጉድ አደረከኝ!"

"ደንገጬ ነው" አልኩት፣ "ደግሞም የሰው ገንዘብ ማስቀረት ጥሩ አይደለም"

"ዝም ብለህ መውጣት ነበረብህ!"

" አልፈለኩም"

"አይቆጨኝም ግን... ልክ ልኩን ነገርኩት አይደል ጋሼ?"

"ደምወዝህስ?"

"ምንም ደምወዝ አልቀረኝ፡፡ የተረፈውንም አይሰጠኝም"

"ምን ትበላለህ?"

"ለዛሬው ይሄ አለ፡፡ ሁለት ብር አሸጠዋለሁ፡፡" አለና ይዞት የወጣውን የቢኖ መክፈቻ ከኪሱ አውጥቶ አሳየኝ፡፡

"ነገስ? ከነገ ወዲያስ?"

"አላህ ያውቃል!"

"እዝናለሁ" አልኩት ለመሄድ እየተዘጋጀሁ

"ጋሼ" አለ ዲነጋ ጭንቅላቱን እያከከ፡፡

"ምነው ዲነጋ?"

"አንድ ለመንገድ አትለኝም?"

"እንዴት?"

"ያው መንገድ ላይ አይደለም ያለነው?" አለና ሳቀ፡፡

ሀምሳ ሳንቲም ሰጠሁትና "በል ደቅናህ

ዲነጋ... በርታ!" አልኩት፡፡

"መቼስ አባህ ይስጥህ ጋሼ!" አለ ዲነጋ፣ ድፍን ሀምሳ ሳንቲሟን ተቀብሎ፣ "መቼስ አባህ ብሎ ሱቁን የከፈትኩ እንደሆነ ውለታህን እከፍላለሁ!"

"እውነት ነው እንዴ ዲነጋ? ሱቅ መክፈት ትችላለህ?"

"እድሜ ይስጥህ እንጂ ታያለህ ጋሼ... መሃመድ ቤት ፊት ለፊት ሱቅ ከፍቼ ያልሳቅሁበት እንደሆነ ሰው አትበለኝ! እኔ ደግሞ እንደ እሱ አልኮል አልነግድም፡፡ ለሰው በሽታ እየሸጥኩ አልከብርም፡፡ ብቻ ለማንኛውም ታየዋለህ ጋሼ!" አለኝና ሰላምታ ሰጥቶኝ ሄደ፡፡

ከሳምንት በሁዋላ በዚያ አካባቢ ሳልፍ ዲነጋ ተሸክሞ እየዞረ ከሚሸጠው የሽንብራ እሸት ከሀምሳ ሳንቲም በላይ የሚያወጣውን አሸከመኝና፣ "የሱቁን ነገር የረሳሁት አይምሰልህ ጋሼ! ከአባህ ጋራ በቅርብ ቀን አሳይሃለሁ... እኔ እንደ መሃመድ በሽታ እየሸጥኩ ገንዘብ አልሰበስብም!" አለና የሽንብራ እሸቱን ዋጋ እንዳልከፍለው ነው መሰለኝ እየሮጠ ከአጠገቤ ተሰወረ፡፡



# የዋዜማው እንግዳ

ከሰዓት በኋላ የሉበሳንግ ራምፓን አስደናቂ ታሪኮች እያነበቡ ሲከራከሩ ነው የዋሉት፡፡ ሁለቱም ልጅ እግሮች ናቸው፡፡ የአዲስ አመት ዋዜማ ምሽት ነው፡፡

"ቅድም እንዳልኩህ የራምፓን ታሪኮች ሳነብ ምን እንደሆነ አላውቅም ደስ አይለኝም፤ ይደብረኛል፡፡" አለ ታደሰ፣ መፅሐፉን አስቀምጦ ቴፑን እየከፈተ፡፡

"የራምፓ ታሪኮች አይደሉም የሚያስፈሩህ፡፡ ጫቱ የፈጠረብህ ስሜት ነው፡፡" አለ ጌታቸው፣ ታደሰ የተባለው ልጅ ያስቀመጠውን መጽሐፍ አንስቶ ገፆቹን እያገላበጠ፡፡

"ጫቱ አይደለም፣ መጽሐፉ ነው" አለ ታደሰ ሰዓቱን እየተመለከተ፣ "የማይታመኑ ታሪኮች ናቸው፡፡ ደግሞም በዛሬው እለት የሚነበብ መጽሐፍ አይደለም፡፡ ለማንኛውም ወጣ ብለን እንመለስ"

"ስንት ሰዓት ሆነ?" ጌታቸው የሚባለው ልጅ ጠየቀ፡፡

"አራት ሰዓት ሊሆን ነው" ታደሰ

መለሰለት፡፡

"ከአሁን ወዲያ ወጥተን ምን እንሰራለን?" አለ ጌታቸው፣ "በዛሬው ምሽት መውጣት ጥሩ አይመስለኝም"

"እኔ በዛሬው ቀን እቤት አላመሽም፡፡" አለ ታደሰ፣ "በአዲስ ዓመት ዋዜማ እቤት ውስጥ አላመሽም፡፡ ይልቁንስ ወጣ ብለን አዲሱን ዓመት እንቀበለው"

"እኔ እዚሁ ሆኜ እቀበለዋለሁ፡፡" አለ ጌታቸው፡፡

"እባክህ እንውጣ!" አለ ታደሰ፡፡

"እኔ አልወጣም! እኔ መጽሐፉን አነባለሁ፤ አንተ ግን ሂድ" አለ ጌታቸው፡፡

"ብቻዬን?" ታደሰ ጠየቀ፡፡

"ወጣ ካልክ ሺህ ሰው ታገኛለህ! ወይንም ለምን መጠጡን እዚሁ አስመጥተህ አትጠጣም?"

"አንተስ ትጠጣለህ?"

"እኔ አልጠጣም፡፡ ከዛሬ ጀምሮ አልጠጣም፡፡ በአዲሱ ዓመት ላለመጠጣት ወስኜአለሁ፡፡ መጠጣቱ ምንም አልጠቀመኝም፡፡"

"ብቻዬንስ አልጠጣም" አለ ታደሰ፣ ቢሆንም ግን ጫት ቅሜ ሳልጠጣ አላድርም፡፡

"ካልጠጣሁ እንቅልፍ አይወስደኝም፡፡ ፍርሃት ፍርሃት ሲለኝ ያድራል፡፡"

"መጥፎ ልማድ ነው፡፡" አለ ጌታቸው፣ "እኔስ ባልጠጣም ምንም አይሰማኝም፡፡"

"አንተ ምንም አይሰማህም" አለ ታደሰ፣



"እድለኛ ነህ፡፡ ዛሬ በተለይ ፍርሃት ለቆብኛል፡፡ የራምቻ መጽሐፍ ነው መሰለኝ..."

"መጽሐፉ አይደለም፡፡ ጫቱ የፈጠረብህ ስሜት ነው፡፡"

"ለማንኛውም አንድ ሁለቱን በቁሜ ወርውሬ እመለሳለሁ፡፡ አለበለዚያ ዱካኩ አያሳድረኝም!" አለና ታደሰ ከተቀመጠበት ተነስቶ መለባበስ ጀመረ፡፡

"ለማንኛውም ጠንቀቅ በል፡፡ ዛሬ ምሽት ብዙ ሰው ሳይሰክር አይቀርም፡፡ እና ብዙ ሰው ሲሰክር ጥሩ አይሆንም!"

"አሁን እመለሳለሁ፡፡ እንዲያውም ከሰው ጋር አልጠጣም፡፡ አንድ ሁለቱን በቁሜ ቋ! አድርጌ እመለሳለሁ፡፡"

"ታዲያ ከጠጣህ በኋላ ሌላ ቦታ እንዳትሄድ!"

"የት ሌላ ቦታ?"

"ሌላ ነገር ፍለጋ!"

"ምን ሌላ ነገር? "

"ሴት፡፡ በዛሬው ምሽት ቢቀርብህ ይሻላል፡፡"

"ጫት ስቅም ሴት ያስጠላኛል፡፡" አለ ታደሰ፣ "ጫት ስቅም ሴት አልፈልግም፡፡ አሁን እመለሳለሁ፡፡"

ከዚያም ከቤት ወጥቶ ሄደ፡፡

አውራ መንገዱ ዳር ከተኮለኮሉት መጠጥ ቤቶች ሶስቱን ተራ በተራ አዳርሶ አራተኛው ቤት ገባና ገርበብ ካለው በር አጠገብ ወንበር ስቦ ከተቀመጠ በኋላ፣ "ጂን! ባሮንስ ጂን! ደብል አድርጊው!" አለ ታደሰ፡፡

አሳላፊዋ ጂን የተቀዳበትን ብርጭቆ አምጥታ አጠገቡ ካለው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠችለትና፣ “አምቦ ውሃ?” ብላ ጠየቀችው። እንደማይፈልግ በጭንቅላቱ ምልክት ሰጣትና ብርጭቆውን አንስቶ ከመጠጡ ተጎነጨለት። ከዚያም በአይኖቹ አሳላፊዋን ተከተላት። ተመልሳ ወደ መቀመጫዋ ሄደችና ራቅ ብላ ከፊት ለፊቱ ተቀመጠች። ሊጠራት ፈለገ። ወዲያው ደግሞ ሃሳቡን ቀየረና አይኖቹን ወደ ባንኮኒው አካባቢ መለሳቸው።

ሶስና ከባንኮኒው ጀርባ ቆማለች። ድምጿ ይሰማዋል። መልኳ ግን አይታየውም። ከፊት ለፊቷ የቆመው ሰውዬ ትከሻ ከልሏታል።

“እንዴት ነው ታዲያ አዲሱ አመት?” ሰውዬው ሶስናን ጠየቃት። ግዙፍ ነው ሰውዬው። ከጥቁር ሱፍ ጨርቅ የተሰፋ ሙሉ ልብስ ለብሷል።

“በጣም ጥሩ ነው አዲሱ ዓመት!” አለች ሶስና በመዘንጋት አይነት። ሌላ ነገር የምታስብ ትመስላለች።

“በአዲሱ ዓመት ምን ለማድረግ አስበሻል ታዲያ?” ሰውዬው እንደገና ጠየቃት። ድምፁ በመሳሪያ ብቻ ከተቀነባበረውና ቤቱ ውስጥ ከሚሰማው “ትዝታ” ከተሰኘው ሙዚቃ በላይ ይሰማል።

“መቼ? ዛሬ ማለትህ ነው?” ሶስና መልሳ ጠየቀችው፣ አሁንም ተዘናግታ። ‘በአዲሱ አመት’ የሚሉትን ቃላት በደንብ አላዳመጠችም ነበር።

“ኖኖ! በአዲሱ አመት! ነገ በሚገባው አዲስ አመት!” አለ ሰውዬው እያንዳንዱ ቃል



ላይ እየተጫነ።

“ውይ! ነገ በሚገባው አመት ነው እንዴ ያልከኝ? ይገርማል! ዛሬ ዋዜማ መሆኑን እንኳን እርስት አድርጌዋለሁ!” አለች ሶስና ራሷን ነቅንቃ።

“በአዲሱ አመት እያልኩሽ?” አለ ሰውዬው አቋርጧት፣ “የአዲስ አመት ዋዜማ እንዴት ይረሳል? ምን እያሰብሽ ነው ግን?”

ሶስና ትንሽ አሰበችና፣ “በአዲሱ አመትማ... እ... ነገ በሚገባው አዲስ አመት?...” ካለች በኋላ እንደገና ዝም አለች። ትንሽ ቆይታ ደግሞ፣ “በሚመጣው አመት እዚህ ሀገር የምቆይ አይመስለኝም... የዛሬ አመት ይሄን ጊዜ እዚህ ቤት አልገኝም።” አለች። ከዚያም ጎንበስ አለችና የውስኪ ብርጭቆዋን በትካዜ ተመለከተችው።

“የት ትሄጂያለሽ?” ሰውዬው ጠየቃት።

“ጂዳ!” አለች ሶስና “ሳውዲ አረቢያ!”

“እወስድሻለሁ ያለኝ ሰው አለ። አረብ ነው። እጮኛው እንድሆን ጠይቆኛል። አገባሻለሁ ይለኛል። በየአመቱ ለእረፍት አዲስ አበባ ይመጣል። ብዙ ገንዘብ ይሰጠኛል። ብዙ እቃ ይዞልኝ ይመጣል። ይሄውልህ ይሄንን ወርቅ ያመጣልኝ እሱ ነው።” አለች ሶስና ከቀኝ እጅዋ ሶስተኛው ጣቷ ላይ ያጠለቀችውን ወርቅ ለሰውዬው እያሳየችው። ባለ ትልቅ ፈርጥ ቀለበት ነው።

“ሳውዲ ምን ትሰሪያለሽ?” ሰውዬው እንደገና ጠየቃት።

"እዚያማ በቃ... ብዙ ገንዘብ አለ አሉ... ሁሉ ነገር እንደልብ ነው አሉ... ስራ ሞልቷል... እቃ ርካሽ ነው አሉ... እና ትንሽ ገንዘብ ማጠራቀም እችላለሁ..."

"ታዲያ አረቡን ወዳጅሽን ታገቢዋለሽ?" አላት ሰውዬው፣ ፌዝ በተቀላቀለበት አንደበት፡፡

"አሁን እኮ እጮኛዬ አይደለም!" አለች ሶስና አቋርጣው፣ "እሱ አይደል... በጣም ስለሚወደኝና አገባሻለሁ ስለሚለኝ... በቃ አለ አይደለም... እኔም ምንቸገረኝ ብዬ ለአፌ እሺ እለዋለሁ፡፡ ከልቤ አይደለም፡፡ ብዙ ስለዋለልኝ ነው... ደስ ይበለው ብዬ... ነገር ግን አላገባውም... ከልቤ አልወደውም፡፡ ደግሞም እዚህ ሌላ ወዳጅ አለኝ፡፡ ብቻ ሰሞኑን ተጣልተናል እንጂ... አሁን እንኳን ስለ እሱ እያሰብኩ ነበር..."

"ለምን ተጣላችሁ?"

"ከአረቡ ወዳጄ ጋር ስላየኝ በቃ ተጣላኝ፡፡ ደግሞም ሰዎች የሆነ ያልሆነውን ነግረውታል መሰለኝ እንደ እብድ ነው የሆነው፡፡ እሱም አገባሻለሁ ይለኛል፡፡ ይታይህ እስኪ ስንት ሰው ማግባት እችላለሁ? እኔ ግን እዚህ እንደማልቆይ ነግሬዋለሁ፡፡ እና እንደዚህ ስለው በጣም ተናዶ ደበደበኝ፡፡ ይሄውልህ በጥፊ የመታኝ ቦታ ይታይሃል?" አለችና ሶስና በባንኮኒው ላይ ተንጠራርታ በጥፊ የተመታችበትን ቦታ ለሰውዬው አሳየችው፡፡ ከዚያም "ይታይሃል አይደል? አሁንም ያመኛል፡፡ በልሂል አይደል? ሰንበር አውጥቷል?" ብላ ጠየቀችው፡፡



"መቼ ነው የመታሽ?"

"ከትናንት ወዲያ"

"ለምን ታዲያ ይሄንኑ ሰውዬ አታገቢውም?"

"የቱን?"

"የመታሽን ሰውዬ?"

"ውይ! ሰይጣን ነው እሱ! አላገባውም፡፡ በፍፁም አላገባውም፡፡ እብድ ነው! ይገድለኛል! ሰው ቀና ብለሽ እንዳታይ ነው የሚለኝ፡፡ ሰይጣናም ቢጤ ነው፡፡ ይታይህ እስኪ... ሌላ ሰው ሳላይና ከሌላ ሰው ሳልነጋገር እንዴት እኖራለሁ? አይገርምህም የፍቃዱ ነገር?"

"ፍቃዱ ነው ስሙ?"

"አዎን ፍቃዱ ነው ስሙ፡፡ ፀባዩም እንደ ስሙ ነው፡፡ እሱ የፈቀደው ነገር ካልሆነ በቃ ሞቼ እገኛለሁ ይላል፡፡ ብታየው ከፊቱ የተጣላ ነው!"

"እሺ በአዲሱ አመት ጂዳ ነሻ!" አለ ሰውዬው ርዕሱን ለመቀየር መፈለጉ እየታወቀበት፡፡

"አዎን አምላክ ከፈቀደ ሳውዲ ነኝ... ግልግል ነው እባክህ፡፡ ትንሽ ጊዜ እፎይ እላለሁ፡፡ ቆንጆ ሀገር ነው አሉ ጂዳ፡፡ አረቡ ወዳጄ ያልኩህ ከተማውን በፎቶግራፍ አሳይቶኛል፡፡ በጣም ቆንጆ ሀገር ነው፡፡ የፈረንጅ ሀገር ነው የሚመስለው፡፡ ባህር ዳር ላይ ነው ከተማው የተሰራው፡፡ ባህር ዳር የተሰራ ከተማ እንዴት ደስ ይላል መሰለህ! ምፅዋን ታውቃታለህ? እኔ በፊት ምፅዋ ነበርኩ... እና እንዴት ደስ ይላል መሰለህ! ባህሩ በተለይ ወደ ማታ... ንፋሱ ላይ ሲነፍስ... ፀሐይ ልትጠልቅ

አካባቢ ባህሩ ምን ይመስላል መሰለሀ... አቤት ደስ ሲል! እና ጂዳም ቆንጆ ከተማ ነች አሉ፡፡ ብዙ ቱሪስቶች ሳይመጡ አይቀሩም... እና ጥሩ ቢዝነስ ሳይኖር አይቀርም" አለችና ሶስና ድንገት ዝም ብላ የውስኪውን ብርጭቆ በትካዜ መመልከቷን ቀጠለች፡፡

ከዚያም ብርጭቆውን አንስታ ቂጡ ስር በቀረው ጭላጭ እያለቀለቀችው ሳለች ከእጅዋ አመለጣትና መሬት ላይ ወድቆ ተሰበረ፡፡

ወዲያው በሌላ ብርጭቆ ውስኪ ቀድታ አመጣች፡፡

"ከርሞ የሳውዲ ልጅ ነሽ!" አለ ሰውዬው እንደገና በቀልድ አይነት፡፡

"ለአንድ አመት ብቻ!" አለች ሶስና እግሯ ስር ተሰብሮ የወደቀውን ብርጭቆ ጎንበስ ብላ እየተመለከተችና ስብርባሪውን በጫማዋ አንድ ቦታ እየሰበሰበች፡፡

"ለምን? ለምን አንድ አመት ብቻ?"

"ትንሽ ገንዘብ እስከማጠራቅም"

"ከዚያስ?"

"ከዚያማ ተመልሼ እመጣለሁ፡፡"

"መጥተሽስ?"

"መጥቼማ በቃ... እዚሁ የራሴን ቢዝነስ እጀምራለሁ"

ታደሰ በብርጭቆው ቂጥ ጠረጴዛውን አንኳኳ፡፡ ሶስና አንገቷን አስግጋ ተመለከተችው፡፡ ከፊቷ የቆመውም ሰውዬ ዞር ብሎ ታደሰን አየው፡፡ ቀይ ቆንጆ ነች፡፡ ሶስና እሷ እራሷ አረብ



ለመምሰል ምንም ያህል አይቀራትም፡፡ ቅላቷ ማለት ነው፡፡

አሁንም "ትዝታ" የተሰኘው ዘፈን በመሳሪያ ቅንብር ይሰማል፡፡ መጀመሪያ ለታደሰ ጂን የቀዳችለት አሳላፊ ጠርሙሱን አምጥታ ብርጭቆው ውስጥ አንቆረቆረችለት፡፡ መጠጡን ጨልጦ መሄድ ፈልጓል፡፡ ሶስናንም በደንብ ለማየት ይፈልጋል፡፡

"እሺ ሶስና..." አለ ሶስና ፊት የቆመው ሰውዬ አንድ ጊዜ በረጅሙ ተንፍሶ፣ "ከጂዳ ስትመለሺ ምን አደርጋለሁ ነበር ያልሺው ቅድም?"

"የራሴን ቢዝነስ እጀምራለሁ፡፡ በቃ ራሴን ችዬ ለመኖር ነው የምፈልገው፡፡ ያን ጊዜ ማንም ሰው እንደ ፈለገው አይደበድበኝም፡፡ ሁልጊዜ ለገብርኤል የምሳለው ይሄንን ብቻ ነው፡፡ በንፁህ ልቡና ከለመኑት ይሰማል አሉ፡፡ የራሴ ቤት ካለኝ የማንም መጫወቻ አልሆንም፡፡"

"ቁርጥ ነዋ መሄድሽ?" አለ ሰውዬው ሳቅ ብሎ፡፡

"አዎን ቁርጥ ነው፡፡" አለችው፡፡

"ዛሬስ ታዲያ?" አላት፡፡

"ዛሬማ... ዛሬማ ይሄውልህ እዚህ ነኝ..." አለችው እየሳቀች፡፡

"ምን አሳቀሽ ታዲያ?" ጠየቃት፡፡

"ጥያቄህ ነዋ!" አለችው፡፡

"ብቻሽን ነሽ ዛሬ?" ፈገግ ብሎ ጠየቃት፡፡

"ይሄውልህ ብቻዬን ነኝ ዛሬ" አለችው በረጅሙ ተንፍሳ፡፡ ወዲያው ደግሞ፣ "አይበርድህም

ግን የዘንድሮ አመትባል?" አለችው፡፡

"እውነትሽን ነው... የዘንድሮው ዋዜማ ከወትሮው ጭር ያለ ነው፡፡" አላት፡፡ ወዲያ ደግሞ፣ "እዚህ ያለውስ ሰውዬ?... ተደባዳቢው... ዛሬ አይመጣም?" ብሎ ጠየቃት፡፡

"አይመጣም እባክህ እሱ... ይሄን ጊዜ በንዴት ከአንዱ ሆቴል ጥምቢራው ዞሮ ያየውን ሰው ሁሉ ልደብድብ ይላል... እንዳልኩህ ሰይጣናም ብጤ ነው!"

"ለምን ሰው ይደበድባል?"

"በቃ ከእኔ ጋር ሲጣላ እንደ እብድ ያደርገዋል፡፡ ሲጠጣ ደግሞ ይብስበታል፡፡ ታዲያ እኔ ምን ላድርገው? ገና ለገና እሱ ይናደዳል ብዬ የወደፊት እድሌን አላበላሸውም፡፡ በጊዜዬ ካልሰራሁበት እኮ ወደፊት ተስፋ የለኝም፡፡ ዞር ብሎ የሚያየኝ ሰው የለም፡፡" አለች ሶስና፡፡ ትንሽ ቆይታ ደግሞ፣ "እሱም እራሱ ቢሆን ዞር ብሎ አያየኝም፡፡ ወረቱ እስኪያልፍለት ድረስ ነው እንደዚህ የሚሆነው፡፡ የወንዶችን ፀባይ መቼ አጣሁት..." አለች፡፡

"ምን ያድርግ... ይወድሽ ይሆናላ!"

"ኤጭ አባክህ! ፍቅር ብሎ ነገር... የሞኝ ጨዋታ ነው!"

"እንዴት?"

"የጅሎች ጨዋታ ነው ፍቅር... የስራ ፈቶች ዘይቤ ነው!"

"ከፍቅር የበለጠ ነገር ምን አለ?"

"ኤጭ! ፍቅር! ፍቅር!... ፍቅር ምንድነው?"



"ፍቅርማ ፍቅር ነው! ምን ትጠይቂኛለሽ?"

"ፍቅር! ፍቅር!... ፍቅር ይበላል? ፍቅር ይጠጣል? ፍቅር ጌጥ ይሆናል? ፍቅር ብቻውን ዋጋ የለውም፤ የሞኝ ጨዋታ ነው!"

"ታዲያ ምንድነው ዋጋ ያለው?"

"ይሄንን አንተስ አጥተኸው ነው የምትጠይቀኝ?"

"ምንድነው እሱ? ሙች አላውቀውም!"

"ንብረት ነዋ! ገንዘብ ነዋ! ሌላ ምንድነው? እስኪ አንተ ነገ ጠዋት ባዶ እጅህን ናና አነጋግርህ እንደሆነ ታያለህ! እውነቴ ነው፤ ማንም ወንድ ቢሆን ገንዘብ ካልያዘ ዞር ብዬ አላየውም፡፡ አላነጋግረውም፡፡ ምን በወጣኝ አነጋግረዋለሁ? ገንዘብ ከሌለህ ዘመዶችህም አይወዱህም፡፡ የገዛ እናትህም ብትሆን አትወድህም፡፡ ማንም አይፈልግህም፡፡ ሞኝ አትሁን!"

"አሁንስ?" ጠየቃት ሰውዬው በፌዝ አይነት ሳቅ ብሎ፣ "አሁንስ ዞር ብለሽ ታይኛለሽ?"

"አሁንማ ምን ትጠይቀኛለህ? አለች ሶስና አጭርና ደረቅ ሳቅ ስቃ፣" "አሁንማ ውስኪ እየጋበዝክ ታዝናናኛለህ፡፡ እኔም አጫውትሃለሁ፡፡ አይደለም እንዴ?"

ሶስና ብርጭቆውን አንስታ ጭላጩን ውስኪ አፍዋ ውስጥ ወረወረችውና ከንፈሮቿን አሞጥሙጣ አጣጣመችው፡፡ ከዚያም ቀና ብላ ሰውዬውን አየችውና፣ "የሚደብር ምሽት! የሚደብር ዋዜማ! ልድገም?" ብላ ጠየቀችው፡፡

"ድገሚ! ድገሚ!..." አለ ሰውዬው፣ አንድ ጊዜ ፊቱን በእጁ መዳፍ ሞዠቆ በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ፡፡

"ትዝታ" የተሰኘው የሙዚቃ ቅንብር አልቆ በሌላ ተተክቷል፡፡

ታደሰ ሞቅ ብሎታል፡፡ ሶስናን በደንብ ለማየት ፈልጓል፡፡ ለማየትና ለአንድ ጊዜም ቢሆን ሊጠይቃት፡፡ እመቢ ካለችም ወደ ቤቱ ለመመለስ...

"ታዲያ በስንት ሰዓት ልመለስ?" ሶስና ፊት የቆመው ሰውዬ ሰዓቱን አየት አድርጎ ጠየቃት፡፡

"መቼ?" አለችው ሶስና፡፡

"ዛሬ ነዋ!" አላት ሰውዬው፡፡

ሶስና ትንሽ አሰበችና፣ "በቃ... ሩብ ጉዳይ ላይ ተመለስ!" አለችው፡፡

"ለስድስት ሩብ ጉዳይ?" አላት፡፡

"አዎን፡፡ ለስድስት ሩብ ጉዳይ፡፡ ገና አምስት ሰዓት ነው አሁን!" አለችው፡፡

"ሻርፕ ሩብ ጉዳይ እ?" አላት፡፡

"ሩብ ጉዳይ!" አለችው፡፡

ከኮቱ የደረት ኪስ የገንዘብ መያዣ ቦርሳውን አወጣና ድፍን የሃምሳ ብር ኖት ባንኮኒው ላይ አስቀመጠ፡፡ ሶስና ገንዘቡን አነሳችና፣ "እኔ ጋ ሁለት ውስኪ... አንተ ጋ አራት... እሺ ስንት ይሆናል?"

"አልጋ ያዝልኝ" አለ ሰውዬው አቋርጧት፡፡

"ውስኪው አስራ ስምንት ብር... አሺ አልጋ አስር... እሺ ስንት ይሆናል?"



"የቀረው ገንዘብ አንቺ ጋ ይቆይ!" አላት ሰውዬው እንደገና አቋርጧት፡፡ ሶስና ቀና ብላ አየችውና "ይሄ ብቻ?" ብላ ጠየቀችው፡፡

"ስንት ልጨምርልሽ?" አላት፡፡

"እኪ ተወው በቃ! ስትመለስ እንነጋገርበታለን!" አለችው፡፡

"ሻርፕ ሩብ ጉዳይ እ?" አላት፡፡

"ሩብ ጉዳይ!" አለችው፣ "ለስድስት ሩብ ጉዳይ!"

ብርጭቆውን አንስቶ የቀረውን መጠጥ ጨለጠና ወደ ውጪ ወጣ፡፡ ሶስና ባንኮኒውን እንደተደገፈች ብቻዋን ቆማለች፡፡ ለስላሳ ሙዚቃ ቤቱ ውስጥ ይሰማል፡፡

ታደሰ ሶስና ያያታል፡፡ ሶስና ውጪ ውጪውን ታያለች፡፡ አሳላፊዋ መሬት መሬቱን ትመለከታለች፡፡ ሶስና የውስኪ ብርጭቆዋን ከባንኮኒው ላይ አነሳችና ወደ ጓዳ መግቢያው በር አጠገብ ካለው ወንበር ላይ ተቀምጣ ጨለማውን ማየት ቀጠለች፡፡

ታደሰ ሊጠራት ፈለገ፡፡ ወይንም እሱ እራሱ ሄዶ ለምን በአዲሱ አመት ዋዜማ እንደዚህ በትካዜ ብቻዋን እንደተቀመጠች ሊጠይቃት ዳዳው፡፡ ወዲያው ደግሞ የቅድሙ ሰውዬ "ሻርፕ ሩብ ጉዳይ!" ያለው ቃል ጆሮው ውስጥ የማስጠንቀቂያ ደውሉን ደወለበትና ከተቀመጠበት ቦታ መቆየቱ መረጠ፡፡

ብዙም ሳይቆይ አንድ ሌላ ሰውዬ ድንገት

እንደ እሳት እራት ዘው ብሎ ወደ ቤቱ ገባና አይኖቹን ሶስና ላይ አጉረጠረጣቸው፡፡ አጭርና ፈርጠም ያለ ነው፡፡ ሶስና ፊት ተቸንክረና ቁልቁል ተመለከታት፡፡ ሶስና ድንገት ጨው የመሰለውን ፊቷን ቀና አደረገችና ሰውዬውን ተመለከተችው፡፡ አሳላፊዋ እንደቆሰለች ሚዳቋ ዘላ ወደ ጓዳ ገባችና ተሰወረች፡፡ አሁንም በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ ይሰማል፡፡

ሰውዬው ከመቀፅበት ሽጉጡን ከቀበቶው ስር ሳጥ አደረገና፣ "ድም! ድም! ድም!" ሶስት ጥይቶች ሶስና ላይ ተኮሰ፡፡ መጀመሪያ በአንድ ሁለት ጥይት ደረቷ አካባቢ ሲመቷት እንደ እስክስታ ትከሻዋን ሰበቅ ሰበቅ፣ ነዘር ነዘር አደረገችና "እ... እንዴ!... እ... እን!" ብላ ጮኸች፡፡ ወዲያው ግን ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠች ግድግዳውን ተደገፈችና ጭንቅላቷን ወደ ጎን ዘንበል አድርጋ ክንዶቿን ቁልቁል አዝለፍልፋ ጣለቻቸው፡፡

ሙዚቃው አሁንም ይሰማል፡፡

ገዳዩ ከጃኬት ኪሱ ውስጥ ሌሎች ጥይቶች አውጥቶ ሽጉጡን ሲያጎርስ ታደሰ የሞት ሞቱን ድንገት እንደ በረዶ ቀዝቅዞ ከተቀመጠበት ተነሳና ቆመ፡፡

ሰውዬው ሽጉጡን እያቀባበለ ፊቱን ወደ ታደሰ አዞረና፣ "አንተም ትፈልጋለህ?" ብሎ ጠየቀው፡፡

"ኖኖኖ!... እ... አልፈልግም! ሰ... ሰላም!... ፒስ፣ ፒስ! ፒስ!..." አለ ታደሰ፣ የቀኝ እጁን ሁለት



ጣቶች እንደ መቀስ ቀስሮ፡፡ ከዚያም በዝግታ ወደ ኋላው እያፈገፈገ ወደ በሩ ከተጠጋ በኋላ ድንገት ወደ ውጪ ሮጦ ወጣ፡፡

ከሶስት ደቂቃዎች በፊት የተመለከተው ትእይንት አሁንም በሃሳቡ ደጋግሞ ይመጣበታል፡፡ መቶ ሜትር ያህል እንደ ተራመደ እንደገና የተኩስ ድምፅ ሰማ፡፡ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የተተኮሰው "ድም!" አለ ልክ ብርድ ልብስ በዱላ ሲነረት በሚፈጥረው አይነት ድምፅ፡፡

"አሁንስ ለእራሱ ሳይሆን አይቀርም..." አለ ታደሰ በሃሳቡ፡፡ ከዚያም ፊቱን ወደ መጠጥ ቤቱ አዞረና ተመልሶ ሄደ፡፡ በሩ ላይ ሲደርስ ቆም አለና ገርበብ ባለው በር በኩል ወደ ውስጥ ተመለከተ፡፡ ቤቱ ውስጥ ማንም ሰው የለም፡፡ ሙዚቃው ግን አሁንም አላቋረጠም፡፡ ሶስና ግድግዳውን ተደግፋ ተቀምጣለች፡፡ ጭንቅላቷን ወደ ጎን ዘንበል ብሏል፡፡ ወደ አንድ ጎን ዝርግፍ ብሎ የተንጠለጠለው ፀጉሯ መልኳን አያሳይም፡፡ እግሮቿ ተዘርግተዋል፡፡ ደረቷ አካባቢና ሆዷ ላይ በጥይት ከተበሳሳችበት ቀዳዳዎች ደሟ እየመነጨ በጭኖቿ መጋጠሚያ በኩል አቋርጦ በተቀመጠችበት ወንበር ላይ እያለፈ መሬቱ ላይ ይንጠባጠባል፡፡ ከሶስና እግር ስር ደግሞ ገዳዩ በጀርባው ወድቆ ከጆሮ ግንዱ አካባቢ የሚፈልቀው ደም ወለሉ ላይ በቀጭኑ ይወርዳል፡፡

አሁንም ሙዚቃው እቤቱ ውስጥ ይሰማል፡፡

ታደሰ ሰዓቱን ተመለከተ፡፡ ለስድስት ሩብ ጉዳይ ሆኗል፡፡ በፍጥነት እርምጃ ወደ ቤቱ ሄደ፡፡

"የአዲስ አመት ዋዜማ... ጂዳ... ሰይጣናም ቢጤ ነው... ፍቅር የሞኘ ጨዋታ..." የሚሉት ቃላት ጆሮው ውስጥ አሁንም አሁንም ይደውላሉ፡፡

ታደሰ ቤቱ እንደገባ በጉልበቱ መሬት ላይ ተንበረከከና፣ "ከዚያ መአት ስላዳንከኝ ምስጋና ይግባህ!" አለ፡፡

ጌታቸው አይኖቹን ከመፅሐፉ ላይ አንስቶ ግራ በመጋባት አይነት ታደሰን ተመለከተውና፣ "ምነው ታዴ ምን ሆንክ? ደህና አይደለህም እንዴ?" ብሎ ስጋት በተቀላቀለበት ድምፅ ጠየቀው፡፡

ታደሰ፣ "በስመአብ ወልድ!" ብሎ አማተበና ተነስቶ ቆመ፡፡

"ምን ሆንክ ታዴ? ደህና አይደለህም እንዴ?" አለው እንደገና፡፡

"በስመአብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! እውነት እውነት አይመስለኝም!" አለ ታደሰ፡፡

"ምንድነው እንደዚህ የሚያደርግህ? እንደዚህ ስትሆን አይቼህ አላውቅም!" አለ ጌታቸው የሚባለው ልጅ፣ "ምርቃናው ነው ወይንስ ጨብሲው ነው እንደዚህ የሚያደርግህ?"

"በስመአብ! በስመአብ! እውነት እውነት አይመስለኝም!" አለ ታደሰ፡፡

"በጫት ላይ መጠጣት ትርፉ ይሄው ነው!" አለ ጌታቸው፣ "ጨብሲ የምትሉት ነገር መጥፎ ነው፡፡ ትንሹ ነገር ካለመጠን ያስጨንቃችኋል!"

"ጨብሲው አይደለም እባክህ!" አለ ታደሰ፡፡

"ታዲያ ምኑ ነው እንደዚህ የሚያደርግህ? ራምፓ ነው?"

"ራምፓ አይደለም እባክህ! በስመአብ ወልድ! ለማመን ያስቸግራል!"

"ምኑ?"

"ሲያቀብጠኝ ወጥቼ..."

"ሲያቀብጥህ ወጥተህ ምን ሆንክ?"

"ሞቼ ነበር!" አለ ታደሰ፣ "ሳላስበው ሞቼ ነበር!"

"ለምን ትሞታለህ?" ጌታቸው ጠየቀው "ትቀልዳለህ እንዴ?"

"ሞቼ ነበር!" አለ ታደሰ፡፡

"እንዴት?" ጌታቸው ጠየቀው፣ "ታሾፋለህ መሰለኝ!"

"አላሾፍም ጌቾ! ሞቼ ነበር! አንዱ ሰውዬ አንዷን ልጅ በሽጉጥ ገደላት... ከዚያም እኔን ሊገድል ሲል አመለጥኩ! ከዚያም ሰውዬው እራሱን ገደለ! በስመአብ ወልድ!"

"ትቀልዳለህ እንዴ?"

"ምን እቀልዳለሁ ጌቾ... ገደላት አልኩህ ገደላት! እራሱንም ገደለ... በስመአብ ወልድ!" አለ ታደሰ፡፡ ትንሽ አሰበና ደግሞ፣ "ለምን የገደላት ይመስልሃል ጌቾ? ለምን እራሱን ገደለ?" ብሎ ጌታቸውን ጠየቀው፡፡

ጌታቸው ትንሽ አሰበና፣ "ምን ይታወቃል? ምናልባት ያለፈው አመት ለእሱ መጥፎ ጊዜ ሆኖበት ይሆናል... ማን ያውቃል?" አለው፡፡

"ቢሆንስ ጌቾ ለምን እራሱን ይገድላል?"

ደጋግመው ያዩ ሰዎች"

"ሁለተኛ ማየት አልፈልግም!" አለ ታደሰ፣ "ሁለተኛ ሰው ሲሞት ማየት አልፈልግም፡፡ ሁለተኛ ጫት አልቅምም፡፡ ሁለተኛ አልጠጣም፡፡ እንኳን ብቻ ዛሬ ተረፍኩ!"

"ማየትህ እንኳን አይቀርም" አለ ጌታቸው፣ "እዚያ ቤት ባትሄድም ታየለህ" ታደሰ ዝም ብሎ ያስባል፡፡ ወዲያውም ከሩቅ የሚመጣ የደውል ድምፅ ሰሙ፡፡

"ይሄውልህ አዲሱ አመት ገባ፡፡ ደወሉን ትሰማለህ?" አለ ጌታቸው፡፡

"ለጥቂት እኮ ነው የሞቱት!" አለ ታደሰ "ለጥቂት!"

"በቃ እሱን እርሳውና ደውሉን አድምጥ!" አለ ጌታቸው፡፡

"በአዲሱ አመት ዋዜማ መሞት!" አለ ታደሰ፣ "በጣም ያሳዝናል! ያሰቡትን ሳይፈጽሙ መሞት!"

"ሞትን እርሳውና ስለ ሕይወት አስብ!" አለ ጌታቸው፣ "ስለሞት ማሰቢያችን ጊዜው ገና ነው!"

ታደሰ ዝም ብሎ ያስባል፡፡ ደውሉ አሁንም ይሰማል፡፡

"እንኳን ለአዲሱ አመት አደረሰህ ታዴ!" አለ ጌታቸው፡፡

"እንኳን አብሮ አደረሰን!" አለ ታደሰ፣ በሃሳብ እንደተዋጠ፡፡



"ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ በለው አለ!"

"ማነው እንደሱ ያለው ጌቶ?"

"ብሂል ነው።" አለ ጌታቸው፣ የአማርኛ ብሂል ነው። በቃ ሁሉንም ነገር እርሳውና እንተኛ። ስትተኛ ሁሉንም ነገር ትረሳዋለህ!"

"እሺ ጌቶ፣ እተኛለሁ።" አለ ታደሰ፣ "መተኛታችንማ አይቀርም!"

ያን እለት ሌሊት እንቅልፍ እንደማይወስደው ግን በልቡ ያውቀዋል። ያንን ምሽት ምናልባት እስከመጨረሻው ሽልብታው አይረሳው ይሆናል። "ከሰው ሞት የበለጠ ምን እንቅልፍ የሚነሳ ነገር ይኖራል?" አለ ታደሰ፣ ብርድ ልብሱን አፍንጫው ላይ ጣል አድርጎ እንቅልፉን እየተጠባበቀ።

# የተገፋውና የተረሳው

እኔስ በአንድ ወቅት ሥራ ነበረኝ አይደል... ነበረኝ ልበል እንጂ! ታዲያ አሁን ሥራ ባይኖረኝ ምን የሚያስገርም ነገር አለ? ስድስት ሰዓት ሆነ መሰለኝ ሠራተኞች ወጡ፡፡ ያንን እዚያ ማዶ የተቀመጠውን ሰውዬ አውቀዋለሁ፡፡ ድሮም ይሄው ነው - ምሳውን አንድ ሳምቡሳ በአንድ ስኒ ሻይ ነው የሚበላው፡፡ እንዴት ከስቷል በናታችሁ! ከእኔ የበለጠ ግን አልከሳም፡፡ ይኸው የአንድ ሳምቡሳና የአንድ ሻዩን ዋጋ ከፈለ፡፡ እኔስ በአንድ ወቅት እንደሱ ሥራ ነበረኝ አይደል? የዛሬን አያድርገውና እኔ ግን ክትፎ ወይንም ጥብስ ነበር ምሳዬን የምበላው፡፡ አሁን ኪሴ ውስጥ ስንት ሳንቲም አለኝ? አስር፡፡ አስር ሳንቲም ብቻ! ሰላሳ ሳንቲም የሚሞላልኝ ሰው ባገኝ አንድ ሻይ እጠጣ ነበር...

ይኸው እንግዲህ መንገዱ በሰው ተሞላ፡፡ አቤት ግርግር! አቤት ግፊያ! ዘላለም እንደተገፋፉ ይኖራሉ፡፡ ሁሉ ቦታ መገፋፋት፡፡ መንገድም ላይ መገፋፋት፡፡ ድሮ ሰው እንደዚህ አይበዛም ነበር፡፡



አውቶብሷ መጣች፡፡ እንዴት ሞልታለች! በሩ ተከፈተ፡፡ ሰዎች እየተጋፉ ወጡ፡፡ እየተጋፉ ገቡ፡፡ እነዚያ ሶስቱ ሰዎች ሌቦች ናቸው! በደንብ አውቃቸዋለሁ፡፡ ሌላው ሰው ግን አያውቃቸውም፡፡ አንደኛውን አንድ ቀን ፖሊሶች ይዘውት ሲሄዱ አይቼዋለሁ፡፡ አንደኛውን ደግሞ በሌላ ቀን ስንት ቁጥር አውቶብስ ላይ ነው?... ሲደበድቡት አይቼዋለሁ፡፡ በደንብ አስታውሳለሁ፡፡ ይኸው እነሱም ከተሳፋሪው ጋር ይጋፋሉ፡፡ እነሱስ ወደ ሥራ አይደለም የሚሄዱት? ኮሚክ ነገር ነው እባካችሁ! ቂቂቂ!... በሆዴ ልሳቅ እንጂ ጥርሴስ በስብሷል፡፡ ሌብነቱ ይቀናቸዋል ወይንም አይቀናቸውም፡፡ ይሄው ገቡ፡፡ ሥራ ገቡ ማለት ነው፡፡ ከእኔ ሥራ ፈትነት የእነሱ ሥራ ሳይሻል አይቀርም፡፡ ቢሻል ባይሻል ምን ቸገረህ? ያንተ ችግር ሌላ የእነሱ ችግር ሌላ፡፡ አሁን ሰላሳ ሳንቲም የሚሞላልኝ ሰው ባገኝ ኖሮ አንድ ሻይ እጠጣ ነበር...

ይኸው ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ተለቀቁ፡፡ እኔስ ብሆን ተምሬአለሁ አይደል፡፡ ተምሬ ነበር፡፡ ያውም እስከ ቢ.ኤ.ዲግሪ! እስከዛሬ ዶክተርም መሆን እችል ነበር፡፡ ታዲያ ምን የሚያስደንቅ ነገር አለ? እድል ቢያገኝ ዶክተር መሆን የማይችል ማነው? ምናልባት እህያ ብቻ ትሆናለች፡፡ የእህያ ዶክተር ቢኖርስ ኖሮ? ቂቂቂ!... በሆዴ ልሳቅ እንጂ ጥርሴስ በስብሷል፡፡ ሰብአዊ ጭንቅላት ያለው ሰው ሁሉ ማንም ከደረሰበት

መድረስ ይችላል፡፡ ዋናው እድሉ ነው፡፡ ሎተሪው ነው፡፡የሕይወት ሎተሪ፡፡ ተማርክ አልተማርክ ምን ልዩነት አለው? አንዱ ያጣል ሌላው ያገኛል፡፡ ታዲያ ምን የሚያስገርም ነገር አለ? ይልቁንስ አሁን ሰላሳ ሳንቲም ባገኝ አንድ ሻይ እጠጣ ነበር..

እዚህ ቡና ቤትስ ሰው አያስቸግሩም፤ ደጎች ናቸው፡፡ ዝም ብዬ ስቀመጥ እስካሁን አንድ ጊዜ እንኳን መጥቶ ምን ልታዘዝህ ያለኝ ሰው የለም፡፡ እንኳን ዝም አሉኝ ግን፡፡ ሁኔታዬን አይተው ይሆናል ዝም ያሉኝ፤ እብድ መስዬአቸው ይሆናል፡፡ ሌላ ቦታ ቢሆን ኖሮ ይሄን ጊዜ አባረውኝ ነበር፡፡ ምናልባትም ከናካቴው አያስገቡኝ ይሆናል፡፡ ለደረቅ ወንበር! አይበላ አይጠጣ፡፡ ብቀመጥ ምንለበት? እኔስ በአንድ ወቅት ወንበር ነበረኝ አይደል? ያውም ተሽከረካሪ ወንበር! ታድያ ቡና ቤት ወንበር ላይ ብቀመጥ ምን አደርገዋለሁ? እኔ ስለተቀመጥኩበት አያልቅ፡፡ እምቢ አልወጣም ብል ደግሞ ሌላ ነገር ይከተላል፡፡ ረብሸኛ ነው ብለው ፖሊስ ጣቢያ ይወስዱኛል ደግሞ የሻማ ብለው ይደበድቡኛል፡፡ ቢሆንም እዚያው ሳይሻለኝ አይቀርም፡፡ ደግሞ ብለህ ብለህ ፖሊስ ጣቢያ መግባት አማረህ? አሁን ያለኸው የት ነው? አራት ኪሎ ነዋ! ምን እንድልህ ፈልገህ ነው? አማኑኤል? ሁለተኛ አልገባም፡፡ አሁን ሰላሳ ሳንቲም የሚሞላልኝ ሰው ባገኝ አንድ ሻይ እጠጣ ነበር...

አሁን ግን ይቺ ፀሐይ ከበረደችልኝ ዙረቴን እቀጥላለሁ፡፡ ማለቴ ሥራዬን እቀጥላለሁ፡፡ የስራፈት ሥራዬን፡፡ አ! "ጌማዬም አልቋል ለካ፡፡ ያ ሰውዬ ደግሞ ምን ጊዜ ሻይና ዳቦውን ጨረሰው? ምን ያድርግ እንደኔ ርቦት ይሆናል፡፡ ደሞዙ አይበቃው ይሆናል፡፡ የኑሮ ውድነት ነው የሚሉት? የዋጋ መናር? ድሮኮ ኢኮኖሚክስ ተምሬአለሁ፡፡ ኢንፍሌሽን-ብዙ ገንዘብ ትንሽ እቃ ሲያሳድድ፡፡ የዋጋ መናር አጥቅቶት ነው ማለት ነው ሰውዬው አንድ ሻይና አንድ ዳቦ ብቻ ምሳውን የበላው፡፡ በዚህ አለም ላይ እሱን የሚመስሉ ስንት ሚሊዮን ሰዎች ይኖሩ ይሆን? ከእሱ የሚያንሱስ? በጣም ብዙ ሚሊዮን! አንደኛው መቼም እኔ ነኝ፡፡ አሁን ግን ሰላሳ ሳንቲም የሚሞላልኝ ሰው ባገኝ አንድ ሻይ እጠጣ ነበር...

አንድ ዳቦና አንድ ሻይ ለምሳ፡፡ አንድ ሳምቡሳ አንድ ሻይ ለምሳ፡፡ ቆይ፣ ቆይ፣ ቆይ፣... ይገጥማል እባካችሁ! አንድ ሳምቡሳ አንድ ሻይ ለምሳ! ለካስ ሳላውቀው ገጣሚ ነኝ፡፡ ባለቅኔ ነኝ፡፡ ከዚህ ሌላ ምን ያስፈልጋል? ሌላውስ ሰው ከዚህ የበለጠ ምን ይገጥማል? ባባ፣ ታታ፣ ቻቻ እያሉ ቤት ስለመቱ ነው? በቃ ካሁን ወዲያ ገጣሚ ነኝ ልበል መሰለኝ፡፡ ሥራ የለኝም ከማለት ሳይሻል አይቀርም መቼም፡፡ አንድ ሳምቡሳ አንድ ሻይ ለምሳ፡፡ ምነው ይሄ ሐረግ ሀሊናዬን ሙጭጭ አድርጎ ያዘው? እኔ ግን ምን ቸገረኝ ማንስ ምን ቢበላ፡፡ ደርሶ አዛኝ ቅቤ አንጓች፡፡ ለራስህ አልሆንክ ለሰው ታስባለህ፡፡ የራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች አሉ እያቴ! ሌላውን ነገር ሁሉ ተወውና

እስኪ ስራህን ለምን ጥለህ ወጣህ? ብቻ ምን ታደርግ? አላሰራ ሲሉህ... ሲገፉህ፣ ሲገፉህ በመጨረሻ በምቀኝነት ከሥራ አስወጥተውህ መልሰው ደግሞ ሰካራም፣ እብድ ወይንም በረንዳ አዳሪ ይሉሃል። እኔ ምን ላድርግ ታዲያ? አሁን ግን ሰላሳ ሳንቲም የሚሞላልኝ ሰው ባገኝ አንድ ሻይ እጠጣ ነበር...

አይ እሱስ የአንተም ጥፋት ነው። ለምን ሲገፉህ ተገፋህላቸው? ለምን ወደቅህላቸው? ከእነሱ በላይ ችሎታ እያለህ፣ ከነሱ በላይ ተምረህ፣ ከእነሱ በላይ እየሰራህ እንዴት አንተ መንገድ ላይ ወድቀህ የማይረቡ ሰዎች እየሳቁብህ ያልፋሉ? ይቺ ልጅ እንዴት ቆንጆ ናት በናታችሁ! እቺ አሁን ከሰውዬው ጋር ገብታ ፊት ለፊቴ የተቀመጠችው ልጅ። ሰውዬው ጀርባውን ሰጥቶኛል። ልጅቷ ግን ምን ትመስላለች!... አይ መልክ፣ አይ እግር፣ አይ ባት... ድሮም ቢሆን ከሴት ልጅ መልክ ደስ የሚሉኝ ባትና ጡት ነው። ጡቷን አላየሁትም። እግሯ ግን... ግ! አይወራም። ጡቷም ቢሆን በጣም ቆንጆ ነው የሚሆነው። ምናለበት አሁን አይኖቼ ቀሚሷን ዘልቀው ጡቶቿን የማየት ኃይል ቢኖራቸው? ደግሞም ወገኛ ነህ። እንደዚህ ሆነህ ስለ ውበትና ስለ ወሲብ ታስባለህ! ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ። አሁን ግን ሰላሳ ሳንቲም የሚሞላልህ ሰው ብታገኝ አንድ ሻይ ትጠጣ ነበር...

ውሃ በኃይል ጠምቶኛል። አሳልፊውን ውሃ አምጣልኝ ልበለው? ምንም ነገር ሳልወስድ ውሃ ብጠይቀው ምን ይለኝ ይሆን? አይ ይቅርብኝ አልጠይቀውም። ሰዓቱ ጮኸ። ስድስት ተኩል ሳይሆን አይቀርም። ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሰው ሁሉ ወደ ሥራው ይገባል። እኔም ወደ ሥራዬ እሄዳለሁ። ዙረትስ ቢሆን ሥራ አይደል? ያውም ቀላል ሥራ... ቂቂቂ! በሆዴ ልሳቅ እንጂ ጥርሴስ ወይቧል። ብገልጠው ሰው ሁሉ አውሬ መስዬው ጥሉኝ ይሮጥ ነበር። አሁንስ ቢሆን ከአውሬ በምን እሻላለሁ? በሁለት እግሩ የሚሄድ እንስሳ ማነው እሱ? ቆይ እስኪ-ዳይኖሶር ነው። ቅድመ ታሪክ እንስሳ። እኔም ዘመናዊ ዳይኖሶር ነኝ። የተገፋው ዳይኖሶር። ተጠቅመውብት እንደ እቃ የጣሉት ዳይኖሶር። 'ዘዋሪው ዳይኖሶር' በሚል ርእስ አንድ ቀን መፅሐፍ ሳልፅፍ እቀራለሁ ብላችሁ ነው? የታሪኩን ሴራ አውቀዋለሁ። እንደዚህ ነው። አንድ ዳይኖሶርና አንድ ጅብ አድነው ያገኙትን አብረው ለመብላት ይስማሙና አንድ ሰሞን ጓደኞች ይሆናሉ። ትንሽ ቆይተው ጅቡ አንድ ሕግ ይደነግጋል። ዳይኖሶሩ ለፍቶ ያመጣውን ጅቡ ብቻውን እንዲበላ። የዋሁ ዳይኖሶር እሻፈረኝ ይላል። ያምፅና ይጠፋል። ጅቡም ስለተነቃበት ወደማያውቁት ሃገር ሄዶ ሲመሽበት ቆዳ እንጥፉልኝ ይላል። ዳይኖሶሩ እንዲህ እንደ እኔ ሲዞር ይኖራል-ከጅቡ የተሻለ ጓደኛ ፍለጋ። የታሪኩ ሂደት እንደዚህ ነው። መፅሐፉን መቼ እንደምፅፈው አላውቀውም። አሁን ግን ሰላሳ ሳንቲም የሚሞላልኝ ሰው ባገኝ አንድ ሻይ እጠጣ ነበር...

ይቺ ልጅ እንዴት ነው የምትስቀው

በናታችሁ? አይ ፈገግታ፣ አይ ጥርስ፣ አይ ባት! ይሄን ጊዜ'ኮ አብሯት ያለው ሰውዬ ምንም አይመስለውም ይሆናል፡፡ የእኔ ሚስት ብትሆንስ? በቃ የእኔ ሚስት ናት! በሃሳቤ አግብቻታለሁ፡፡ ቂቂቂ! በሆዴ ልሳቅ እንጂ ጥርሴስ ወይቧል፡፡ ልባሷን አውልቃ ራቁቷን ስትሆን ምን ትመስል ይሆን? ጉልላት ትዝ አለችኝ፡፡ ጉልላት የድሮዋ ሚስቴ፡፡ ጥላኝ ሄዳለች፡፡ ድሮስ ሥራ የሌለው ባል ምን ይሰራላታል፡፡ ምርጫዋ ነው፡፡ በሰው ምርጫ ምን አገባኝ? ጉልላት የወደቀ አንሺ የመሆን ግዴታ የለባትም፡፡ ካልጠቀመው የወደቀን ማን ያነሳል? ገንዘብ ወድቆ ቢያዩት አልፈውት ይሄዳሉ፡፡ ሎጂክ ነው፡፡ ኢሰብአዊ ሎጂክ፡፡ ሎጂክ የሚባለውን ትምህርት ድሮም ኮሌጅ በነበርኩበት ጊዜ አልወደውም ነበር፡፡ በዚህ አለም ምን ሎጂክ አለና! ምስቅልቅል አለም፡፡ የዛሬው እውነት የነገው ውሸት፡፡ የዛሬው ውሸት የነገ እውነት፡፡ እስኪ የእኔን ነገር እንውሰድ ለምሳሌ፡፡ የሰው ልጅ በዚህ ዘመን ተመልሶ ዳይኖሶር መሆኑ ትክክል ነው? በዳይኖሶሩ ድካም ጅቡ ቁጭ ብዬ ልብላ ማለቱ ትክክል ነው? ይህንን ሎጂክ ዳርዊን ቢያይ ኖሮ ምን ይል ነበር? ሰው ተመልሶ ዳይኖሶር ሲሆን? እና በጉልላት አልፈርድም፡፡ በፈጠረህ ብለህ ጉልላትን እርሳት፡፡ ሥራህን ግን ለምን ተውከ? ለምን ሲገፋህ ተገፋህ? አንተ እራስህ ጭምር ተጠያቂ ነህ፡፡ እነሱ በከፊል አንተ በከፊል- ሃምሳ ሃምሳ...

ደግሞ ካሺሪዋ እንዴት ነው የምታየኝ? ሶስት



አራት አምስት ጊዜ ስታየኝ አየኋት፡፡ ይሄን ጊዜ በልቧ ምን ይሆን የምትለው? ዱርዬ ነው፣ እብድ ነው ወይንስ ድሃ ነው? የእኔ እመቤት፣ ሶስቱንም ነኝ፡፡ ምናልባት ባይጎሳቆል ቆንጆ ሰውዬ ነበር ትል ይሆናል በልቧ፡፡ በልቧ ትመኘኝ ይሆናል ማን ያውቃል፡፡ ካሺሪዋን ድሮ አውቃታለሁ፡፡ እሷ ግን ረስታኝ ይሆናል፡፡ የቡና ቤቱ ባለቤት ሚስት መሆኗን አውቃለሁ፡፡ ታሪኳን እንደ ነገሩኝ ከሆነ ልጅ ሆና እዚህ ቤት ውስጥ በሻይ አፍይነት ትሰራ ነበር አሉ፡፡ የቤቱ ባለቤት ሽማግሌ ናቸው፡፡ እሷ ደግሞ ልጃገረድ ነበረች አሉ፡፡ ታዲያ ሰውነቷ ቢያረጅ ልብ አያረጅም አይደል፣ ሽማግሌው አንድ ቀን እንደ ምንም ክብረ ንፅህናዋን ይወስዳሉ፡፡ አግባብተው ወይንም አስገድደው ይሆናል የደፈሯት፡፡ ይሄንን እንኳን አፍ ሞልቶ መናገር አይቻልም፡፡ ማንም ሰው አላያቸውም፡፡ መቼስ እንዲህ አይነቱን ነውር ነገር እማኝ አቁመው አይሰሩት... ታዲያ ሽማግሌው የልባቸውን ከሰሩ በኋላ ልጅቷን ውጪልኝ አሏት፤ ጉዳቸው እንዳይታወቅ፡፡ ትንሽ ቆይታ ልጅቷ አረገዘች አሉ፡፡ ውጪ ሲሏት አልወጣም አለች፡፡ ኋላም የግድ በሚስትነት ጠቀለሏት፡፡ አሁን ይኸው ወልዳ ከብዳ ንብረታቸውን የምትቆጣጠረው እሷ ነች፡፡ ሰውዬው ሲሞቱ ደግሞ ሁሉንም ነገር ወርሳ ቁጭ ትላለች፡፡ ጎበዝ ናት፤ ሲገፏት አልተገፋችላቸውም፡፡ ይኸው አሁን የተወለወለ ብርጭቆ መስላ ቁጭ ብላለች፡፡

ሕይወት እንደሆነች ሁልጊዜም የመገፈታተር ጨዋታ ነች፡፡ ቢያልፍለትም ባያልፍለትም አንዱ ሌላውን ገፍትሮ ቦታውን ለመያዝ መሞከሩ የማይቀር ነገር ነው፡፡ ታዲያ ይሄንን እያወቅህ ለምን ተገፋሀላቸው? እምቢ አልገፋም ማለት ነበረብህ፡፡ ግዴለም ይግፉኝ፡፡ መገፋት ጥሩ ነው፡፡ ፈጣሪ የጃቸውን ይሰጣቸዋል፡፡ ገፊ ከምትሆን ተገፊ ብትሆን ይሻልሃል፡፡ አሁን ግን ሰላሳ ሳንቲም ባገኝ ኖሮ አንድ ሻይ ጠጥቼ እኔም ዙረቴን እቀጥል ነበር፡፡

ይቺ ቆንጆ ልጅ ምን ይሆን የምታወራው? አብሯት ያለው ሰውዬ ግን አይስቅም፡፡ እሷ ጥርሷን አትከድነውም፡፡ ምናልባት'ኮ ይሄን ጊዜ ሰልችታው ይሆናል ማን የውቃል፡፡ ይቺን የመሰለች ቆንጆ አስጠልታው ይሆናል፡፡ በእጅ የያዙት ወርቅ ነው የሚባለው... ይሄን ጊዜ'ኮ ከእሷ ጋር መተኛት ያስጠላው ይሆናል፡፡ ወቸው ጉድ! ምን አገባህና ደግሞ ስለ ሰው መኝታ ታስብ ጀመር? ለመሆኑ የአንተ መኝታ የት ነው? መናፈሻ ውስጥ! በረንዳ! በረንዳ እያደርክ ለሰው አልጋ ትጨነቃለህ፡፡ ከእብዶችና ከየኔ ቢጤዎች ጋር እያደርክ ለሰው ሞዝቦልጅ አልጋ ታስባለህ፡፡ ለመሆኑ ለምን መጀመሪያ ለራስህ አልሆንክም? ለምን ሲገፋህ ተገፋህላቸው? አሁን እነሱ በአንተ ይስቃሉ፡፡ ቢስቁ ምን ቸገረኝ ታዲያ! እኔ እንደነሱ አልሆን፡፡ እንደ እባብ በሣር ውስጥ በደረቴ ተስቤ ሄጄ ሳያዩኝ ሰው አልነክስ፡፡ የሣር ውስጥ እባብ አይደለሁ፡፡ ጅብ ከመሆን ዳይኖሶር ሆኜ ብጠፋ እመርጣለሁ፡፡



ለማንኛውም ሁላችንም አንድ ቀን መጥፋታችን የማይቀር ነው፡፡ እንኳንስ እንጠፋለን! እልል በቅምጤ ነው! ባንጠፋ ኖሮ ይቺ ዓለም ምንኛ ዝንተ ዓለም በግፈኞች ስታለቅስ ትኖር ነበር! ተመልከት-ለመጀመሪያ ጊዜ ያ ሰውዬ ሳቀላት! አይ እግር! አይ ባት! እርግጠኛ ነኝ እግሯ ላይ አንዲት ጭረት እንኳን አይኖረባትም፡፡ ሰውነቷም ቢሆን እንደ አራስ ልጅ ገላ ለስላሳ ነው የሚሆነው- እርግጠኛ ነኝ፡፡ ምናለበት አሁን አይኖቼ በልብሷ ውስጥ ዘልቀው ሰውነቷን የማየት ችሎታ ቢኖራቸው! እኔ ግን ሰውነቴን ከታጠብኩ ስንት ጊዜ ሆነኝ?

ሰውነቴን ከታጠብኩ አልክ? አዎን! ሰውነትህን ከታጠብክ ሁለት ወይንም ሶስት አመት ይሆንሃል፡፡ ሰው ግን በቀን በቀን ወይንም በሳምንት ይታጠባል፡፡ ቢታጠቡ ግን ምን ዋጋ አለው? ልባቸው ቆሽሾ ሰውነታቸውን ቢታጠቡት ምን ይሰራል? ለመታየት ካልሆነ በስተቀር! እኔ ደግሞ መታየት አልፈልግም፡፡ ከታጠበ ጅብ ያልታጠበ ዳይኖሶር መሆን ይሻለኛል፡፡ ለማንኛውም አንድ ቀን ጎርደሜ ወንዝ ገብቼ እታጠባለሁ፡፡ ግን ባልታጠብስ? የወንዙም ውሃ ቆሻሻ እኔም ቆሻሻ፡፡ ማን ማንን ሊያፀዳ ነው? በቆሸሸ አለም ውስጥ የእኔ ሰውነት መታጠቡ ምን ፋይዳ አለው? እንደቆሸሸኩ እኖራታለሁ፡፡ ወይንም አልኖርም፡፡ ስሞት በግድ ያጥቡኝ የለ፡፡ ባያጥቡኝስ እኔ ምን ቸገረኝ! ቢፈልጉ የትም ይወርውሩኝ፡፡ መቼም እሬሳ መወርወር

ያውቁበታል፡፡ መጀመሪያስ ተወርውሬ አይደል ወደዚህ ቆሻሻ ሕይወት የመጣሁት፡፡ ፈልጌ አልተወለድኩ መቼስ፡፡ መወርወር-ወደ ሕይወት ሲመጡም ከሕይወት ሲሰናበቱም፡፡ ሜዳ ላይ ተወረወርኩ መቃብር ውስጥ ምን ልዩነት አለው? አሁን ግን ሰላሳ ሳንቲም የሚሞላልኝ ሰው ባገኝ ሻይ እጠጣ ነበር..

አ! ሞት እረፍት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይቅርታ ግን አላየሁትም፡፡ እራሴን ግን አልገድልም፡፡ ይሄ የፈሪ ሙያ ነው፡፡ መኖር እፈልጋለሁ፡፡ እንደ ጅብ ሳይሆን እንደ ዳይኖሶር፡፡ ከድሮው እንዲያውም አሁን ነው ነፃነት የሚሰማኝ፡፡ ሞት ግን ደርሰው የሚመለሱበት የእረፍት ቦታ ቢሆንስ ኖሮ? ይሄንን የሕፃን አስተሳሰብህን ወዲያ ጣለው! እንኳንስ መመለስ ያልኖረ፡፡ እንኳን በዚያው መቅረት ሆነ! ስንቱ ይቺ አለም የማትፈለገው ጨካኝ ተመልሶ እየመጣ ሰውን ሲያሰቃይ ይኖር ነበር፡፡ እራሴንስ አልገድልም፡፡ እራሴን ለመግደል አስቤ አላውቅም፡፡ የመጣው ይምጣ እንጂ እስከ መጨረሻው መኖርን እመርጣለሁ፡፡ ማነው እሱ የመኖር ወይንም ያለመኖር ጥያቄ የፍልስፍና እንብርት ጥያቄ ነው ያለው? ሕይወት እንኳን ፍቺ ሲያጣ ለምን ሰዎች መኖርን ይመርጣሉ? በነገራችን ላይ የዚያች ቆንጆ ልጅ እንብርት ምን ይመስል ይሆን? የሴት ልጅ እንብርት ምን ይመስል ይሆን? የሴት ልጅ እንብርት ማየት ደስ ይላል፡፡ ባት፣ ጡት፣ እንብርት-የውበት ሶስቱ ስላሴዎች፡፡ አንተም



ከሥራህ ባያስወጡህ ኖሮ ስንት እንብርት ታይ ነበር! አሁን ግን እንደዚህ ሆነህ ስለ ሴት እንብርት ማሰብ ምን ይሰራልሃል? ምን ላድርግ የፍልስፍና እንብርት ብዬ ሳስብ ፊት ለፊቴ የተቀመጠችው ቆንጆ ልጅ እያየሁ እንብርት ትዝ አለኝ፡፡

አሁን ሁሉን ነገር ተውውና ለዚህ ጥያቄ ስጠኝ፡፡ ለምን ሲገፉህ ተገፋህ? በቃ አትጨቅጭቀኝ! ገፉኝ ገፉኝ! ወደቅሁ ወደቅሁ! እግዜር ይመስገን ሰው ባይቀበለኝ መሬት ተቀብላኛለች፡፡ መንገዱ ተቀበለኝ፡፡ መናፈሻው ተቀበለኝ፡፡ ይሄ ሎተሪ ሻጭ ደግሞ ወደኔ እንዳይመጣ! አዎን ወደኔ ነው የሚመጣው እኔንም ሎተሪ ቁረጥ ሊለኝ? እባክህ ተወኝ ባለ ሎተሪ... ሕይወት እራሷ ሎተሪ ናት፡፡ የገንዘብ ሎተሪ ምን ይሰራል? ይቺ ቆንጆ ልጅ ልትሄድ ነው መሰለኝ... ከተቀመጠችበት ተነሳች፡፡ ሰውዬው የጠጡትን ለስላሳ ዋጋ ከፈለ፡፡ መልሱን ተቀበለ፡፡ ምናለበት አሁን ከተቀበለው መልስ ሰላሳ ሳንቲም ቢሞላልኛና ሻይ ብጠጣ? ልጂቷ ከኋላዋ እንዴት ቆንጆ ነች! በቃ በሕይወቴ ሁለተኛ ደግሜ አላያትም ማለት ነው፡፡ አንዳችን ለሌለው ባይታወር ሆነን ኖረን በመጨረሻ እንደዚህ እንለያያለን፡፡ በይ ደህና ሁኚልኝ የኔ ቆንጆ፡፡ ቆንጆ ነገርን ባያገኙት እንኳን ቢያዩት ደስ ይላል፡፡ ምናልባት'ኮ አብሯት ካለው ሰውዬ ይልቅ እኔ ልጅቷን በማየት ብቻ ይበልጥ ተደስቼ ይሆናል፡፡ በሃሳቤ አቅፌታለሁ፣ ሰውነቷን ዳብሼዋለሁ፣ ከንፈሮቿን ስሜአቸዋለሁ፣ አብሬአት

ተኝቼ ተነስቼአለሁ። ለማንኛውም ደህና ሁኚልኝ የእኔ ቆንጆ! ሁለተኛ አላይሽም። ስትለይኝ ከእሁኑ ብቸኝነት ተሰማኝ። በመንፈስ አብረን ነበርን ማለት ነው። አሁን ግን ሄደች በቃ። ሁሉም ሰው እየመጣ ሄደ። ትንሽ ቀይቼ ብቻዬን መቅረቴ ነው። ደግነቱ ሁላችንም ብንሆን ብቸኞ ች ነን። አሁን ግን ሰላሳ ሳንቲም ሞልተውልኝ ቢሄዱ አንድ ሻይ እጠጣ ነበር...

እግዜር ይስጣቸው፤ እስካሁን በሰላም ተቀምጠው ቆየሁ። እስኪ ልሂድ- ምናልባት መንገድ ላይ ሰላሳ ሳንቲም ወድቆ አገኝ ይሆናል ማን ያውቃል... ለማንኛውም ልውጣና እድሌን ልሞክር። በጣም ርቦኛል። መቼ ነበር ለመጨረሻ ጊዜ የበላሁት? ትናንት ነው? እኔ እንጃ! ረስቼዋለሁ። ለአንድ ሚሊዮን አንድ መቶኛ ጊዜ ልጠይቅህ- ስራህን ለምን ተውክ? አላሰራ አሉኛ! ስታስበው ሰው ወዶ ስራውን ይተዋል? ለምንንና እንዴት እንደገፉህ አንተ እራስህም ታውቀዋለህ። አሁን ብዘረዝርልህ ምን ዋጋ አለው? ግዴለም! በመጨረሻ ገፊም ተገፊም ወደማይኖርበት አለም ተራ በተራ እንሄዳታለን። ህይወት አጭር ናት። ከሃምሳ አመታት በኋላ የአሁኖቹ ገፊዎችም ሆንን ተገፊዎች ወይ ሞተናል ወይም ከሞት አፋፍ ላይ ነን። ታዲያ የዛሬው መገፈታተር ምን ዋጋ አለው? እዚያኛው አለም ህይወት ኖረም አልኖረ ይሄኛውን አለም ለምን የመገፈታተሪያ መድረክ እናደርገዋለን? ስንሞት ደግሞ ሶስት ክንድ መሬት ብቻ አይደለም የሚበቃን? እውነትም ገፊና ተገፊ ባይኖር ያስኛል። ወይ ነዶ! ማንም ለማንም ግድ የለውም! እስኪ ለማንኛውም ከዚህ ልውጣና የእስር ሳንቲም ቆሎ ገዝቼ ልቆረጣጥም...

በዚህ አራተኛ የአጫጭር ልብወለድ ታሪኮች ስብስብ በሆነው ስራው፣ ደራሲ ሙሉጌታ ጉደታ 'የተገፋትና የተረሱት' ስማበለው ሆኖ ነው የቀረበው። በዝምታ ለሚሰቃዩ ምስኪን ነፍሶች ይናገራል። ጌትነት፣ አስቻለው፣ ዲነጋ፣ ሱዚ እንዲሁም "ስንታየሁ እስስቱ" ሳይቀር እጣቸው በዚህ ትርጉም የለሽ (አብዘርድ) አለም መናወዝ ነው። "ሁሉም ነገር የማታ ማታ ባዶነት በሆነው ህልውና፣ የቀረ ተስፋ ቢኖር የህይወትን አስከፊ ገፅታ የምንቋቋምበት የመተዛዘንና የፌዝ ስሜት (ሴንስ ኦፍ ሂውመር) ነው።" የሚለን ይመስላል ደራሲው። በእነዚህ ሰባት ታሪኮች ሙሉጌታ ጉደታ ማህበራዊና ስነልቡናዊ ጭብጦችን ከነፍልስፍናዊ አንደምታቸው በማንሳት በተለመደው ቴክኒካዊ ውበትና የተባ ቋንቋ ከሽኖ ወደ አርኪ ዳር ያደርሳቸዋል።

ዋጋው ብር 8.00

ንግድ ማተሚያ ድርጅት